# የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት

በ

ገዛኸኝ አሰፋ በየነ

በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ቴሲስ

አማካሪ

ዶ/ር ብርሃኑ ማቲዎስ

የካቲት 1999 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

# የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት

በ

ገዛኸኝ አሰፋ በየነ

በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ቴሲስ

አማካሪ

ዶ/ር ብርሃኑ ማቲዎስ

የካቲት 1999 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ት/ቤት

# የከምባታ ህገረሰባዊ ትውን ጥበባት

በ

ገዛኸኝ አሰፋ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| ስም | ፊርማ |
|---|---|
| 1. ብርሃኑ ማቲዎስ (ዶ/ር) አማካሪ | ---------- |
| 2. አያሌው ገብሬ (ዶ/ር) የውጭ ፈታኝ | ---------- |
| 3. ዘሪሁን አስፋው (አቶ) የውስጥ ፈታኝ | ---------- |

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አጠቃሎ

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አንድ ሕዝብ ባህላዊ ወይም ልማዳዊ ልብሶቹን ለብሶ፣ በሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ታጅቦ፣ በልዩ ልዩ ስርዓቶች ላይ የሚተወናቸው ሕዝባዊ ባህላዊ ሀብቶቹ ናቸው። እነዚህ ሕዝባዊ ባህላዊ ሀብቶች ፎክሎር ተብሎ በሚጠራው የእውቀት ዘርፍ ውስጥ ይካተታሉ።

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ከከምባታ ፎክሎራዊ የሕዝብ ሀብቶች መካከል የሀገረሰብ ትውን ጥበባቱን መሰብሰብ፣ ማጥናት እና ሰንዶ ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማቆየት ነው። ከከምባቶች ፎክሎራዊ ህይወት ውስጥ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱን የሚመለከተው ይህ ጥናት የተደረገው ከመስክ እና ከቤተመፃህፍት ተገኝተው ከተነበቡ የተለያዩ የጽሑፍ የመረጃ ምንጮች፣ እንዲሁም ከኢንተርኔት ከተገኙ ወቅታዊ መረጃዎች ለጥናቱ አግባብነት ያላቸውን በመምረጥ ነው። አስፈላጊ የሆኑትንም ተጨባጭ መረጃዎች በመስኩ ላይ በአካል በመገኘት ከተፈጥሯዊ መቼቱ እንዲሁም በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ፊልም፣ በመቅረፀ ድምፅ ተቀርፀው ቀርበዋል። ጥናቱ የተመሰረተውም በዋነኛነት በተግባር (activities) በሚከወኑትና ማህበረሰቡን አጉልብተው በሚገልጹት ላይ ሲሆን በቂ ትንታኔና ገለፃም ተሰጥቶባቸዋል።

በዚሁ መሰረት በተደረገው ጥናት የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ማህበረሰቡ ስለህይወት ያለውን ስሜት ያንፀባርቃሉ። የሚነገሩት፣ የሚተረኩት፣ የሚዜሙት ጥበባቱም የታዳሚዎቹን፣ የአዳማቂዎቹን እና የተሳላፊ ተመልካቾቹን ትኩረት የሚስቡ ናቸው። ከምባቶች ዳንሳቸውን በደስታ ወቅት (ለምሳሌ በወሊድ)፣ በሀዘን ወቅት፣ እንዲሁም በሃይማኖታዊ ስርዓቶች ወቅት ሁሉ ይከውናሉ። ማህበራዊ ተግባራቸውም የማህበረሰቡን ውስጣዊ ስሜት መግለፅ ነው። የህይወት ጫናቸው ይንፀባረቅበታል፣ የመንፈስ ስብራታቸውንም ይጠግኑበታል። በአጠቃላይ የከምባታ ትውን ጥበባት በህብረት የሚተወኑ፣ ከወገብ በላይ ባሉ የሰውነት ክፍሎች እንቅስቃሴ የሚቀርቡ ሲሆኑ የትውን ጥበባቱ ቅርጽም በክብ መልክ የሚከናወን እንደሆነም በጥናቱ ታይቷል።

# ምስጋና

ይህንን ጥናት ለዚህ ደረጃ ለማብቃት ባለውለታዎቼ ብዙ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የጥናቱ አማካሪ ዶ/ር ብርሃኑ ማቲዎስ ስለ ክልሉ እውቀቱ ከፍ እንዲልና ጥናቱ በተገቢው አቅጣጫ እንዲሄድ በመምራት ብዙ ደክመዋልና ይመስገናሉ፡፡

የጥናቱን የተወሰነ ወጪ በመሸፈን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃና የምርምር ክፍል ላደረገው እገዛም አመሰግነዋለሁ፡፡

የመስክ ምርምሩን ባከናወንኩበት ጊዜም ከጐኔ ባለመለየት፣ በማስተርጐም እና ተፈላጊዎቹን መረጃ አቀባዮች በማገናኘት ጭምር የደከመልኝ ወርቁ ጌጂባ ውለታ እጅግ ብዙ ነው፡፡ በመኖሪያ ቤቱ እንግዶቹን በማስተናገድ፣ በመንከባከብና እንዲረዱኝም በማግባባት ታላቅ አስተዋፅኦ አበርክቷልና እጅግ አመሰግነዋለሁ፡፡

በአባሪው የተጠቀሱት መረጃ አቀባዮች ሁሉ ባህላቸውን እንዳጠና፣ እንድቀርፅና፣ ጠይቄያቸውም እንድረዳ ስለተባበሩኝ፣ እንዲሁም ያለንፍገት በጠየኳቸው ሁሉ ስላገዙኝ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

ለመስሪያ ቤቴ እና ለቤተሰቦቼም ሁሉ በጠየኳቸው እርዳታ ሁሉ ከጐኔ ስለነበሩ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በተለይም ወንድሜ ጌታቸው አሰፋ ዘወትር ‹‹ምንደረስክ›› እያለ በሞራልም በሀሳብም ከጐኔ ስለተገኘ ባለውለታዬ ነው፡፡ ይህንን ፅሁፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በኮምፒውተሯ በመፃፍ፣ በማረምና በማስተካከል በፈለኩት ጊዜም እንዲደርስልኝ የእረፍት ጊዜዋን ጭምር በመሰዋት ለተባበረችኝ ለወ/ሮ ባንችጊዜ ስንታየሁ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ስማቸው ያልተጠቀሰ በየትኛውም መልኩ የረዱኝን ሁሉ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ገዛኸኝ አሰፋ በየነ

# ማውጫ


ገጽ

- አጠቃሎ ---------- I
- ምስጋና ---------- II
- ማውጫ ---------- III
- መግቢያ ---------- V

ምዕራፍ 1. አጠቃላይ ዳራ ---------- 1

1.1 የጥናቱ ስልትና አካሄድ ---------- 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ---------- 1

1.3 የጥናቱ አላማ ---------- 2

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ---------- 3

1.5 የጥናቱ ትኩረትና ወሰን ---------- 4

1.6 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ---------- 4

1.7 የአጠናን ዘዴ ---------- 5

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ---------- 6

ምዕራፍ 2. የከምባታ መልክዓ ምድራዊና ታሪካዊ ገጽታ ---------- 7

2.1. የከምባታ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ---------- 7

2.2 የከምባታ ታሪካዊ ገጽታ ---------- 9

ምዕራፍ 3. ክለሣ ድርሳን ---------- 13

3.1 ፎክሎርና የአጠናኑ ትውሮች ---------- 13

3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ---------- 22

ምዕራፍ 4. የከምባታ ሀገረ ሰባዊ ትውን ጥበባት ---------- 27

4.1 ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ---------- 27

4.1.1 ሀገረሰብ ዘፈን ---------- 29

4.1.2 ሀገረሰብ ዳንስ---------- 34

4.1.3 ሀገረሰብ ድራማ ---------- 36

4.1.4 የሀገረሰብ ሙዚቃ፣ ዳንስ ድራማ መስተጋብር ---------- 38



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምዕራፍ 5. ሀገረሰባዊ ትወና በልዩ ልዩ ሃይማኖቶች፣ ልማዶችና ስርዓቶች --- 56
5.1 ፀዋትወ ሃይማኖት------------------------------- 56
5.1.1 ሀገር በቀል ሃይማኖትና ትወና ----------------------------- 59
5.1.2 ታሪካዊ ሃይማኖትና ትወና -------------------------------- 62
5.2 የልጆች ጨዋታዎችና ትውና --------------------------------------- 71
5.2.1 ደነባ /Danaba'a/ -------------------------------------- 72
5.2.2 ኣዴ /Ade'e/ ----------------------------------------- 73
5.3 የልደት ወቅት አተዋወን ----------------------------------------- 73
5.4 የግርዛት ወቅት አተዋወን ----------------------------------------- 78
5.5 የሠርግ ወቅት አተዋወን ----------------------------------------- 82
5.6 የሞት ወቅት አተዋወን ----------------------------------------- 86
ምዕራፍ 6 -------------------------------------------------------------- 93
- ማጠቃለያ ---------------------------------------------------------- 93
- ማጣቀሻ ጽሑፎች / References/ ----------------------------------- 98
- አባሪዎች I. ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው-------------------------------- 104
II. የመረጃ መግለጫ------------------------------------------ 106
III. የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ--------------------- 108

# መግቢያ

በትወና ሰው ራሱን ለእራሱ ይገልፃል:: ይህም በሁለት መንገዶች ይገለፃል:: አንደኛው ተዋናዩ የተሰጠውን ተግባር በሚገባ በመተወኑ ወይም ባለመተወኑ ስለ ራሱ የሚገልፀው ነገር ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ አንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን በሌላኛው ማህበረሰብ ወይም ቡድን የተፈጠረውን እና ለእይታ የቀረበውን በአግባቡ በመመልከትና በድርጊቱ በመካፈል ራሱን ለሌላኛው ቡድን የሚያሳውቅበት መንገድ ነው(Turner, 1986)::

በአንትሮፖሎጂስቶቹ አመለካከት ትወና አንድን ድርጊት በመቅዳት፣ በመኮረጅ፣ወይም አስመስሎ በመተወን እንደሚከናወን ይገለፃል (Aristotle in Schechner, 1988):: ትወና የሰውን ተራክቦ ማጥኛ መሰረታዊ መንገድም ነው:: ህብረተሰቡን በጋራ የሚያገለግል፣ የጋራ ሀብት፣ ለተግባቦትም የታዳሚ መኖር ወሳኝ የሆነበት ነገር ነው:: የሀገረሰብ ልብስ ተለብሶ፣ በሀገረሰብ የሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅቦ የሚከወነውን ነው ሙያው የሚያጠናው (ፈቃደ፣ 1991)::

የጥናቱ ትኩረት የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በማህበረሰቡ ተራክቧዊ እሴቶች ላይ ያላቸውን ሚና በመመርመሩ ላይ ነው:: በትውን ጥበባቱ ከምባቶች ራሳቸውን ይገልፃሉ፤ ልማዳዊ ስርዓቶቻቸውንም ለልጅ ልጆቻቸው ያስተላልፋሉ:: ጥበባቱ እርስ በርሳቸው የሚማማሩባቸው፣ የሚፅናኑባቸው፣ የሚዝናኑባቸውና የሚፋቀሩባቸውም ናቸው::

ጥናቱ ስድስት ምዕራፎችን ይዟል:: የጥናቱን አጠቃላይ ዳራ አስተዋውቆ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን አስፈላጊነት የጥናቱን ትኩረትና ወሰን፣ ዓላማውን እና ዘዴውን የሚያቀርበው የመጀመሪያው ምእራፍ ነው:: በሁለተኛው ምእራፍ የተዛማጅ ስራዎችና ንድፈ ሃሳቦዊ ቅኝት ይቀርብበታል:: ስለ ዞኑ ባህላዊ ፣ አካባቢያዊና ታሪካዊ ዳሰሳ የሚያደርገው ሦስተኛው ምእራፍ ነው:: የከምባቶችን አካባቢያዊ ገፅታንና ታሪካዊ ዳራን የሚቃኘው ሦስተኛው ምዕራፍ እንደመንደርደሪያ ሆኖ ወደ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ የሚያዘልቅ ነው:: በአራተኛው ምዕራፍ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱን ፀዋትው (genres) የሚመለከቱት ሀገረሰብ ዘፈን፣ ሀገረሰብ ዳንስ (ጭፈራ)፣ ሀገረሰብ ድራማ የተሰኙት ርዕሶች እንዲካተቱ ተደርገዋል:: ከምዕራፍ ሁለት እስከ ምዕራፍ አራት ባሉት ክፍሎች ውስጥ በከምባቶች የአኗኗር ልማዶችና ስርዓቶች ውስጥ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቶቻቸው እንዴት እንደተንፀባረቁ፣ ምን ያህሎቹ አብረዋቸው እንደዘለቁ፣ የመተላለፊያ መንገዶቻቸው፣ ሁሉ ይዳስሳሉ:: በተጨማሪም በሀገረሰባዊ ልማዶቻቸውና

ሥርዓቶቻቸው ውስጥ ትወና ምን መልክ እንዳለው በትኩረት የሚታይ ነው። ይህንን በተመለከተ በምዕራፍ አምስት ውስጥ ሃይማኖትና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን እንዲሁም ደግሞ በልደት፣ በግርዘት፣ በትዳር ምስረታ ወቅት እና በሞት ወቅት ያሉት ትወናዎች ተካተዋል። ስድስተኛው ምዕራፍ የጥናቱን ማጠቃለያ የያዘ ነው። በጥናቱ ሂደት የተደረሰበትን መደምደሚያ፣ የጥናቱን አበይት ግኝቶች እና ጥናቱ የሚያቀርባቸውን አስተያየቶች አካቶ ይዟል። በመቀጠልም ጥናቱን ለማድረግ ያገለገሉና በዋቢነት የረዱ ማጣቀሻ ጽሑፎችን የሚዘረዝረው ክፍል ይቀርባል። እንዲሁም የጥናቱን ሀሳብ እንዲያጐለብቱ የተጠቀመባቸውን አባሪዎች አካቷል። እነዚህም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የሰጡ ተባባሪዎች ዝርዝር፣ ስለመረጃ አሰባሰቡ ሂደት የሚያመለክቱ መግለጫዎች፣ የቃለ መጠይቅ፣ የምልከታና የተለያዩ ትወናዎችን መግለጫዎች የሚያመለክቱ ጠቋሚ ሰነዶች ናቸው። ጥናቱ ሲደረግ ከቤተመፃህፍትና ከመስክ፣ ከኢንተርኔት፣ ጠቃሚ መረጃዎችን በመውሰድ ጥቅም ላይ እንደዋሉ አስቀድሞ ተጠቁሟል። እነዚህም መረጃዎች ጽሑፋዊ፣ ቃላዊ፣ ህትመታዊ፣ ኤሌክትሮኒክሳዊ ናቸው። ለጥናቱ ስራም አጋዥ እንደመሆናቸው መጠን እንደአስፈላጊነቱ በየተጠቀሱበት ዓውድ የሚገኙባቸውን ገጾች፣ ስፍራዎች በደራሲዎች ስሞችና በየታተሙበት ጊዜ ቅደም ተከተል ጥቆማ እየተደረገባቸው እንዲመላከቱ ተደርገው ቀርበዋል።

በጥናቱ ሂደት ጥቅም ላይ የዋሉ ምንጮችን በማጣቀሻ ጽሁፎች (References) ዝርዝር ውስጥ እንደተገኙበት ቋንቋ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች አባሪ ተደርገዋል። በጥናቱ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በቀጥታ የተወሰዱ ጥቅሶች በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር መሰረት፣ የአማርኛዎቹ ምንጮች ደግሞ በኢትዮጵያውያኑ የዘመን አቆጣጠር መሰረት ነው የቀረቡት።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. አጠቃላይ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ የከምባታ ህገረሰባዊ ትውን ጥበባት ለሚለው ጥናት ፍሬ ነገሮች አቀራረብ የሚያመለክቱ ሃሳቦች ይቀርባሉ። የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱን ሂደት፣ ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ ንድፈሃሳባዊ ትውሮችን የሚመለከቱ ነጥቦች ተገልፀው ይገኛሉ።

### 1.1 የጥናቱ ስልትና አካሄድ

ጥናቱ ስለ ህገረሰባዊ ትውን ጥበባት በአጠቃላይ እና ትወናን፣ ህገረሰብ ጥበብን፣ ህገረሰብ ድራማን ከመሳሰሉት ንድፈ ሀሳቦች በተጨማሪ ስለጠቅላላው ፎክሎር በቀረቡት ገለፃዎች መሠረት ተካሂዷል። ከዚህም አኳያ ከስነሰብ /Anthropology/፣ ከስነ ፅሁፍ ምሁራንና አቀንቃኞች ንድፈ ሃሳብ አንፃር ለማየት ተሞክሯል። ፎክ አርት /folk art/ ሊጠና ከሚችልባቸው አራት አንፃሮች አንደኛ፣ ህገረሰብ ጥበብን እንደ ታሪክ ቅሪት በመቁጠር መሰብሰብ፣ ሁለተኛ ገለፃና ትንታኔ በመስጠት፣ ሦስተኛ ህገረሰብ ጥበብን እንደ ባህል መግለጫ ወስዶ በማየት፣ አራተኛ ህገረሰብ ጥበብን እንደ ሰብአዊነትና የሰው ባህርይ መቅረጫ በመውሰድ የተቀነቀኑትን ተመልክቷል።

ጥናቱም ከእነዚሁ አራት አንፃሮች የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን በዋነኛነት፤ ቀሪዎቹን ሁለት አንፃሮች ደግሞ በደጋፊነት ወስዶ ተጠቅሞባቸዋል። የማህበረሰቡን አጠቃላይ መለያዎች፣ እሡ ስለ እሡ ይገልፁኛል የሚላቸውን፣ የሚያከብራቸውንና የሚጠብቃቸውን መገለጫዎቹን ያመለክታል፣ በሰው ለሰው ተራክቦና ተግባቦታዊ ባህርያት የተፈጠሩ ለውጦችንም በንፅፅር ያቀርባል። ማህበረሰቡ በዕለት ገጠመኙ የሚተውናቸውን፣ በስርዓታዊ ሁኔታዎች የሚፈፅማቸውን፣ በልማዳዊነታቸውም የሚተገብራቸውን ትውን ጥበባቱን በመሰብሰብ፣ በመሰነድና በማጥናት ለመጪውም ግኝቱን ይጠቁማል።

### 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ከምባቶች ሰፊ ታሪክ፣ የራሳቸው የሆነ ባህልና የፎክሎር ሀብቶች አሏቸው። ይሁን እንጂ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት፣ የባለሙያ እገዛ ተደርጐበት የተመረመረ፣ የተሰነደና፣ ለመጪው ትውልድ ሊተላለፍ የሚችል የፎክሎር ጥናት በበቂ አልተደረገም። ከፎክሎር የቃላዊነትና የተለዋዋጭነት ባህርይ የተነሳም የጠፋው ጠፍቶ፣ የተለወጠው ተለውጦ፣

የተቀየጠው ተቀይጦ፣ ወዘተ. የማህበረሰቡ መለያ አሻራዎች ደብዛቸው ከመጥፋቱ በፊት ያሉትንና የተቻሉትን ያህል አሰባስቦ ለመሰነድ ማሰቡ የመጀመሪያው ምክንያት ነው።

ሌላው ምክንያት ደግሞ በሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ ዙሪያ ወደፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ እና ጥልቅ ጥናቶች፣ እንዲሁም በአጠቃላይ የከምባታን ፎክሎር የተመለከተ ጥናት ለማድረግ ለሚነሳ በማነፃፀሪያ ጥናትነት ሊረዳ የሚችል ግብዓት ማቅረብ መታሰቡ ነው። የመጨረሻው ምክንያትም የብሔረሰቡ ሀገረሰባዊ ጥበብ ያለበትን ደረጃ በማመላከት፣ በመቀጠልም ምን መደረግ አለበት የሚል የመፍትሔ ሃሳብ ለማንሳት በማሰብ ነው ጥናቱ የተካሄደው።

### 1.3 የጥናቱ ዓላማ

ጥናቱ የሚከተሉት አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

ሀ. አጠቃላይ ዓላማዎች ደው

- የከምባቶች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ምን ይዘት እንዳሏቸውና፣ ከምባቶችን እንዴት እንደሚገልጿቸው መለየት፣
- የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ያሉበትን ደረጃ መመልከትና ተፅእኖዎችም እስከ ምን ድረስ እንደደረሱ መመርመር ናቸው።

ለ. ዝርዝር ዓላማዎች

- የከምባቶችን ትውን ጥበባት የአተዋወን ስልቶች መለየትና የታዳሚዎች ሚና እና ተሳትፎን መመርመር፣
- የትውን ጥበባቱን ማህበራዊ ተግባራትና ለከምባቶች ማህበራዊ ህይወት ያሏቸውን አስተዋፅኦዎች መለየት፣
- ትውን ጥበባቱ የከምባቶችን የህይወት ተሞክሮዎች እንዴት እንደሚገልጹ እና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ማመልከት፣
- የከምባቶች ትውን ጥበባት ባህላዊ፣ ጥበባዊ እና ውበታዊ እሴቶቻቸውን ማሳየት፣
- የትወናን አወንታዊና አሉታዊ ተግባራት ማመልከት፣
- ከምባቶች ትውን ጥበባቸውን እንዴት እንደኖሩበትና እንዴት ተለወጠ የሚሉትን መርምሮ ማሳየት ናቸው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የባህል ፖሊሲ (1990) የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቅርሶች፣ ታሪኮች፣ ሥነ-ጥበባት፣ ልዩ ልዩ ትውፊቶች /ተረቶቻቸው፣ ምሳሌያዊ ንግግሮቻቸው፣ ጭፈራ፣ ውዝዋዜና ዘፈኖቻቸው፣ ወዘተ... /ወጥነታቸውን እንደጠብቁ/ ሳይበረዙና ሳይከለሱ/ ተሰብስበው፣ ተመዝግበውና ተጠንተው በእኩልነት እንዲታወቁና እንዲበለፅጉ ለማድረግ፣ እንደሚፈልግ ይገልፃል:: (ሰረዙ ለትኩረት ሲባል በአጥኚው የተጨመረ ነው::)ይህ ጥናት ይህንን ፍላጐት ለማሟላት በመሞከሩና በአጋዥነቱ ተፈላጊነት ይኖረዋል::

ከዚህም በተጨማሪ የከምባታ ህገረሰባዊ ትውን ጥበባትና ማህበራዊ ተግባራቸው መጠናቱ የሚኖረውን አስፈላጊነት እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል::

- በአጠቃላይ የፎክሎር፣ በተናጠል ደግሞ የህገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ፣ የከምባታን ማህበረሰብ የእርስ በርስ ተራክቦና ተግባቦት፣ /interaction and communication/ የአኗኗር ዘይቤያቸውን እና ሥርዓቶቻቸውን፣ የልዩ ልዩ ስሜቶቻቸውን መገለጫዎች ምን እንደሆኑ ለመረዳት፣
- ከህዝቦች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስና የመቀላቀል ማህበራዊና ተፈጥሯዊ ባህርይ የተነሳ እንዲሁም ከኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ታሪካዊ አጋጣሚዎች የተነሳ፣ የማህበረሰቡ ፎክሎር የመለወጥ፣ የመቀየጥ፣ የመዋጥ ባህርይ የማሳየት አዝማሚያዎች በመከሰት ላይ በመሆናቸው ያሉበትን ደረጃ ለማሳየትና ያልተበረዙትንም እንዳሉ ቀርጾ ለማቆየት ለመሞከር፣
- በፌደራል ደረጃም ሆነ በየስልጣን ተዋረዱ በሚገኙ መዋቅሮች፣ እንዲሁም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችም ከምባቶችን ይበልጥ እንዲያውቋቸው፣ ስሜቶቻቸውን፣ ፍላጐቶቻቸውንና ዝንባሌዎቻቸውን ቀርበው የሚረዱበትን መንገድ ለማመላከት፣ በዚህም ተጠቅመው የህዝቡን ፍላጐት ጠብቀውና አክብረው ለሀገራዊ ጉዳዮች ማስተባበር የሚችሉባቸውን አቅጣጫዎች ለማመላከት፣
- በሀገራችን በተደረጉት ፎክሎራዊ የአካዳሚ ጥናቶች አንድ ተጨማሪ ግብዓት ለማከልና ለቀጣይ ጥናቶችም የበኩሉን አስተዋጽኦ ከማበርከት አኳያ ይህ ጥናት አስፈላጊነት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 1.5 የጥናቱ ትኩረትና ወሰን

ጥናቱ የሚያተኩረው በከምባታ ማህበረሰብ ላይ ሲሆን የጥናቱ ጂኦግራፊያዊ አካባቢውም የከምባቶችን ማእከላዊ ስፍራ ዱራሜን መነሻ አድርጐ እስከ አንገጫ ይዘልቃል:: ይህም በማእከል እና ከማእከሉ በራቁ ወረዳዎች የሚገኙ ትውን ጥበባትን ይዘት በንፅፅር ለማየት፣ የለወጡን እና የማህበረሰቡን ተራክቧዊ ውጤቶችም መመርመር እንዲያስችል ነው::

ስለሆነም አጥኚው ከቤተመፃህፍት እና ከመስክ የሰበሰባቸው መረጃዎች በእነዚህ አካባቢዎች ላይ የሚያተኩሩትን ነው:: ለተጨማሪ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ግን ከማህበራዊ መቼቱ ውጭ ከሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት ጋር በተደረጉ ውይይቶች ስለ ህዝቡ ትውን ጥበባትና በአጠቃላይም ስለባህሉ አጠቃላይ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል::

ከሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ዋና ዋና ፀዋትው (genres) አንፃር ሀገረሰብ ሙዚቃ፣ ሀገረሰብ ዳንስ፣ ሀገረሰብ ድራማ ላይ ጥናቱ ያተኩራል:: ይኸውም አጥኚው ሊደርስባቸው የቻለውን ያህል መረጃዎች ያህል ይዞ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት ከዚህ ጥናት አስቀድሞ በተጠኑ የከምባታ ፎክሎር ቅርጾች ላይ የተደረጉትን ምርምሮች እንደመነሻ በመውሰድ እነሱን ላለመድገም ሲባል ሙሉ ትኩረቱን በትውን ጥበባቱ ላይ በማድረግ ትወናቸውን ማእከል ያደረገ ጥናት /performance — centered approach/ በማቅረብ አንፃር የተወሰነ ነው::

## 1.6 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ጥናቱ ከቤተመፃህፍት እና ከመስክ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የሚደገፍ ሆኖ አይነታዊ /qualitative/ በሆነ ዘዴ ላይ የተመሰረተ ነው:: አጥኚው ለጥናቱ በመረጣቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች (ቴፕ፣ ቪዲዮ፣ ፎቶ ካሜራ) በመታገዝ በቀጥታ በመስኩ፣ በዞኑ ዋና ከተማ ዱራሜ በአካል በመገኘት፣ከብሄረሰቡ ባህል አዋቂዎች፣ ከታዋቂ ሰዎች፣ ከቃል ታሪክ አዋቂዎች በቃለ መጠይቅና በምልከታ በመጠቀም መረጃዎቹ ተሰብስበዋል::

በጥናቱ ሂደት አጥኚው በመስክ ቆይታው በቃለመጠይቅ ያሰባሰባቸውን መረጃዎች የተቻለውን ያህል ቀድቶ ይዟል:: በተጨማሪም በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የማህበረሰቡ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አባላት ትውን ጥበባቸውን ሲተውኑ ተመልክቶ በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎቹ ቀርጾ ለማስቀረት ጥረት አድርጓል። ይሁን እንጂ በዞኑ ከሚገኙት ሌሎች ተዛማጅ ህዝቦች ጋር በተደረገው ታሪካዊ የመዋሃድ ሂደትና የትውን ጥበባቱ የመለወጥ አዝማሚያ ነባሩን ቅርስ እንዳለ ለማስቀረት ያደረገው ጥረት ሙሉ በሙሉ የተሳካ ነበር ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም ከተፈጥሯዊ መቼቱ ተፈጥሯዊ ባህሪውን እንደጠበቀ ሊገኝ ያልቻለውን በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ተጠቅሞ ነባሩን የማህበረሰቡን ባህል ያውቃሉ የተባሉትን አዋቂ ሰዎችም ጭምር ተሳታፊ በማድረግ ለመቅረጽ የተሞከረ ሲሆን ትኩረቱንም ይህንኑ ወደመሰነዱና አስፈላጊ የሆኑ ትንታኔዎችን ወደመስጠቱ አምርቷል።

ከሀምሌ ወር 1998 ዓ.ም እስከ ታህሳስ ወር 1999 ዓ.ም ድረስ ለጥናቱ ከተመረጡ የብሔረሰቡ አባላት ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል። እነዚህም 15 የብሔረሰቡ አባላት በእድሜ፣ በፆታ፣ በትምህርት ደረጃ የተለያዩ ናቸው። የዕድሜ ተዋፅኦዎቻቸው በአማካይ ከ40 ዓመት እስከ 85 ዓመት ይደርሳል። በፆታ ደረጃ 11 ወንዶች ሲሆኑ አራቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው። በትምህርት ደረጃም ምንም አካዳሚያዊ ትምህርት ካልተማሩት የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ እስካላቸው ያካተተ ነው። በነዚህ መስፈርቶች በመታገዝ ከተመረጡት የመረጃ አቀባዮች አጥኚው በወሰነው የጥናቱ ርዕሰ ነገር አቅጣጫ ስለሚጠኑት የፎክሎር ቅርፆች ተገቢ መረጃዎችን አሰባስቧል። እነዚህም ከጥናት ወረቀቱ በተጨማሪ በ5 የቪዲዮ ካሴቶች፣ በ8 የኦዲዮ ካሴቶችና በ3 የፎቶ ፊልሞች በ8 ፍሎፒ ዲስኮች አማካይነት ተቀርፀው ቀርበዋል።

### 1.7 የአጠናን ዘዴ

በፎክሎር አዋቂዎች (Goldstein; Wilson; 1986; ፈቃደ፣ 1991) ከመስክ መረጃ የመሰብሰቢያ እንደሆኑ የተገለፁትን፣ እንዲሁም የመስክ ስራንና የመስከኛውን ሃላፊነትና ግዴታዎች በተመለከተ ካሰፈሯቸው በመነሳት መረጃዎቹን ከተፈጥሮአዊ መቼታቸው እንዲሁም በአርተፊሻል መቼት በመጠቀም መረጃው ተሰብስቧል። ቃለ መጠየቅንና ምልከታን እንዲሁም የአጠናን ዘዴውን ትንተናና ገለፃ ናቸው። በዚህም መሰረት ከመስክ የተሰበሰቡት ቀዳማይ መረጃዎች እና ከቤተመፃህፍት የተገኙት ካልአይ መረጃዎች ላይ ትንተናና ገለፃ ተሰጥቷል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

### 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

ይህንን ጥናት በማድረግ ሂደት ውስጥ ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ። ከመስክም ሆነ ከቤተመፃህፍት መረጃ በማሰባሰብ ሂደት ላይ ለጥናቱ ተገቢ የሆኑ፣ ስለ ብሔረሰቡ ባህል በቂ እውቀት ያላቸው መረጃ አቀባዮችን እንደተፈለገውና እንደታቀደው አለማግኘቱ፣ ለጥናቱ አጋዥ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ወቅታዊና ተገቢ መፃህፍትና የህትመት ውጤቶችን በተፈለገው ጊዜ ለማግኘት አለመቻል እና አንዳንዶቹም ጭርሱን አለመገኘታቸው ተቀዳሚዎቹ ችግሮች ነበሩ። የብሔረሰቡን ቋንቋ አካባቢውንና ባህሉንም ያለማወቅ ሌላው ተጠቃሽ ችግር ነበር።

ይሁን እንጂ እነዚህ ችግሮች ሊገጥሙ እንደሚችሉ አስቀድሞ የታሰበባቸው ስለነበሩ አንደኛ ስለባህሉ በቂ እውቀት ያላቸውን የብሔረሰቡን አባላት አጥኚው አስቀድሞ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች አግኝቶ በቂ አቅጣጫ አመላካች ሀሳቦችን ይዞ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም እንደራሳቸው ወገን የተቀበሉት ቤተሰቦችን ማግኘት ችሎ ስለነበረ ወደባህሉና ወደ ማህበረሰቡ ለመቅረብ ብዙም አልተቸገረም። ከምባቶች ሰውን የመቀበል ችሎታቸው ልዩ ነው። በመሆኑም የጥናቱን ሂደት ቀና አድርገውለታል።



ምስል 1 ... ታሪካዊው የአምበሪቾ ተራራ ከርቀት ሲታይ

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ስለ ከምባታ መልክአ ምድራዊና ታሪካዊ ገጽታ

### 2.1. የከምባታ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ .

ከምባታ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ከነበሩት 14 ጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ አንዱ በነበረው በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ስር ተመድቦ የሚገኝ ነበር። በደርግ ዘመነ መንግስት ደግሞ የሸዋ ጠቅላይ ግዛት በአራት ሲከፈል፣ ከምባታ በደቡብ ሸዋ ስር እንዲመደብ ተደርጐ ነበር። አሁን በሥልጣን ላይ በሚገኘው በኢሕአዴግ መንግሥት ደግሞ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር በዞን ደረጃ ተመድቦ ይገኛል።

የከምባታ ጠምባሮ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር ከተዋቀሩት 13 ዞኖችና 8 ልዩ ወረዳዎች ውስጥ አንዱ ነው። በውስጡም ከምባታ፣ ጠምባሮ፣ ደንጋና ሌሎችም ብሔረሰቦች ይገኙበታል። ከምባታን በስተሰሜን ሀዲያ፣ በስተደቡብ ሀዲያና ወላይታ፣ በስተምሥራቅ የአላባ ልዩ ወረዳ፣ በምዕራብ የኦሞ ወንዝ ያዋስኑታል። በዚህ ዞን ስርም የቀዲዳ ጋሜላ፣ የቃጫ ቢራ፣ የአንገጫና የኦሞ ሸለቆ ወረዳዎች ይገኛሉ።

ከምባታን ከአዋሳኞቹ ሕዝቦች የሚለዩት ወንዞችና ሸለቆዎች ሲሆኑ እነዚህም በደቡብ ምዕራብ የኦሞ እና የጊቤ ወንዞች፣ በምስራቅ የብላቴ ወይም የሆራ ወንዞችና ሸለቆዎች ሲሆኑ እንደመለያ ወሰን ሆነው ያገለግላሉ። (Braukamper, 1983, 4). ከእነዚህ ውጪ ይህን ያህል የጐሉ ሌሎች ወንዞች በዞኑ ባይገኙም በደቡቡ ምዕራብ የሚገኘው የአጆራ ፏፏቴ ግን በቱሪስት መስህብነቱና በማራኪነቱ ሊጠቀስ ይችላል።

በጋና ክረምት ሁለቱ ዋነኛ የከምባታ ወቅቶች ሲሆኑ በጋው ፀሃያማ ክረምቱም ዝናባማ ናቸው። የክረምቱ ወራት ከሰኔ እስከ መስከረም ይዘልቃል። ይሁን እንጂ ተፈጥሮ በፈቀደው መጠን ወቅቱ መርዘም ወይም ማጠሩ፣ ወይም መለዋወጡ አልቀረም።

ዞኑ ከደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ከተማ አዋሣ በ125 ኪ.ሜ፣ ከአዲስ አበባ ደግሞ በ350 ኪ.ሜ በስተደቡብ የሚገኝ ሲሆን፣ ከባህር ወለል በላይ ከ800-3028 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። የቆዳ ስፋቱ 1,434.44 ኪ.ሜ ስኩዌር ነው። በውስጡ

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

የሰፈረው ሕዝብ ብዛትም 800,000 እንደሆነ ይገመታል። የሕዝብ ጥግግቱም[1] 493 ሰዎች በካሬ ኪሎ ሜትር ነው።[2] የመልክዓ ምድር አቀማመጡ 56.5% ወጣ ገባ፣ 22.25% ሜዳማ፣ 21.25% ተራራማ ነው። የአየር ንበረቱም ወይና ደጋ 70.75%፣ ደጋ 22.25% እና ቆላማ 7% ይታይበታል።[3] (አምበሪቾ፣ 1998፣ 25)

የከምባታ ጠንባሮ ዞን ነዋሪ ህዝብ የኑሮ መሠረቱ በዋነኛነት እርሻ፣ እንስሳት እርባታ፣ ንብ እርባታ፣ እደ ጥበብና ንግድ ነው። ዋና ዋና ምርቶቹም እንሰት፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ሽንብራ፣ አጃ ናቸው። ከእነዚህ ምርቶች በተጨማሪም አትክልትና ፍራፍሬ፣ ዝንጅብልና ቡና በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጪ ገበያ ጭምር ያቀርባሉ።

የከምባታ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ

| | ወረዳዎች | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቀዲዳ ጋሜላ | ቃጫ ቢራ | አንጋጫ | ጠቅላላ (አማካይ) |
| የቦታው ስፋት /በኪ..ሜ²/ | 317.77 | 324.4 | 398.22 | 1040.39 |
| የህዝብ ብዛት /በኪ..ሜ²/ | 499.4 | 412.6 | 436.6 | 449.5 |
| ከፍታ /በኪ..ሜ²/ | 1700 — 3028 | 1600-2500 | 1800-3058 | 1600-3058 |

የጂኦፊዚካል ሁኔታ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተራራዎች (%) | 10 | 7 | 20 | 12.33 |
| ሜዳማ መሬት (%) | 45 | 69 | 20 | 44.66 |
| ኮረብታማ (%) | 45 | 24 | 60 | 43 |

የአየር ሁኔታ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቆላ(%) | - | 3 | 10 | 4.33 |
| ወይና ደጋ (%) | 93 | 71 | 50 | 70.13 |
| ደጋ (%) | 7 | 26 | 40 | 24.33 |
| የዝናብ መጠን በዓመት | 1275mm | 1175 mm | 950 mm | 1133.3 mm |
| የአየር ሙቀት (0c) | 18.28 | 15.22 | 20.28 | 15.28 |

ሠንጠረዥ 1- ምንጭ በላቸው፣ 2001[4]

---

[1] የእንግሊዝኛው 'Ratio' ለመተካት የገባ ቃል ነው።
[2] የፍሬህይወት ጥናት ይህንን አስመልክቶ የዞኑን ፕላንንና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ጠቅሶ 449.5 ህዝብ በኪሎ ሜትር ካሬ እንደሆነ ይጠቅሳል።
[3] አምበሪቾ መጽሔት የዞኑ ባህልና ማስታወቂያ መምሪያ በአመት አንድ ጊዜ የሚያዘጋጀው መጽሔት ነው።
[4] የዚህ መግለጫ ዋነኛው የመረጃ ምንጭ የከምባታና ጠንባሮ ዞን ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ዱራሜ 1991 ነው። ይህንን መረጃ በላቸው 2001 እና ፍሬህይወት 1997 ተጠቅመውበታል። በዚህ ጥናትም የበላቸውን ወደ አማርኛ በመመለስ እንዳለ ተወስዷል።

ADDIS ABABA U
ILS LIBRA

## 2.2 የከምባታ ታሪካዊ ገጽታ

ከምባታ በምሥራቅ ኩሻዊ የዘር ሀረግ የሚመደብ ነው፡፡ የከምባታን ታሪክ ያጠኑ ምሑራን ሁሉ በአብዛኛው ጥናታቸውን የመሠረቱት በቃል ታሪክ ላይ ነው፡፡ በቃል መሰረትም የከምባታ ጥንተ ታሪክ፣ የጐሳዎቹን ስረ መሰረት፣ የአንዳንድ ታሪካዊ ክስተቶችንና ገጠመኞችንም ዝርዝር ሁሉ የያዘ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ቃላዊ ታሪኩ በማመዘኑ ምክንያት ስለ ከምባታ ማህበረሰብ በቂ የሆነ ታሪካዊ መረጃ ለማቅረብ ያዳግታል፡፡ ስለ አንዳንድ ክስተቶችና ስለ ልዩ ልዩ ነገሥትም የአገዛዝ ዘመን የተጨበጡና እርግጠኛ የሆኑ ወቅቶችን ማስቀመጥ ቀላል አይደለም፡፡ ለምሳሌ፣ የከምባታ የመጀመሪያው መሪ ነው ስለሚባለው ስለ ራስ ሃመልማል አዋቂዎች የሚሰጧቸው መረጃዎች የተለያዩ ለመሆናቸው አንድ አስረጅ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ተስፋዬ ሀቢሶ እንደሚለው ‹‹የኦዮታ ነገሥትን ታሪክ ብንመለከት የኦዮታን ስርወ መንግስት የመሰረተውና ለ60 ዓመታት የነገሰው ሃመልማል ነው፡፡›› (1552-1612)[5] Braukamper ደግሞ ሃመልማል የነገሰው ከ1568-1620 ነው ይላል፡፡ ሁለቱን ስናነፃፅራቸው፣ ሃመልማል የሞተበትን ጊዜ አስመልክቶ ተስፋዬ በኢትዮጵያውያኑ የዘመን ስሌት ባስቀመጠው 1612 ላይ 8 ዓመት ሲጨመር ሁለቱ ተመሳሳይ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወደ ስልጣን የመጣበትን ዘመን አስመልክቶ ግን ተስፋዬ በሚለው 1552 ላይ 8 ዓመት ቢጨመርበት Braukamper ከሚለው 1568 ጋር አይመሳሰልም፡፡ እንዲህ አይነቱ ግራ መጋባት የተከተለው ሁለቱም በፅሁፍ በሰፈረ ታሪካዊ መረጃ ላይ ሳይሆን በቃል ታሪክ ላይ በመመስረታቸው ይመስላል፡፡ እንዲህ አይነቶቹ ግራ መጋባቶች የልዩ ልዩ ነገስትን የሥልጣን ዘመን እርግጠኛ ጊዜ ለማመልከት አስቸጋሪ ያደርጉታል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ በከምባታ ላይ ጥናት ያደረጉ በርካታ ምሑራን የሚስማሙበት የመጀመሪያው የከምባታ ገዢ ሃመልማል እንደሆነ ነው፡፡ ብዙዎቹ እንደሚያምኑበትም ሃመልማል የመጣው ከሰሜን ኢትዮጵያ ምንአልባትም ከጐንደር አካባቢ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በእርግጠኝነት ለመናገር ግን አዳጋች ነው፡፡

አስቀድሞ ለመግለፅ እንደተሞከረው ከምባታ በኦሞ እና በብላቴ ወንዞች መካከል የሚገኝ ሰፊ ክልል ነው፡፡ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦችም ይገኙባቸዋል፡፡ ከምባታ፣ ጠንባሮ፣ ደንጋ፣

[5] ተስፋዬ ሀቢሶ፣ 1986፣ 99

ADDIS ABABA UNIVE
ILS LIBRAR

ዱበም፣ ሎካ፣ ሶሮ፣ ሌሞ፣ በደዊቾ፣ ሻሺጐ፣ ኤኔር፣ ሜስ ሜሶ፣ እንደጋኝ፣ አዝነት፣ በርበሬ፣ ሲልጤ፣ ውል ባረግ፣ እና አላባ ይጠቀሳሉ።

ተስፋዬ ሀቢሶ የከምባታን ነገሥት በቅደም ተከተል ማስፈር እንደሞከረው እና ለዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አቶ ኤርሲዶ ሚኰሮ ያረጋገጡት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።[6]

የከምባታ ነገስት ዝርዝር

| ነገሥት | | የንግሥ ዘመን |
|---|---|---|
| 1 | ሃመልማል | 1552-1612 |
| 2 | ደመላሽ /ደሜ/ | 1612-1647 |
| 3 | አየለ /አኖ/ | 1647-1682 |
| 4 | ባላ | 1682-1715 |
| 5 | ከተማ | 1715-1750 |
| 6 | ዲልቦ /ዲላባ/ | 1750-1755 |
| 7 | ሃደሎ | 1755-1758 |
| 8 | ጐንጀቦ | 1763-1768 |
| 9 | ዋቆ | 1768-1803 |
| 10 | ደጐዬ | 1803-1835 |
| 11 | ዲልበቶ | 1835-1885 |
| | ባላባቶች | ያስተዳደሩበት ዘመን |
| 12 | አጋጐ | 1855-1888 |
| 13 | ሞሊሦ | 1888-1912 |
| 14 | በርገኖ | 1912-1939 |
| 15 | አኒዮ | 1939-1966 (የአብዮት ወቅት) |

ሠንጠረዥ 2- የከምባታ ነገሥት፣ ምንጩ ተስፋዬ ሀቢሶ፣ 1983፣ 102

ከምባታ ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ከፈለሱ ጐሣዎች የተዋሀደ ህዝብ ነው። የእነዚህ ጐሳዎች ትክክለኛ ቁጥር ግን አይታወቅም። ለምሳሌ ተስፋዬ ሃቢሶ (1983) 140

---

[6] ተስፋዬ ሀቢሶ፣ 1983፣ 106

በከምባታ ብሔረሰብ ውስጥ የሚገኙትን ጐሣዎች በመወሰን እርግጠኛውን ቁጥር ለማስቀመጥ እንደሚያዳግት የምሑራኑ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ Singer, 26 ናቸው ሲል Braukamper, ደግሞ 81 እንደሆኑ በስም ዘርዝሯቸዋል፡፡[7] ከነዚህ በተጨማሪም (በላቸው፣ 2001) ከወርቁ ጊጂባ አገኘኋቸው ያላቸውንና Singer, 1977፣ Braukamper, 1983, በተስፋዬና በሌሎችም ያልተካተቱ ናቸው የሚላቸውን 98 ጐሣዎች ዘርዝር አቅርቧል፡፡[8]

በአጠቃላይ ያሉትን መረጃዎችና በሠንጠረዥ በዝርዝር የቀረቡትን መዘርዝሮች በመመልከት ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ወደ ከምባታ የፈለሱት ጐሣዎችን በአራት መመደብ የሚቻል ይመስላል፡፡

1. ሴማዊ ቡድኖች፣ እነዚህም ከሰሜን ኢትዮጵያ የፈለሱት የፖለቲካና የኢኮኖሚውን ከፍተኛ ስፍራ ይዘው የነበሩ
2. ኦሞአዊ ቡድኖች
3. ምስራቅ ኩሻዊ እና
4. ፋጋዎች ናቸው፡፡

ከምባታ የበዙ ጐሣዎች ውሁድ ነው፡፡ በእርግጥ በከምባታ የሚገኙት ጐሣዎች እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑና ከዚህ ሊበልጡም እንደሚችሉ የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ አጥኝዎችን ስራዎች በመጥቀስ አስቀድሞ ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡
ስለዚህ የከምባታን ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እናጥና ሲባል ይብዛም ይነስም ሰፊና ጥልቅ የሆነ የብሔር ብሔረሰቦች እና ከልዩ ልዩ ስፍራዎች በመምጣት ተቀላቅለው ከምባታነትን ተቀብለው የሚኖሩትን ጐሣዎችም ጭምር ለመሆኑ ይህ ዝርዝር ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የዚህ ጐሣ ነው፣ ያ ደግሞ የዚያኛው ጐሣ ነው ብሎ ለመለየት ምን ያህል አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ከላይ በስፋት የቀረቡት መልክዓ ምድራዊና ታሪካዊ ገጽታዎች ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡
የዚህ ውሁድ ህዝብ ባህሉ፣ እምነቱ፣ አስተሳሰቡና ትውን ጥበባቱም ቢሆኑ ከዚህ የመዋሀድ ባህሪ ሊያመልጡ አይችሉም፡፡ ይብዛም ይነስም የዚህ ነፀብራቅ ናቸውና፡፡

---

[7] ፍሬህይወት 1997፣ 35 ይህንን ሲጠቅስ ሲንገር 33 ብራው ካምፐር ደግሞ 80 ናቸው ብሏል ይላል፡፡ የሁለቱም ጥናቶች ግን ይህንን አያሳዩም፡፡
[8] በላቸው፣ 2001፣ 142

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. ክለሣ ድርሳን

### 3.1 ፎክሎርና የአጠናኑ ትውሮች

በምሁራን የተደረጉ ጥናቶች እንደሚመሰክሩት ፎክሎርን አስመልክተው የተደረጉት ጥናቶች ከጊዜ ወደጊዜ እየተለወጡ ነው የመጡት:: ቀደም ባለው ዘመን የነበሩት ምሁራን ፎክሎር፣ በአጠቃላይ ደግሞ ባህል የሚያረጅ፣ የሚከስምና ጨርሶ የሚጠፉ እንደሆነ አድርገው ያምኑ የነበረ ሲሆን አሁን በተደረሰበት ደረጃ ግን ትርጉም የሚሰጥ ሂደት እንዳለው እየገለጹ ነው:: የማህበረሰብ የጋራ ሀብት፣ የማንነት መገለጫ እንደሆነም እየተወሳ ይገኛል::

/William John Thoms/ ፎክሎር የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በ1846 (እ.ኤ.አ) ሲያስተዋውቅ የቃሉ ምንጭ የሚከተለው ነበር:: "folk" የሚለው "folc" አንድ አይነት እሴት ያላቸው የሰዎች ቡድን ነው ከሚለውና "lore" ደግሞ "lar" አስተሳሰብ የሚል እንደ ነበረ፣ ይህንን የተጠቀመውም በእንግሊዝ የተለመዱትን popular antiquities ‹‹ህዝባዊ ቅሪቶች›› የሚለውን ለመተካት መሆኑን ይጠቀሳሉ (Dundes, 1965):: ይህ ስያሜ በዚህ መልኩ ከመታወቁ በፊትም ቢሆን "oral traditions" (from 1777) "traditional lore, "popular traditions" በሚሉት ስያሜዎች በእንግሊዝ ይታወቁ ነበር:: ይህንኑ ፅንሰ ሀሳብ ፈረንሳዮቹ "traditions populaires" ጀርመኖች "Volks konde" እና "Volks leben" በሚሉት ከ1806 ጀምሮ ይጠሩት እንደነበር (Dundes,1965) በመግለፅ ጽፏል::

የቀደሙት የፎክሎር አጥኚዎች ትኩረታቸው የነበረውም ዘፈኖችን እና ፎክቴሎችን በመሰብሰብ ያለፈውን ዘመን ተረድቶ፣ መጪውን ዘመን ደግሞ ለመቅረፅ እንደሚያገለግል ነበር (Dorson, 1972, 12-13)::

ላለፉት ከአንድ መቶ ሃምሳ አመታት ላላነሱ ጊዜያት አንስቶ ስለፎክሎር የተለያዩ ብየኔዎች* (definitions) ተሰጥተዋል:: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህልም የሚከተሉት ቀርበዋል::

- ፎክሎር በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚደረግ ጥበባዊ ተግባቦት ነው artistic communication in small groups. (Ben-Amos, 1972)::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

* ፎክሎር ማለት በራሱ ዓውድ ውስጥ የሰዎችን ፈጠራ የምናጠናበት ነው The study of human creativity in its own context. (Glassie, 1993)። Bauman ደግሞ ፎክሎርን ከክወና፣ ከማህበራዊ እና ከተግባቦት ጋር አያይዞ ይመለከተዋል። ይህ በሰፊው ቀርቧል።

> *ፎክሎርን እንደተግባራዊ እንቅስቃሴ እመለከተዋለሁ። በዚህም ትኩረቱ ፎክሎር በትወና አማካይነት እንድሚተገበር፣ ሀልውናውም በህዝቦች በባህሉና ባህሉ በሚፈጥረው ተግባቦት ላይ ነው። ይህም ፎክሎር የሚኖረውን ማህበራዊ መሰረት፣ ማህበረሰባዊ ግንኙነቶችና ተግባቦታዊ ተራክቦን ያመለክታል። (Bauman, 1984, 16)*

ከእነዚህና ከሌሎችም በርካታ ብያኔዎች አንፃር ሲበየን የኖረው ፎክሎር የህዝብ ሀብትነቱ ባያከራክርም በሚያነሳቸው ጥሬ ነገሮችና በጽንሰ ሀሳቡ ረገድም ብዙም መግባባት የተደረሰበት አይመስልም። አንዳንዴም ከባህል ጋር የሚገናኙበትን ለመለየት አዳጋች የሚሆንበት አጋጣሚ እንዳለ ሳይጠቆም አልቀረም። ለዚህ የሚከተለው አስረጅ ነው።

> *የሚሉትን ውሳኔፎክሎርን በቀላሉና ማንኛውም ሰው እንዲረዳው ፎክ እና ሎር መስጠት ተገቢ ነው። ፎክ የሚለው ቃል አንድ በጋራ የሚያስተሳስራቸው ነገር ያላቸውን የሰዎችን ስብስብ ያመለክታል። የሚያገናኛቸው ነገር... የጋራ ስራ፣ ቋንቋ ወይም ሃይማኖት... ይሁን ቁምነገሩ የኔ የሚሉት ባህል ያላቸው መሆኑ ነው። (Dundes,1965, 32)*

ፎክሎር የሚለው ቃል የገላጭነት ባህርይ እንዳለው፣ በገፅ ለገፅ ተራክቦ አማካይነት በልምድ የምንማረው፣ የምናስተምረው ወይም የምንገልፀው ነገር እንደሆነና የሚታወቅ ቅድመ ታሪክ ያለው፣ በጊዜና በቦታም ሳይገታ የሚተላለፍ እውቀት፣ አስተሳሰብ፣ እምነትና የስሜታችን መግለጫ እንደሆነም ይገልፃል።

የፎክሎር ብያኔ እንዲህ ሊሰፋ የቻለው የፎክሎር አዋቂዎቹ ፎክሎርን ከተለያየ አቅጣጫ በማየታቸው ነው። የተወሰኑት ከስነ ቃል አኳያ፣ ቃላዊ ጥበብነቱን በማጉላት፣ ከፊሎቹ ከክዋኔው አኳያ ዐውዱን በማግዘፍ፣ ቀሪዎቹ በማህበራዊ ስርዓቱ፣ በልማዱ በዘፈኑ ወዘተ. ላይ በማተኮራቸው እንደሆነ ይገልጹታል (ፈቃደ፣ 1991)።

ፈቃደ ተግባራዊ ብያኔ ለመስጠት በሞከረበት ወቅት ‹‹... ባጭሩ ፎክሎር የሰዎች መንፈሳዊና /spiritual/ ቁሳዊ (material) ባህል (culture) ነው። የጥናት ወይም የሙያ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መስኩም በዚሁ ቃል ይጠራል፤ ይላል።(ፈቃደ፣ 1991፣ 16)። ተግባራዊ ብያኔውንም የሚያጠቃልለው የሚከተለውን ገልፆ ነው። ‹‹… በድንጋጌ መሰል ነገር ለመደምደም ያህል፣ ‹‹ፎክሎር›› የሚለው ቃል፣ ሥነ-ቃልን ቁሳዊ ባህልን፣ ማህበረሰባዊ ልማድን እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበቦችን ያካተተውን ቅርስ እና፣ እነዚህን ቅርሶችም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠናው የሙያ መስክ ይገለፃል (ፈቃደ፣ 1991፣ 15)።

ይህ ጥናት በተለይ አተኩሮ ለማየት የሚሞክረው ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱን እንደመሆኑ መጠን ለዚህ እንደመንደርደሪያ ሊረዱ የሚችሉትን ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ደግሞ መመልከቱ ተገቢ ነው። አስቀድሞ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በዋነኛነት የሚያተኩሩት በሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ዳንስ፣ ተረክ ትረካ* እና ድራማ ላይ ነው። እነዚህ ነጥቦች በሙሉ ከትወና ጋር በእጅጉ የተቆራኙ የጥበብ መስኮች ናቸው። ከትወና ጋር የተገናኙ እንደመሆናቸውም መጠን ለተፈጥሮ ይበልጥ የቀረቡ ናቸው።

ትወናን አስመልክተው የተሰጡ በርካታ ንድፈ ሃሳቦች አሉ። እነዚህም ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተቃኙ ናቸው። የአንዳንዶቹ የትወና ንድፈ ሀሳብ ትወናው የተከሰተበትን አጋጣሚና የአተዋወኑን ጥበባዊነት ደረጃ ይመለከታል። ይኼ አይነቱ አመለካከት የውበት ነገር ግድ የሚለው ነው። ከትወናው ውስጥም ትወናው የቀረበበትን ቋንቋ ግልፅነት፣ የንግግሩን ሂደትና እና የፀዋትዎቹን ስንስል በትኩረት ይመለከታል። በዚህ አይነቱ አተያይ ጥናቱ መደረግ ያለበት ከባህሉ፣ ከቋንቋው በወጡ ሰዎች ነው። ስለሆነም ውስጠ አዋቂ አጥኚ ያስፈልገዋል። በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሠረት ከትወናው አስቀድመው የተሰበሰቡ ጥሬ ነገሮች በሙሉ ጥበብ አልባ እንደ ሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ።

ማንኛውም ትወና በተዋኙ ብቃት ላይ የሚመሰረት ነው። በሚከሰተው እያንዳንዱ ክስተት ላይ ተዋኙ ሁኔታዎችን እየተመለከተ የመለዋወጥ፣ ሃላፊነት አለበት። እነዚህ ሁኔታዎችም መቼቱ፣ ታዳሚው፣ እና ማህበረሰቡን እየተመለከተ እንዲቀበሉ ትወናውን የማመቻቸት ኃላፊነቱን የሚያመለክቱ ናቸው። ፎክሎር ትዕምርታዊ እንደመሆኑ፣ ከባህል ጋር እንደመታሰሩ፣ ከተግባር ጋር የተያያዘ እና የሰውን ባህርይ እንደማንፀባረቁ መጠን እነዚህን ነጥቦች በትኩረት ማየት እንደሚያስፈልግ *Bauman* እንደሚከተለው ገልፆታል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

*የፎክሎር ቀዳማዊ ሕልውና በሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ሲመሰረት ስረመሰረቱም ማህበራዊና ባህላዊ ሕይወት ናቸው:: የስነቃል ጥሬ ነገሮች አድርገን የምንመለከታቸውም የሰው ልጅ ጥልቅ ባህሪያት ናቸው:: የእኔ ትኩረትም ስነቃል፣ ግለሰብን በጥልቀት ለመረዳት፣ ግለሰቡን የቀረጹትንና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ምን አይነት ፀባይ ማሳየት እንዳለበት ያደረጉት ማህበራዊ፣ ባህላዊና ስረመሰረታዊ ሁኔታዎችን ማጤኛ እንደሆነ ነው:: (Bauman, 1986,2)*

ትዋኔን በአግባቡ ለመረዳት አውዱን መረዳት የግድ ነው:: በተረክ ትረካ፣ በዳንስ፣ በሙዚቃም ሆነ በሌላው ፀዋትው ከዐውዱ የሚገኘው መረጃ ትዋኔውን ለመረዳት ወሳኝነት አለው:: « ከዐውዱ የተፋታ ትዋኔ፣ የተረክ ገፀንባብም ሆነ የታተመ ጽሑፍ ከስጋ እንደ ተለየ አጥንት የሚቆጠር ነው»(Dorson,1986):: ብዙዎቹ የፎክሎር ምሑራንም ትወና ሲጠና ለዐውዱ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ያሳስባሉ:: በእርግጥ አንድ አጥኚ የሰበሰበው አውዳዊ መረጃ ብዛት ስለትዋኔው ለመረዳት አጋዥ ነው:: ምክንያቱም ባህልን፣ ባህል የፈጠረውን ሰው፣ ሰው የፈጠረውን ውስጣዊ ስሜት፣ እናም ስሜቱ የተገለፀበትን መንገድ በውሉ ለመረዳት ዐውዱን በቦታው ተገኝቶ መሰብሰቡ ቀላል ግምት ሊሰጠው አይገባም:: ስለ አንድ ክስተት፣ ክስተቱ ስለተፈጠረበት አጋጣሚ፣ አጋጣሚው የፈጠራቸውን ሁኔታዎች ወዘተ. መተረክ ይቻል ይሆናል:: አንድን ማህበረሰብ፣ ማህበረሰቡ የፈጠረውንም ማህበራዊ መዋቅር፣ የኢኮኖሚ መዋቅር፣ መግለፅም ይቻል ይሆናል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሁኔታዎች ምን ፍቺ እንደሚሰጡ፣ በሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ የሚያሳድሩትን ጫናና ጫናውም የፈጠረውን ውስጣዊ ስሜት ሀዘን፣ ጭንቀት፣ ሽብር፣ ፍርሃት ወዘተ. ከነዐውዱ፣ ትወናውንም ከነ ዐውዱ ካላቀረቡት በአግባብ ለመረዳት ሳያዳግት አይቀርም::

ስነ ሰብአዊው /Anthropologic/ የትወና አጠናን አቅጣጫ ደግሞ ትወና የሰውን ሁለንተናና ባህርይ የመግለጫ መንገድ አድርጎ ይወስደዋል:: ከዚህ የአጠናን አቅጣጫ ተጠቃሽ የሆነው Richard Schechner ነው::

እንደ እሡ ከሆነ አርስቶትል የተጠቀመበትን (mimetic) አስመስሎ መተወን የሚለውን በመውሰድ ትወና ማለት አስመስሎ መጫወት ማለት ነው:: *Tragedy is the imitation* of an action magnitude. (Aristotle 1961: 61 in Schechner 1988: 37) በእርግጥ ትወና አንድን ድርጊት ኮርጆ፣ አስመስሎ መጫወት ብቻ ነው ወይ? ብሎ መጠየቅ ይቻላል:: ሳይኮርጁስ ፈጥሮ፣ መጫወት አይቻልም ወይ? ብሎም መከራከር ይቻላል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ለምን ቢሉ በሀገራችን በአንድ አጋጣሚ ላይ በቦታው ድንገት ተገኝተው፣ በቦታው ላይ እዚያው ፈጥረው የሚተውኑ ተዋኞች ይገኛሉና ነው፡፡ ትወና በባህሉ ማዕቀፍ ውስጥ ተቀባይነት ያለው ተግባር እና የጋራ ስምምነትን የሚጠይቅ ትዕምርትም ነው፡፡ ሂደትም ነው፡፡ በአንድ ባህል ውስጥ የሚገኙ ጥሬ ነገሮች ከስሜት እንዲዋሃዱ የሚያደርጓቸውን ጥበብ ተላብሰው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚለውጡበት ነው፤ ትወና፡፡ ለዚህ ነው የሰዎችን ተልዕኮም የማጥኛ መሠረታዊ ነገሮች ተደርገው የሚቆጠሩት፡፡ የትወና ጥበባቱም በተከታትይ ምዘና፣ እና አስተያየቶች ዘወትር የሚዳብሩ፣ በጋራ የሚፈጠሩ፣ ከተመልካች ከታዳሚ፣ ከአድማጭ ጋር የጋራ መግባቢያ መንገዶች ናቸው፡፡ ምሁራኑ እንደሚሉት በአካባቢያዊ ሁኔታዎች፣ ማህበራዊና ባህላዊ ዐውዶች ያሏቸው፣ ዘወትር የሚከሰቱ ነገሮች ናቸው፡፡ Bauman ይህንን እንደሚከተለው ነው የገለፀው፡፡

> *የትወና ዋነኛ ነገር የሚያርፈው በተግባቦታዊ ነገሮች፣ በግለሰቦች ብቃትና በተሳታፊዎች ሚና ላይ ሲሆን ይህም በወቅቱ በሚከሰቱ አውዳዊ ነገሮች ላይ ይመሠረታል፡፡ በዚህ ውስጥ አስፈላጊዎቹ ነገሮች ትወናውን ለመተወን የትወናው ፀዋትዎች፣ ገቢሮች፣ ክስተቶች፣ የአተዋወኑ ደንቦችና በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸው የአተዋወን ስርዓቶች ናቸው፡፡ (Bauman, 1991, 15)*

አንድ ትወና በሚተወንበት ወቅት ከተዋናዩ የሚጠበቁ ክሂሎችም አሉ፡፡ ተዋናዩ ሲናገር፣ ሲተርክ፣ ሲጫወት፣ ሲዘፍን፣ ወይንም አካላዊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ እንዲያሳይ የሚጠበቅበት ልዩ ችሎታ አለ፡፡ ይህ ነጥብ ነው አንዱን ተዋኝ - ተዋኝ ነው ወይም አይደለም፣ ብቁ ነው ወይም ብቁ አይደለም በማለት የተቀባይነት ደረጃውን የሚወስነው፡፡ ትወናውንም ውጤታማ ነበር፣ ውጤታማ አልነበረም ተብሎ የሚመዘነውም በክሂሉ መጠን ነው፡፡ ተዋኙ ተገቢ ክህሎት ኖሮት ካልተወነ አድማጩ ወይንም ተመልካቹ ተቀባይነት ይነሳዋል፡፡ በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ተቀባይነት የሚያጡት ከተዋኙ ብቃት ማነስ ብቻ ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡ አንዳንዴ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ይፈጠሩና ትወናው ሊበላሽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የሠርግ ዘፈን እየተዘፈነና እየተጨፈረ ድንገት አንድ የደነበረ በሬ ዘሎ ቢመጣ፣ አንድ የምረጡኝ ንግግር የሚያደርግ ፖለቲከኛ ድንገት መብራት ቢቋረጥበት፣ አንዲት አስለቃሽ እያዜመችና ደረት እያስደቃች ሳለ ድንገት ሆዷን ቢቆርጣትና ቢያማት … ወዘተ. ትወናው ሊበላሽ ይችላል፡፡ ስለዚህ ለትወና መበላሸት ሁሌም ተዋናዩ ተጠያቂ አይደለም ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከተዋኙ የሚጠበቁትን

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

መሠረታዊ ክሂሎች ተዋኙ የመፈፀም ኃላፊነት እንዳለበት Beeman እንደሚከተለው ዘርዝሯቸዋል፡፡

1. ተዋኙ ምንጊዜም ቢሆን ተግባሩን መፈተሽና መመርመር ይጠበቅበታል፤ እንዲሁም እሱ/እሷ ትወናውን በተገቢው መንገድ ለመወጣት ምን እንደሚያስፈልግ መመርመር አለበት/አለባት፡፡
2. ክወናውን በአግባቡ ለመወጣት አካላዊ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
3. ከዋኙ ምንጊዜም ቢሆን ሁኔታዎችን አገናዝቦ፤ የራሱን ፈጠራ፣ የእሡ የራሱን የተለየ ችሎታ አክሎ ለመተወን መዘጋጀት አለበት፡፡ (Beeman, 1993, 202)

ከዚህ በተጨማሪ ተዋኙ ሊተገብራቸው የሚገቡት ስልቶች አሉ፡፡ 1ኛ ጊዜ /Time/ ተዋኙ ትወናውን በሚፈፅምበት ወቅት ጊዜን የመጠቀም ብቃት ሊኖረው የግድ ነው፡፡ ጊዜን ከሁኔታው ጋር አጣጥሞ መጠቀም ከተዋኙ የሚጠበቅ ችሎታ ነው፡፡ 2ኛ /Charisma/ ግርማ ሞገስ መላበስ- የታዳሚውን አድናቆትና ተቀባይነት ለማግኘት ትኩረታቸውን መሳብ አለበት፡፡ 3ኛ /Focus and concentration/ አትኩሮት፣ በስራው ላይ ሙሉ ትኩረቱን መጣል፤ 4ኛ አዲስነት፣ /Freshness/ ሁሌም አዲስ ነገር ለማቅረብ መጣር አለበት፡፡

በተቃራኒው ትዕምርታዊ የሆኑ ነገሮችን ደግሞ ደጋግሞ ለማለት መሞከርና እርስ በርስ መገፋፋት ከተከሰተ የትወናው መልዕክት ሊበላሽ እንደሚችል መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም ተገቢውን አትኩሮት አለመስጠት፣ በግዴለሽነት ከችሎታ በታች መዘጋጀት /under preparation/ ፣ ከተገቢው በላይ ተጨናንቆ መዘጋጀት /over preparation/፣ አውዱን አዛብቶ መረዳት /Miscalculation of context/ ከተከሰተ ትወናውን ሊያበላሽ፣ ተቀባይነቱንም ሊያጣ እንደሚችል ምሁራኑ ያሳስባሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተዋኙ ታዳሚዎቹ* ምን ያህል እየተከታተሉት እንደሆነ ማጤንና የትወናውን አወራረድም በትክክል እየተጓዘ መሆኑን ቸል ሳይል ማስታወስ ይጠበቅበታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ትወናው ፍሰቱን ለቆ ሊሄድበት ይችላል፡፡ አንዳንዴም ታዳሚዎቹ መስማት (ማየት) ከሚችሉት በላይ ሆኖባቸው፣ ወይም ተሰላችተው እያንጐላጁ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች መከታተል ተገቢ እንደሆነ ምሁራኑ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ይመክራሉ:: ይኼ በትወና ወቅት የሚያጋጥም ወሳኝ ነጥብ በመሆኑ ከዚህ በታች ተገልጿል::

> *ድንዛዜ የሚከሰተው አንድ ታዳሚ የሚመለከተው ትዕይንት አካላዊውንም ሆነ መንፈሳዊ ስሜቶቹን ከመጠን በላይ ወጥረው ሲቆጣጠሩት ነው:: በተለይም ይህ አይነቱ ክስተት የሚያጋጥመው ያልተለመደ፣ አስልቺ እንቅስቃሴ ሲደረግና በታዳሚው ላይ ጉጉት ካላጫረ ነው:: (Beeman, 1986, 202)*

አንድ ተዋኝ ከሌሎች ተዋኞች ጋርም አብሮ የመስራት ችሎታና ፈቃድኝነት ሊኖረው ይገባል:: እርስ በርስ ለመማማር እና ለመተራረም ጥሩ አጋጣሚ ሊያገኝ ይችላል:: በተጨማሪም ከተመልካቾቹ፣ ከአድማጮቹ፣ በአጠቃላይ ከታዳሚው ጋር እነሡን በሚያሳትፍ መልኩ ቢተውን ተመራጭ እንደሆነም ብዙዎቹ ይሞክራሉ:: ትወና ሁለቴ የሚተገበር ነገር እንደሆነም ተዋኙ ልብ እንዲለው ይመከራል (Schechner, 1994):: መለማመድና፣ መዘጋጀት፣ ከዚያም መተግበር:: እንደገናም ይህንኑ መድገም::

አንድ ትወና በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ሊመዘን ይችላል:: ትወናው በአዎንታዊ መልኩ ይታይ ዘንድ ትዕምርታዊ እውነታውን በሚገባ ማቅረብ ይጠበቅበታል:: ከዚህ በተጨማሪም ነፃ፣ ተፈጥሯዊና ያለምንም ውጪያዊ ተፅእኖ መተወኑ (spontaneous)፣ እውነትን ይዞ መገኘቱ (true) ክህሎታዊ /skillful/ መሆኑ፣ እና ውጤታማ /effective/ ሆኖ መገኘቱ ናቸው:: ተቀባይነት ያለውንና ባህሉ ያፀደቀውን እውነታ ይዞ ከተገኘ ተመልካቹ ወይም ታዳሚው ትወናውን በአዎንታዊ መልኩ ሊቀበለው ይችላል:: በአሉታዊ መልኩ የሚታዩት ትወናዎች ደግሞ ቀላል ያልሆኑት እራሱን (ተዋኙን) ብቻ ማዕከል ያደረጉት፣ ክሂል አልባ እና ውጤታማ ያልሆኑት ናቸው::

ታዳሚው በአዎንታዊም ሆነ ትዕምርታዊ በሆነ መልኩ ትወናው እንዲቀጥል፣ በርታ የሚል ማበረታቻ ይሰጣል:: ትወናው እንዲደገምለትም መግለፅም ሆነ ሽልማትና ማበረታቻ መስጠት ምልክቶቹ ናቸው:: አሉታዊ ለሆነ ትዋኔ ደግሞ እልልታው አይሰማም፣ ጭብጨባው አይደመጥም፣ ሳቅና ደስታው በጨፈገገ ፊት ይለወጣል:: ትኩረቱን አይሰጠውም፣ ይደገም ከማለት ይልቅ በፋጨትና በጩኸት ተቃውሞውን ይገልፃል:: ከመሸለም ይልቅ ጀርባውን ሰጥቶ አዳራሹን ለቆ መውጣት ይመርጣል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ስለዚህ ተዋኙ እነዚህን ሁኔታዎች በመመልከት እራሱን ማስተካከል ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡

ባህላዊ ትወናዎች የተለዩ ቅርፆችም አሏቸው፡፡ ለምሳሌ የድራማን አተዋወን ብንመለከት፣ ድራማ የስነፅሁፍ ይዘቶች ያሉት በመሆኑ የሚተርከው ታሪክ አለው፡፡ ይህ ታሪክም አብዛኛውን ጊዜ ከግጭት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴ እና በምልልስ መልክ የሚቀርብ ነው፡፡ በመሆኑም፣ የሚተውኑት ተዋናዮች፣ የሚቀርብላቸው ታዳሚዎች ያሉት በመሆኑ በትወናው የሚሳተፉበት አጋጣሚም ከባህል ባህል ይለያያል፡፡

ሀገረሰባዊ ድራማዎች እንደመድረክ ላይ ድራማዎች ሁሉ ማህበረሰቡን የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ትወና በሀገረሰብ ድራማዎችም ውስጥ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ረገድ የሚስተዋሉት ነጥቦችም የሚከተሉት ናቸው፡፡ ትወናዊ እንቅስቃሴዎች አንድን ማህበረሰብና የእሱን የተቃራኒውንም ማህበረሰብ ገፅታዎች ስለው የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ የሥልጣን የበላይነትና ቀውሶችን፣ ማህበረሰቡ የተጋረጡበትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች፣ መስዋዕት ማቅረብን የመሳሰሉ ነገሮች ይንፀባረቁበታል፡፡ አልፎአልፎም የሀሳባዊውን ዓለምና ሚታዊ (Mythical) የሆኑ ነገሮችም ይታዩበታል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚከናወኑ የማንፃት ስርዓቶች፣ መስዋዕት የማቅረብ ስርዓቶች፣ የመሳሰሉት ትዕምርታዊ በሆነ መልኩ ሲተወኑ እንደሚታዩ Turner ያመለክታል፡፡

> *የማህበራዊ ድራማ ጥንካሬው የሚለካው ልምድን ወይም የተጠራቀመ ልማዶችን ማካተቱ፣ ባህላዊ የአተዋወን ፀዋትዎችን እና ተግባራቸውን መያዙ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ፀዋትው በከፊል የተቀዱ፣ ሂደታዊ ቅርፅ ያላቸው ማህበራዊ ድራማዎች፣ እና በከፊልም ፍቺን የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ (Turner, 1986, 95)*

እነዚህ ሀገረሰባዊ ድራማዎች ይብዛም ይነስም ታዳሚው አካባቢውን የሚያውቅባቸው ወይም ስለ አለም ያለውን አመለካከት የሚቀርፅባቸው፣ ናቸው፡፡ በአመለካከቱ ላይም አክራሪ፣ ወግ አጥባቂ ወይም ለውጥ ፈላጊነትን የሚፈጥሩበት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ድራማዊ አቀራረቡ ማህበራዊ ስርዓትን መቅረጫም ነው፡፡ ሰናይ እና እኩይ ምግባሮችን በምፀት፣ በስላቅ፣ በፌዝም መልክ ያሳያሉ፡፡

ትወና የለዋጭነት ባህርይ ስላለውም ነባሩን ምግባር በአዲስ የመለወጥ፣ የቆየን ማህበራዊ መዋቅር በአዲስ እንዲተካ የማድረግ፣ የተዋኙንም ሚና ቢሆን እንደገና እንደ አዲስ የመቅረፅ ባህርይ አለው፡፡

የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱን አስመልክቶ በአሁኑ ጊዜ የሚሰጡት ንድፈ ሀሳቦች አቀንቃኞቻቸው እንደሚከተሏቸው የአጠናን ስልቶች፣ ሊያጠኑዋቸው እንደመረጡዋቸው የፎክሎር ቅርፆች ይለያያሉ። የቀደሙት አጥኚዎች ፎክሎርን በመሰብሰብ ላይ ሲያተኩሩ፣ ዘመነኞቹ ደግሞ ከዚያ ባሻገር ሄደው ጥናቱ ባለው አውድ እና የማህበረሰቡ ዕለታዊ የኑሮ ዘይቤ አንፃር እየተነተኑ ማሳየቱን ይመርጣሉ። የቀደሙት የፎክሎር ቅርጾች ከመጥፋታቸው በፊት ቀደም ደርሶ በማስቀረቱ ላይ ያተኩሩ ነበር። የአሁኖቹ ደግሞ በፎክሎሮቹ እየተጠቀመባቸው የሚገኘውን ማህበረሰብ፣ መስኩ ድረስ ሄደው በመገናኘት አውዱን ጭምር እያገናዘቡ መተንተኑን ተያይዘውታል፤ ትወና ማህበረሰቡን ይገልፃል ብለው ስለሚያምኑ። ይህን አቅጣጫ አስመልክቶ በመፃፍ ላይ ከሚገኙት ውስጥ Magoulick የምትጠቀስ ሲሆን የእሷ ሀሳብ ከዚህ በታች እንዳለ ቀርቧል።

> *የትወናን ቲዎሪ የሚያጠኑ የፎክሎር ምሁራን ስለሚያጠኑዋቸው ማህበረሰቦች በአንፃራዊ መልኩ የተሟላ አውዳዊ ስዕል ይሰጣሉ። እነዚህ አውዶች የሚተረኩ ተረኮችን ወይም ሌሎች አካላዊ የመግባቢያ ቅርፆችን እንድንረዳቸው ያግዙናል። ፎክሎር፣ ፎክ እና ሎር የሚሉትን እንድሚያካትት ልብ ማለት ይገባል፤ ሁሉም ባህሎች እና ሰብዓዊ ፍጥሮችም ፎክሎርን ይፈጥሩታል። (Magoulick, 2003, 3).*

ስለ ትወና ንድፈ ሃሳቦች የአጠናን ሂደት የበለጠ ውጤታማ የሆነው ዘዴ በተግባር፣ በአካል በመስኩ ላይ በመገኘት ከተጠሪው ማህበረሰብ እውነተኛ የህይወት ተሞክሮ በመቅዳትና በመተንተን እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ። ትወና ለህይወት ትርጉም መስጫ፣ ኪናዊ ቅርጾችን ማስተማሪያ፣ ስለ ሰው ሰብአዊነት ማስገንዘቢያም ጭምር ነው። ለምሳሌ የሀገረሰብ ጥበቡን ለማጥናት በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ በቅድሚያ ራሳቸው ለራሳቸው ማዝናኛ እንደሚተውኗቸው ከመስክ ማረጋገጥ ይቻላል። በሀገረሰባዊ ዘፈኖቹ ራሳቸውንና ታዳሚዎቻቸውን ዘና ለማድረግ ሲተውኑ ማየት ይቻላል።

የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ ፀዋትው እርስበርሳቸው ሊገናኙ እንደሚችሉ ከዚህ በላይ የቀረበው ሀሳብ በበቂ ሊያስረዳ ይችላል። ይሁንና የእያንዳንዳቸውም ሆነ የተናጠል ግባቸው ራስን፣ ተመልካችንና በአጠቃላይም ማህበረሰቡን ለማነቃቂያ፣ ለማስተማሪያ፣ ለማነጫ እንደሚውሉ ከተረዳን ዘንዳ ባሉበት መልኩም ቢጠኑም ብዙም ክፋት የለውም። ትወናው በቃልም ሊቀርብ እንደሚችል Okpewho ቃላዊ ትወና oral performance ከሚለው መገንዘብ ይቻላል። የዚህ አይነቱ ትወና በተዋኙ ዕድሜ፣ በተዋኙ ጥንካሬ፣

በመተወኛው አጋጣሚ (ሞት፣ ሠርግ) በዘፈኑ አይነት፣ በሙዚቃ መሣሪያ የመታጀቡ ያለመታጀቡ፣ በተዋኙ ብቻ በግል መነባንቡ ወይም በቡድን በመሆን መተወኑን ከመሳሰሉ ሁኔታዎች መለየት እንደሚቻል ይገልፃል (Okpewho: 1992: 42)::

በአጠቃላይ ተዋኙ ሌሎች ደጋፊዎቹን (አጫፋሪዎቹን) /Accompanist/ በመያዝ፣ ወይም ለብቻው፣ ታዳሚ ባለበት ወይም በሌለበት (ለምሳሌ እረኛች ዋሽንታቸውን እየነፉ አንድም ታዳሚ በሌለበት ከብቶቻቸውን ፈቅደው ለረጅም ሰዓት እያንጐራጐሩ ሊዝናኑ ይችላሉ:: (Okpewho: 1992: 57) በተጨባጩ ግን ቃላዊ ትዋኔ ታዳሚው ተዋኙን እያደነቀው፣ እያሞገሰው የሚከወን ነው::

### 3.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ጥናት ከሚያነሳው ርዕሰ ነገር ጋር በቀጥታ የተገናኘ ሌላ ጥናት አጥኚውን አልገጠመውም:: ይሁን እንጂ ይህ ጥናት የሚያተኩርበትን ማህበረሰብ አስመልክቶ ከዚህ በፊት የተሰሩ ሥራዎችን መቃኘቱ ተገቢ ስለሆነ እንደሚከተለው ቀርቧል::

እስከአሁን የተደረጉት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኞቹ ከስነቃል ጥናት ያልዘለሉ ናቸው:: ስለከምባታ ብሐረሰብ ባሕልና የትመጣ (origin) የጥናት ጽሑፍ በማቅረብ N.J. Singer (1975, 1977) Braukamper (1983) ይጠቀሳሉ:: Braukamper የብሔረሰቡን እምነትና መሰረት ከታሪክ ጋር እያጣቀሰ በማቅረቡ፣ Singer ደግሞ የከምባታን ህዝብ ለማስተዋወቅ ባደረገው ጥረት ሁለቱ በተለይ ይጠቀሳሉ::

ፈቃደ (1977፣ 1984፣ 2001) ያቀረባቸው መጣጥፎችና የምርምር ስራዎች እንደሚጠቁሙት አብዛኞቹ በፎክሎር የተደረጉት ጥናቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም መምህራን እና ተማሪዎች የቀረቡ ናቸው:: ብዙዎቹም ጽሑፎች ለመጀመሪያ እና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ እንደሆኑ ተጠቅሷል::
ከሌሎች በስነጽሑፍና ፎክሎር ዙሪያ ከተደረጉ ጥናቶችና ከምባቶችን ከተመለከቱት ውስጥ የ(ብርሃኑ ማቲዎስ (1986) “An analysis of Kembatta Proverbs) በኤም.ኤ.ዲግሪ የምርምር ስራ በቀዳሚነት ይጠቀሳል:: ብርሃኑ በዚህ ጥናቱ የከምባታ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብና በይዘትና በቅርፃቸው ላይ ትንታኔ በማድረጉም ሆነ በቀዳሚነቱ እንዲሁም በስራውም ጥልቀት ይጠቀሳል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የከምባታን ፎክሎር የሚመለከቱት በአጠቃላይ አምስት ለቢ.ኤ. ዲግሪ የተደረጉ ጥናቶች አሉ፡፡ ለቢ.ኤ.ዲግሪ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረቡ ሁለት ስነ-ቃል ላይ ያተኮሩ ጽሁፎች፣ በሶሲዮሎጅ ትምህርት ክፍል ደግሞ አራት ለቢ.ኤ.ዲግሪና አንድ ለኤም.ኤ.ዲግሪ የቀረቡ የምርምር ስራዎች ከብሔረሰቡ ሀገረሰባዊ ልማድና ከቤተሰብ ግንኙነት ጋር በተያያዘ የተሰሩ ይገኛሉ፡፡

ተስፋዬ ሀቢሶ በአማርኛ ቋንቋ ‹‹ከምባታና ሀዲያ፣ የአስተዳደር አካባቢና የብሔረሰቦች ታሪክ አንዳንድ ገጽታዎች›› (1986) በሚል ርዕስ ባቀረበው የጥናት ወረቀት በብሔረሰቡ የቃል ታሪክ አዋቂዎች በተጓዦች፣ በሚሲዮናውያንና በተመራማሪዎች … ስለማህበረሰቡ ታሪክ፣ አስተዳደራዊ ሁኔታዎች ለማመልከት መሞከሩ ተጠቃሽ ነው፡፡ እንዲሁም በእንግሊዝኛ ቋንቋ “Some Records of South West Ethiopia and Short History of Kembatta and its People” (1987) ያቀረበው የጥናት ወረቀትም ስለብሔረሰቡ ታሪክ ለማስተዋወቅ ጥረት አድርጓል፡፡

በሲውድንና በጀርመን ቋንቋዎች ተጽፈው ወደ አማርኛ የተመለሱት የGenstedt (2000) ከሃይማኖት ጋር የተያያዘውና የበላቸው ገብረወልድ (2001) ‹‹ለኢኮኖሚያዊ እድገት የማህበረ ባህላዊው መዋቅር ያደረገው አስተዋጽኦ›› ሌሎች ተጠቃሽ ስራዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ጥናቶች ከዚያ ቀደም ብሎ በተሰሩት የSinger(1975)፣ Baukamper (1983) እና ተስፋዬ (1986) ጥናቶች ላይ በመመስረታቸው ከግኝታቸው ውጪ የከምባቶችን ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በተመለከተ የሰጡት መረጃ በቂ ነው ለማለት አይቻልም፡፡
በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁትና በመጻህፍት መልክ ታትመው ከቀረቡት የወልደስላሴ አቡቴ (2000) “Kambatta” እና የያዕቆብ አርሰኖ (2002) “Seera: A Traditional Institution of Kembatta” በተለይ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ጥናታዊ ድርሳናት በብሔረሰቡ አባላት የቀረቡ ዳጉስ ያሉ ስራዎች በመሆናቸው፣ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር በተያያዙ የቀረቡ የምርምር ስራዎች በመሆናቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ወልደስላሴ በጥናቱ በደቡብ ኢትዮጵያ ስለሚገኙ ‹‹አናሳ›› ስለሚባሉ ነገር ግን ከፍተኛ ስራን ስለሚሰሩ የተለያዩ ህዝቦች ባመላከተበት ዳሰሳው የከምባቶችን በመመልከቱ፣ የያዕቆብ ደግሞ ባህላዊ አስተዳደራዊ ስልት ለዘመናዊ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ያለውን ፋይዳ በከምባታ ማህበረሰብ ልምድ በማስተዋወቃቸው ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ከሁሉም ለየት የሚለው ጥናት የቀረበው በፍሬህይወት አድነው በህዳር 1997 የማስተርስ ድግሪ ማሟያ ጽሑፍ ነው። ፍሬህይወት ‹‹ከምባቶመት›› ÷የከምባታ ፎክሎር ይዞታና ለውጥ›› በሚል ርዕስ ባቀረበው ጽሑፍ የከምባታን ሀገረሰባዊ ሃይማኖት፣ ክብረ በዓላትና ጨዋታዎች፣ ልማዶችና ስርዓቶች፣ የከምባቶመት ይዞታና ለውጡን ቃኝቷል። ፍሬህይወት በዚህ ጥናቱ ‹‹ከምባቶመት›› የማድመጥ፣ ባህልን የመጠበቅ፣ የመረጋጋት፣ያለመቸኮልና በቂ መረጃ ይዞ መነሳሳትንና ስራ ወዳድነትን ይገልፃል በማለት ትኩረት የሰጠው ከስነቃሉና ከሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ ይልቅ ለማህበረሰብ ህይወት ልማድና እምነቱ ነው። (ፍሬህይወት፣ 1997)። ይህ ጥናት ደግሞ ትኩረት የሚያደርገው ለሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ ነው።

የሙሉጌታ ጀዋሬ (1998). “A Preliminary Classification and Descriptive Study of Oral Narrative: The Case Study of Dubamo.”Tarika” በእንግሊዝኛ ቋንቋ የዱበሞን የቃል ታሪክ የአቀራረብና የአመዳደብ ጥናት አድርጐ ሲያቀርብ፣ ሙሉጌታ ኢዩኤል (2001) የአንትሮፖሎጂ የምርምር ስራም ‹‹የዱበሞዎች ጎሳዊ ግንኙነቶችና ማህበረ ባህላዊ ለውጥ ሁኔታ ላይ ያተኮረ ነው። ሁለቱም በጥናቶቻቸው ስለ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ የሰጡት መረጃ የለም ማለት የሚያስችል ነው።

ሌሎች በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ የጥናት ጽሑፎች በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለቢ.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ናቸው። እነሱም አምስት ናቸው። የደስታ ገብረሚካኤል (1963) ‹‹የከምባትኛ ተረትና ምሳሌዎች፣ የመኮንን ተሰማ (1970) ‹‹የከምባትኛ እንቆቅልሾች››፣ የደስታ ፀደቀ (1981) ‹‹ኢከምባትኛ ስሞች በከምባታ ማህበረሰብ››፣ የደስታ ሎረንሶ (1982) ‹‹የከምባታ ማህበረሰብ ባለእጆችና ስነቃላቸው›› እና አርቲንግ ደጉ (1995) ‹‹የከምባታ ብሔረሰብ የሰርግ ስርዓትና ግጥሞች›› ናቸው። አርቲንግ በዚህ ፅሑፉ የብሔረሰቡን የሰርግ ወቅት ግጥሞች በመሰብሰብ በመተንተንና በቅርፃቸው ላይ ገለፃ በማድረግ አቅርቧል። ይሁን እንጂ በሰርግ ስርዓቶቻቸው ትወና ረገድ ሰፋ ያለ ገለፃ አላቀረበም። ይሄኛው ጥናት ግን በትወናውና በፋይዳው ላይ ስለሚያተኩር ልዩነት አላቸው። በውጭ ቋንቋዎች የትምህርት ክፍልም በወልደ ስላሴ አቡቴ (1984) “Kembatta Folk Tales” እና የዘለቀ ሰንዳቦ (1995) "The Educational Value of Kembatta Riddles" ሲሆኑ ሁለቱም በስነ-ቃል ላይ ያተኮሩ ናቸው። ከእነዚህ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የጥናት ወረቀቶች መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት ለሆነው ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ጋር በይዘትም ሆነ በቅርፅ የሚመሳሰል አልተገኘም።

ከነዚህ በተጨማሪ በብሔረሰቡ ልማዶችና እምነቶች ላይ የሚያተኩሩ የጥናት ወረቀቶች በሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል ቀርበዋል። እነሱም አራት ሲሆኑ በቅደም ተከተል የሀንዴቦ ኤርገኖ፣ (1982). "*The Family System of the Nationality of Kembata"*፣ የተስፋዬ ሰደኖ፣(1984). *"Mourning and Burial Customs Among the Kembatta*፣ የተከተል አበበ፣ (1985). *"A Study of the Socio Economic Conditions of Fuga* (a low-C*aste Occupational Group) With Particular Reference to Kembatta"* እና የታገሰ ሀሊቦ፣ (1995). "*Indigenous Marriage Practices Among the Kembatta People* of Kachabira Woreda" የሚሉት ናቸው። ከእነዚህ መካከል የተስፋዬ ሰደኖና የታገሰ ሀሊቦ ፅሑፎች ከሐዘንና ከቀብር ስርዓቱ፣ እንዲሁም ከጥንታዊው የጋብቻ ስርዓት አንፃር እንዲሁም ከማህበራዊ ልማዱ ጋር በማነፃፀር የተመለከቱ ናቸው። ከዚህ የተነሳም በሚያነሱት ርዕሰ ነገር ከዚህ ጥናት ጋራ ይመሳሰላሉ። ይሁን እንጂ የትወናውን ይዘትና ማህበራዊ ተግባሩን በጥልቀት ስለማይመለከቱ ይለያያሉ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የምርምር ስራዎች በተጨማሪ በ1970ዎቹ ይወጡ በነበሩት ጋዜጦች ላይ ስለከምባቶች ስነ-ቃል የሚያወሱ ጽሑፎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ በቆጠራ ዮሐንስ (1976) የተዘጋጀው ‹‹የከምባትኛ ስነ-ቃል ጥናት ዘገባ›› ተጠቃሽ ነው።

በአጠቃላይ ሲታይ ከምባታን አስመልክተው የተሰሩት ጥናቶች እነዚህ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ። ለማግኘት ከተቻሉት ውስጥ እና ከዚህ በላይ ከቀረቡት ውስጥ አብዛኞቹ ጥናቶች በስነ-ቃል ላይ ያተኮሩ ናቸው። ጥቂቶቹም፣ ከሀገረሰብ ልማድ፣ ከሀገረሰብ ህይወት፣ ከባህላዊና አስተዳደራዊ ስርዓቶች ወይንም መዋቅሮች አንፃር የተመሰረቱ ሆነው ይታያሉ። እጅግ ጥቂቶቹ ደግሞ ስለብሔረሰቡ የትመጣ የሚናገሩ ናቸው። ሁሉም ጥናቶች ማለት ይቻላል አንደኛ ከምባታን የተመለከቱ በመሆናቸው፣ ሁለተኛ ከተለያየ አቅጣጫም ቢመለከቱት ስለማህበረሰቡ የሚያወሱ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ። ከዚህ ጥናት ጋርም እነዚሁ ጉዳዮች ያመሳስሏቸዋል። ከዚህ ባሻገር በሚከተሉት ነጥቦች እንደሚለያዩ መግለጽ ይቻላል። ይህ ጥናት ከቀደሙት ጥናቶች በሚከተሉት ነጥቦች ይለያል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

- ከፎክሎር ቅርጾች ውስጥ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱን በተለይ አትኩሮ የሚመለከት በመሆኑ፣
- ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ እንዴት፣መቼ፣ በማን፣በምን ሁኔታ (event) እንደሚተወኑ የሚያተኩር መሆኑ፣
- የትውን ጥበባቱ ፀዋትው (genres) ይዘት፣ አንድነትና ልዩነት፣ ማህበረሰቡን የሚለዩባቸውን መንገዶች በመመረመሩ፣
- የትውን ጥበባቱ ማህበራዊ ተግባራት ከማህበረሰቡ እሴቶች አንፃር እንዴት እንደሚተላለፉ፣ እንደሚጠበቁና እንደቀረጹት፣
- ከቃላዊ ይልቅ በተግባራዊ እንቅስቃሴዎቹ ላይ በማተኮሩና የማህበረሰቡን ተራክቦ ለማጥናት መሞከሩ፣
- ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችና ትውን ጥበባቱ የራሳቸውና የእርስ በርስ ተፅእኖዎች ምን እንደሆኑ ለማየት መሞከሩ፣
- የሀገረሰብ ልማዶቹና ስርዓቶችን ከትወና አንፃር ለማሳየት መሞከሩ ናቸው::

ከዚህ በላይ የቀረቡት ነጥቦች እንደሚያስረዱት ይህ ጥናት (Performance-centered Approach) ትወናን ማእከል ያደረገ ጥናት በመሆኑ ከቀደሙት ይለያል:: የጥናቱ ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደሚነሱት ርዕሰ ነገሮች (ለምሳሌ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት) /text-centered Approach/ን የሚጠቀም መሆኑም ጥናቱን ልዩ ያደርገዋል:: እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ሀገረሰባዊ ልማዶችን በተለይም ስርዓቶችን (ወሊድ፣ ሞት) በሚመለከት ምዕራፍ (event-centered approach) ስለሚጠቀም ጥናቱን ከሌሎች ይለየዋል::

# ምዕራፍ አራት

## 4. የከምባታ ሀገረ ሰባዊ ትውን ጥበባት

### 4.1 ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት

የሀገረሰባዊ ጥበባትን /Performing folk arts/ ስናስብ የማህበረሰቡን ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊውን ዳንስ እና ሀገረሰባዊውን ድራማ የሚያጠና እንደሆነ አድርገን በመውሰድ ነው።[9] እነዚህ ፀዋትው ሲተወኑ በማህበረሰቡ ወግና ባህል መሠረት አስፈላጊዎቹ ነገሮች ሁሉ ተሟልተውና በስርዓት ተዘጋጅተው ነው። እዚህ ላይ ባህላዊው ልብስና መጊያጌጫዎች በመጀመሪያ ይነሳሉ።

በቃል ታሪክ አዋቂዎቹ (አቶ ኤርሲዶ፣ አቶ ደስታ) እና (በላቸው፣ 2001) መሠረት ከምባቶች ከጥጥ እና ከሱፍ የተሰሩ የጨርቅ ልብሶችን የመልበሱን ባህል ከአማሮችና ከወላይታዎች ከመውረሳቸው በፊት ገላቸውን የሚሸፍኑት በቆዳ ነበር። በተለይም ሴቶቹ በልዩ ልዩ እንቁዎች ያሸበረቁ የቆዳ ልብሶችን ይለብሱ ነበር።[10] እንደ አሁኑ ሙሉ በሙሉ ገላቸውን እንዲሸፍን ተደርጐ ሳይሆን በተለይ አፍረተ ስጋቸውን ለመሸፈን ሲባል ከወገባቸው በታች ሽብ በማድረግ ነበር። ከወገብ በላይ ያለው ክፍል ብዙውን ጊዜ አይሸፈንም። ወጣት ወንዶቹ ግን እርቃናቸውን ሲንጐማለሉ፣ ወጣት ለጃገረዶች ደግሞ አፍረተሥጋቸውን ከቆዳ በተሰራ ልብስ ሸፍነው ሲዘዋወሩ መመልከት ይቻል ነበር። ጐልማሳ ወንዶች ግን ሃፍረታቸውን ይሸፍናሉ።[11]

የወላይታ ሸማኔዎች የሱፍ ጨርቅ ልብስን ለከምባታ በማስተዋወቁ ረገድ አይነተኛ ሚና ተጫውተዋል። ሲጀመር ገደማ ከሱፍ የሚሰሩ ጨርቆች ይሰሩ የነበረው በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኙ ለነበሩ ባለሥልጣናት ነበር። ይህም የከፍተኛው መደብ አባላት የነበሩት በኢኮኖሚውም ሆነ በማህበራዊው ረገድ አቅሙ እንደነበራቸው ከማሳየቱ ባሻገር እራሳቸውን ከተራው ሰው ለመለየት እንደተጠቀሙበት አመላካች ነው። በጊዜ ሂደት

---

[9] ፊቃደ፣ 1991፣ 12

[10] Braukanper ፣ 80

[11] Straube, Helmut (ed.) 1963, 21 Westkuschitishe volker sud Athiopiens, Stuttgarta. ይህ ጥናት በጀርመን ቋንቋ የቀረበ ሲሆን (በላቸው፣ 2001) ወደ አማርኛ ከመለሰው የተወሰደ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እነዚህ የሱፍ ጨርቆች ወደ ሌሎችም አካባቢዎች በመስፋፋታቸውና ሰውም እያወቃቸው በመምጣቱ ሌሎችም ወንዶች መልበስ ጀመሩ። ሴቶቹ ግን በቆዳው ልብስ ብቻ ተወስነው ነበር። በአሁኑ ዘመን ግን ማንም ቢሆን ባህላዊውን የቆዳ ልብስ (የቆዳ እራፊ) የሚለብስ የለም። ከልብስነት ይልቅ ለመኝታ ምንጣፍነት እየዋለ ነው።

ከልብሱ በተጨማሪ ሌሎች መጊያጌጫዎችን መልበሱም የተለመደ ነበር። በሌሎቹም የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አካባቢዎች እንደሚታየው ሁሉ የነፍሳት ልባስ የሆኑ ቅርፊቶች[12] ከፍተኛ ሚና አላቸው። እነዚህ ቅርፊቶች፣ እንደ ዶቃ ያሉ ሆነው በአንገት፣ ላይ እንደ ሀብል፣ በእጅ ላይ እንደ አምባር፣ በእግር ላይ እንደ አልቦ፣ በጆሮ ላይ እንደ ጉትቻ የሚጠለቁ ሆነው የተለያየ ህብር ያላቸው ናቸው።

አንዳንዴም ከብረት፣ ከመዳብና ከቆዳ የተሰሩ መጊያጌጫዎችን በሴቶቹም ሆነ በወንዶቹ ገላዎች ላይ መመለከት ይቻል ነበር። በልዩ ልዩ ጭፈራዎቻቸው ወቅትም ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣ ከቆዳ የተሰሩ (ማተቦች)፣ የተለያዩ የሳር አይነቶችን በፀጉራቸው ላይ ሰክተው፣ እንዲሁም ከሸክላ የተሰሩ ነገሮችን ለመጊያጌጫነት ይጠቀሙባቸዋል። እነዚህ መጊያጌጫዎች የሚዘጋጁት በወጣቶች አልፎ አልፎም በህፃናት ሲሆን በጥቅም ላይ ሲውሉ የሚታየውም በልዩ ልዩ በዓላት፣ እና ጨዋታዎች ወቅት ነበር። ከነዚህ ውስጥ ዋነኞቹ የዘመን መለወጫ እና የመስቀል በዓላት ከፍተኛውን ቦታ ይይዛሉ። (ሌንጃ እና መሰላ)። ይህንን ወደፊት እንመለከተዋለን።

ለእነዚህም በዓላት ልጆች ከሣር የሚያዘጋጇቸው አምባሮች አሉ። እነዚህ የሳር አምባሮች በተለይ የመስቀልን በዓል መድረስ የሚያመለክቱ ናቸው። አምባሮቹም ለመስቀል ዋዜማ እንዲቃጠሉ የሚደረግ ሲሆን ምክንያቱም የአዲስ ዓመት (ወቅትን) መምጣትን ለማመልከት፣ አዲስ ተስፋ እና ብልፅግናን በመመኘት በትእምርትነት እንዲያገለግሉ ነው። አሮጌው ዘመን፣ አሮጌው ነገር፣ አልፏል፤ አዲስ ዘመን፣ አዲስ ነገር ይመጣል የሚል መልዕክት አለው። ከዚህም አምባር በተጨማሪ ከሸክላ የሚሰራና በቀለበት መልክ የሚዘጋጅ ጌጥም አለ። እነዚህንም በክሮች ላይ በማንጠልጠል ያጌጡባቸዋል።

---

[12] የእንግሊዝኛውን 'Shell' ለመተካት ነው የተጠቀምኩበት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እንዲሁም ወላጆቻቸው የልጆቻቸውን ፀጉር በመላጨት እንዲዋቡ የሚያደርጉበትም ሂደት አለ። ወንዶች ልጆችንም ሆኑ ሴቶች ልጆች ፀጉራቸውን እንዲላጩ ይደረጋል። ልዩነቱ የሴቶቹ ፀጉር ሙልጭ ብሎ ሲላጭ የወንዶቹ ግን ከሴቶቹ እንዲለይ ከወደ ግንባራቸው፣ ከፊት ለፊት በኩል መጠነኛ ፀጉር ብቻ ይተውላቸዋል። ቁንጮ መሰል ነገር ማለት ነው። ከዚህ ውጪ ጉልማሶቹ ፀጉራቸውን እንዲላጩ የሚደረገው የቤተሰባቸው አባል በሞት ሲለይ ለሀዘን ምልክት ነው። ሴቶቹም ከፍተኛ የቤተሰብ አባላቸው በሞት ሲለያቸው ለሀዘን ሲሉ በጥፍሮቻቸው ወይም በእሾሃማ ቅጠሎች ፊታቸውን እየቧጨሩ ሀዘናቸውን ሲገልፁ ይታያሉ። ከዚህ ውጪ የሚገኘው በወንዶቹ ክንድ ላይ የሚታየው ጠባሳ ነው። በጠባሳው ብዛት፣ ስፋት አይነት የተጠበሰውን ወንድ ጀግንነት፣ ድፍረት፣ ጥንካሬ የሚወክሉ ነበሩ። አሁን አሁን ግን እየቀሩ ናቸው።

አልባሳትና መጊያጌጫዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። በጥንቱ ዘመን የነበረው ትወና ለደስታ፣ ለሀዘን፣ ለጨዋታ ወዘተ. በዚህ መልክ ተከሽኖ ይቀርብ እንደነበረ ለመግለፅ ያህልና ባህሉን ለማስተዋወቅ መጠነኛ ፍንጭ ይሰጣል በሚል እምነት ነው የቀረበው።

### 4.1.1. ሀገረሰብ ዘፈን

የከምባታን ሀገረሰባዊ ዘፈን በምንመለከትበት ጊዜ የሙዚቃው ድርሰት በሁለት መልኩ ሊደረስ ይችላል። የመጀመሪያው አስቀድሞ ተዋኙ ደርሶና አጥንቶ ተዘጋጅቶበት ለትወና ወደ አውዱ የሚመጣበት ሁኔታ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ በአንድ በተፈጠረ ክስተት ላይ ወዲያው ሁኔታዎችን እያገናዘበ የሚደርስበትና የሚተውንበት ሂደት ይታያል። የከምባታ ሀገረሰብ ዘፈን በአብዛኛው ሁሉም የባህሉ ባለመብቶች የሚያውቁትና የሚጫወቱት ሲሆን፣ አሁን አሁን ግን ለተለዩ ወገኖች የተተው የሚመስልበት አዝማሚያ አለ። ይህም ከእምነት ጋር ተያያዞ ሲንፀባረቅ ይታያል።

በተለያዩ ጥናቶች እንደሚታየው[13] ከ85% በላይ የከምባታ ብሔረሰብ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ነው በመሆኑም የሀገረሰብ ዘፈናቸውን እንደ ሃጢያት፣ እንደረከሰ ነገር አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ ስላላቸው በዚህ ተግባር ላይ አይሳተፉም፤ ባህላዊ የሙዚቃ

[13] ፍሬህይወት፣ 1997

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

መሳሪያዎቻቸውንም ሳይቀር አውድመዋቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህን ተግባር እየተወኑት የሚገኙት በከምባታ ብሔረሰብ ዘንድ የተናቁ፣ የተገለሉ የሚመስሉት የፉጋ (የእጅ ባለሙያዎቹ) ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ጥናት በሚሰራበት ወቅትም የተወሰኑ ትወናዎችን ለመቅረፅ በሚሞከርበት ወቅት እነዚሁ ወገኖች ናቸው በሙሉ ፈቃደኝነት የተባበሩት፡፡ ጥቂት ቢሆኑም ሌሎቹም መጠነኛ ፍላጐት አሳይተዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት የሀገረሰባዊውን ዘፈን በተመለከተ ከተለየ መደብ በመጡ አባላት መተወኑና በሌሎቹ ዘንድ ደግሞ እንደ ሃጢአት የመመልከቱ እምነት በብሔረሰቡ ዘንድ አለ ማለት የሚቻል ይመስላል፡፡

ሙዚቃዊ ትወና ንቁ የተመልካች ተሳትፎን፣ እና የሙዚቃዊ መሳሪያዎችን አጀብ ይሻል፡፡ ወይም ተመልካቹ ፍዝ ተመልካች፣ ዘፈኑም ያለሙዚቃ መሳሪያ ሊተወን የሚችልበት አጋጣሚ አለ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በከምባታ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ትወና ወቅት ሁለቱም ክስተቶች ተስተውለዋል፡፡

ፉጋ (እጅ ጥበብ ባለሙያዎቹ) በሚተውኑበት ወቅት የሀገረሰብ የመዚቃ መሳሪያቸውን ይዘው፣ በተመልካቾች ታጅበው ሲሆን፣ የሚያጅቧቸውም ሆኑ የሙዘቃ መሳሪያዎቹን የሚጫወቱት ከፕሮቴስታንት እምነት ውጪ ያሉት ብቻ ናቸው፡፡ ፕሮቴስታንት የሆኑት ወገኖች ግን ከዳር ቆመው ከመሳቅ፣ ከመሽማቀቅና ከማፈር ውጪ የተሳታፊነት ባህሪ በጥናቱ ወቅት አልገጠመም፡፡

ፉጋ ተብለው የተፈረጁትን ወገኖች የሚለዩዋቸው በርካታ የአተዋወን ባህሪያትም ይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ ያለምንም የሙዚቃ መሳሪያ፣ ተፈጥሯዊ ድምፃቸውን ብቻ በመጠቀም የሚያወጧቸውን ዜማዎችና ሙዚቃዊ ቅላፄዎች ላደመጠ በእርግጥም ለከምባቶቹ ከሙዚቃ መሳሪያ ይልቅ ከፍተኛ ትወናዊ ዋጋ ያለው ድምፃቸው ነው ያሰኛል፡፡ በእጃቸውና በመላ አካላቸው የሙዚቃውን ቅላፄ ጠብቀው የሚያሳዩት እንቅስቃሴም የተለዩ ያደርጓቸዋል፡፡

በከምባቶቹ ዘንድ ሙዚቃዊ ትወና ሁልጊዜ ማለት ይቻላል፣ በመቅዳት፣ በማስመሰል ሊሆን ይችላል፣ ወይም በድራማዊ እንቅስቃሴ ሊታጀብ ይችላል፣ የሚተወነው በዋናው ተዋኝ እና በተመልካቹ የጋራ ቅብብሎሽና ውዝዋዜ ነው፡፡ የዚህም ውጤት የሚያሳየው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በሙዚቃው ትወና ወቅት የቃላዊ ተስተላልፎ ህልውና በትወናው ውስጥ መሆኑን ነው፤ ሲተወን ተስተላልፎ አለው፤ ሳይተወን ደግሞ ተስተላልፎ የለውም ማለት ይቻላል።

ብዙ ጊዜ ሰዎች ሀገረሰባዊ ዘፈናቸውን ሲጫወቷቸው፣ ሲተውኗቸው አይታዩም። ይሁን እንጂ ዜማ ፈጣሪዎች ባይሆኑ እንኳን በቃል አስተላላፊዎችና፣ በቃል የሰሟቸውን፣ የተማሩዋቸውን፣ ወይም የሽመደዷቸውንና ተዋኞቹ አቀንቃኞች ያዳመጧቸውን ሁሉ ንቁ አስተላላፊዎች ሆነው የሚታዩበት አጋጣሚ አለ። ከአውዳቸው ውጪም ሲያንጐራጉሯቸው የሚታዩበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ የቀብር፣ የሃይማኖት፣ የሠርግ ዘፈኖች ላይ ይህ ይታያል። በዚህ ጊዜ የሚየጋጥመው ሁኔታ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ስሞችን መግደፍ፣ መቀነስ፣ ቃላት ወይም ሀረጋትን ማዛባት የመሳሰሉት ናቸው። ይህ የሚፈጠረው አንድም ሆነ ብለው ከሚያንጐራጉሩበት አውድ ጋር እንዲጣጣምላቸው ለማድረግ አሊያም ያዳመጧቸውንና የሽመደዷቸውን በመርሳት ሊሆን ይችላል።

በከምባታ ብሔረሰብ የሀገረሰብ የሙዚቃ መሣሪያዎችንና በሀገረሰብ ሙዚቃ ትወና ወቅት አብረው የሚቀርቡትን፣ ወይንም ትወናው የሚርቀርብባቸውን የቤት፣ የጦርና፣ የሙዚቃ ቁሳቁስ በማምረት ወይም በማዘጋጀቱ ረገድ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት ‹‹ፋቂ›› የሚባሉት ወገኖች ናቸው። እነዚህ ቁሳቁሶች በከምባቶች ቁሳዊ ባህል ውስጥ የሚካተቱ ቢሆኑም የሀገረሰብ ትውን ጥበባቱን ለማየት በምንነሳበት ወቅት የትወናውን ጥበባዊነት የሚያጐሉ ነገሮችን አብሮ ማጥናቱ ተገቢ በመሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ከምባቶች የራሱ መለያ ያለው የቤት አሰራር ባህል አላቸው። ጥንታዊው የቤት አሰራራቸውም በክብ መልክ የሚሰራ ሆኖ ከውስጥ በኩልም ሌላ ተጨማሪ ክብ እንዲኖረው ይደረጋል። የቤቶቹ ጥራት የክፍሎቹ ብዛት እና ስፋት እንደ ባለቤቱ አቅም የሚወሰን ነው። ይሁን እንጂ አማካዩ የከምባቶች ቤት ስፋት ከቤቱ መሀከል እስከ አንደኛው ጠርዝ ድረስ 5 ሜትር ይሆናል። ዙሪያውን በሸምበቆ የተገደገደ ግድግዳ ሲኖረው ጣራው በሰንበሌጥ (በከምባትኛ ዱፋ /duffa/ ይሉታል) የተከደነ ነው። ከጣራው አናት ጉልላቱ ላይ የወንድ ብልት ቅርጽ ያለው ከቤቱ መሀል ላይ ቆሞ ይታያል። ይህ የአባዊ[14] ስርዓት ትዕምርት ይመስላል። በድሮ ዘመን የከምባቶችን የመደብ ልዩነት እንዲያመለክቱ ሲባል ቤቶቹ ሁለት በሮች እንደነበሯቸው የቃል ታሪክ አዋቂዎቹ

---

[14]“patriarchal” የሚለውን እንዲተካ የገባ ነው።

ይገልፃሉ:: የቤቶቹ የውስጥ ይዘት የሚከተለውን ይመስላል:: ከቤቱ ውስጥ ከበሩ በስተግራ ወይንም በስተቀኝ[15] በኩል የቤት እንስሳት /ፈረስ፣ በሬ፣ ላም፣ ጥጃ ወዘተ/ ይታሰሩበታል:: በተቃራኒው በኩል አልጋዎች ይገኛሉ:: ከቤት እንስሳቱ እና ከማብሰያው በላይ (ከጣራው ስር) በቆጥ መልክ የተሰሩ ደርቦች ይገኛሉ:: እነዚህም በስተግራ የወንዶች፣ በስተቀኝ የሴቶች (የባል፣ የወንድ ልጆች እና የሚስት ሴት ልጆች) ንብረቶችና ቁሳቁሶች የሚቀመጡባቸው ናቸው:: የማብሰያውን ስፍራ እና የልጆችንና የሴቶችን የመመገቢያ ስፍራ ከቤቱ ውስጥ በሌላ ተጨማሪ ግድግዳ ይለዩታል:: ከቤቱ መግቢያ በር ግራ እና ቀኝ እንደ ዋሻ፣ መሸሸጊያ ወይም መተላለፊያ ጉሬ[16] የሚያገለግል ምስጢራዊ መተላለፊያ ይኖራል:: ይህ መተላለፊያ የቤቱ አባ ወራ ጠላቱን ተደብቆ ለመመልከቻነትና፣ ጠላቱ ወደ ቤቱ ዘለቆ ቢገባም በአንድ ቀዳዳ ወጥቶ በጦሩ ወግቶት ተመልሶ ለማምለጫና ለመሰወሪያነት ያገለግላል::

በባህላዊ ቤቱ ውስጥ የተለያዩ ቅርጫቶች ይገኛሉ:: እነዚህም በአብዛኛው በሴቶቹ የሚሠሩ ሲሆኑ አገልግሎታቸውም ጥራጥሬ ለማቅረቢያ (የቡና ቁርስ)፣ ወተት ለማለቢያ፣ ወዘተ የሚያገለግሉ ናቸው::

ከነዚህ በተጨማሪ ከእንጨት የሚሰሩ መቀመጫዎች፣ ጉንጋ /gonga/ የሚሏቸው መክተፊያዎች፣ የድንጋይ ወፍጮዎች፣ እንስራዎች ወዘተ ይገኛሉ:: አነስተኛ የወተት በርጬማዎችና፣ የመኝታ መደቦችም በቤቱ ዙሪያ ይታያሉ:: በድሮው ዘመን እነዚህ መደቦች ይሰሩ የነበረው ከሸክላ አፈር ነበር:: በአሁን ዘመን ግን ከእንጨት (ከብረት) በተሰሩ አልጋዎች ተቀይረዋል::[17]

በከምባቶች ባህላዊ የመኖሪያ ቤቶች ውስጥ ከምናገኛቸው ባህላዊ መሳሪያዎች ውስጥ ጋሻዎችና የሙዚቃ መሳሪያዎችም ይገኛሉ:: እነዚህ ባህላዊ መሣሪያዎች በድሮ ጊዜ ይሰሩ የነበሩት ከከብቶች (ላም፣ በሬ) ቆዳዎች ነበር:: ጋሻዎቻቸው በአብዛኛው ሞላላ የሆነ ቅርፅ ያላቸው ናቸው:: ፉከራን በመሳሰሉ ባህላዊ ትወናዎች ላይ ይታያሉ:: ከበሮ በከምባቶቹ ቀርቤታ የሚሉት ባህላዊ መሳሪያ ከፍተኛ ዋጋ ያለው የመተወኛ መሳሪያ ነው:: ከምባቶች

---

[15] በጥናቱ ወቅት የተዋረሱት ሙዚየም እና የዶ/ር ቦጋለች ባህላዊ ቤቶች የሚያሳዩት ግን ከበሩ በስተግራ በኩል ነው::

[16] የውስጥ ለውስጥ መተላለፊያ ነው

[17] Teshome Tadesse. 1984. 37 Material Culture of the Wolayeta, Addis Ababa University. B.A Thesis. UP.

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሁለት አይነት ከበሮዎች አሏቸው፡፡ ሁለቱንም በተለያዩ አውዶች ላይ ነው የሚጠቀሙባቸው፡፡ አነስ የሚለውና ከስር ጠበብ ከላይ ሰፋ ተደርጐ ከሸክላ ከተሰራ በኋላ ከታችም፣ ከላይም በቆዳ የሚለበደው ከበሮ በሚከተሉት አውዶች ላይ ያገለግላል፡፡

- በባህላዊ ጭፈራዎችና ውዝዋዜዎች ታጅቦ የግዝረት በዓል ሲፈጸም፣
- በባህላዊ የሠርግ ጭፈራ ላይ፣
- በመስከረም ወር መጨረሻ አካባቢ በሚደረገው የልጃገረዶች ባህላዊ የእንገጫ ነቀላ ወቅት ወጣት ወንዶቹ የወደፊት የውሃ አጣጫቸውን ለመምረጥ በሚያደርጉት ባህላዊ ትወና ወቅት - ለመተጫጨት፣
- በምሽት ከገበያ ሲመለሱ /ድሮ/ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ከዚህ ሌላ ትልቅ (ግዙፍ) የሆነ የከበሮ አይነትም አላቸው፡፡ የዚህ አይነቱ ከበሮ አገልግሎት የሚሰጠው አንድ ታዋቂ፣ የተከበረ የጐሳ አባል በሞት በሚለይበት ወቅት ነው፡፡ ይህን አይነቱን ከበሮ የሚጫወቱት ፉጋዎች ናቸው፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አንድ ትልቅ ሰው ሲሞት የሚቹ ቤተ ዘመዶች ይህንን ትልቅ ከበሮ የሚመታውን ሰው ከበውት በመዞር ከከበሮው በሚወጣው የሚያስገመግም ሙዚቃዊ ቅላጼ ታጅበው በማርገድ ሀዘናቸውን ይገልፃሉ፡፡ እስከ ስርዓተ ቀብሩ ፍፃሜ ድረስም ከበሮው በፉጋዎቹ ያለማቋረጥ ይደለቃል፡፡ትወናውም ይዘልቃል፡፡

ይህ ግዙፍ ከበሮ የእንግሊዝኛውን "V" ቅርጽ የሚመስል ሲሆን እንደ አነስተኛው ከበሮ[18] በሁለቱም አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ የማይከደን ሲሆን፣ የላይኛው ክፍል ብቻ ነው በቆዳ የሚለበጠው፡፡ የታችኛው ክፍል ድፍን ሳይሆን በቆዳ ብቻ ይሸፈናል፡፡ እንዲሁም ትንሹ ከበሮ ከሸክላ የሚሰራ ሲሆን ይኸው ግን እንጨት ተፈልፍሎ የሚሰራ እንደሆነ የቃል ታሪክ አዋቂዎቹ ይገልፃሉ፡፡

በድሮ ዘመን ከምባቶች ከከበሮ በተጨማሪ ጥሩምባ[19] ይጠቀሙ ነበር፡፡ እነዚህ ጥሩንባዎች ከከብት ቀንድ ወይም ከእንጨት የሚሰሩ ነበሩ፡፡ አሁን አሁን ግን ከብረት፣ ከኒኬል በሚሰሩ ቁሳቁሶች ተተክተዋል፡፡

---

[18] ቅርጹ ሞላላ እና አነስተኛ ነው፡፡ በሁለቱም አቅጣጫ ከላይም ከታችም በቆዳ ይለበጣል፡፡

[19] አይሁዶች ቀንደ መለከት ከሚሉት የሙዚቃ መሳሪያ ጋር ተመሳሳይ ጥቅም ይሰጣል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የጥሩንባዎቹ አገልግሎትም የሰውን ሞት ለማወጅ፣ ቀባሪ እድርተኞችን ለመጥሪያና ለቀብርም እንዲወጡ ለማንቂያ ህዝባዊ የስብሰባ ጥሪዎችን ለማስተላለፍ፣ ሠርገኞች ወደ ሙሽሪት ቤት ሲሄዱ መዳረሳቸውን ለማሳወቅና ከሠርጉ ቤት ሲወጣም እንኳን ደህና መጣችሁ፣ በሰላም ተመለሱ፣ የሚሉ መልእክቶችን ለማስተላለፍ ይጠቀማሉ:: ክራር፣ ዋሽንት፣ የመሳሰሉ የሙዚቃ መሳሪያዎችም በከምባታ ይገኛሉ:: በአብዛኛው በዋሽንቶቹ የሚጠቀሙት እረኞቹ ሲሆኑ ተፈጥሮን እያደነቁ፣ ድካማቸውን እያስታወሱ፣ የፈቀዷትን ልጃገረድ ስም እየጠሩ፣ ውበቷን እያደነቁ፣ ወዘተ የሚያንጐራጉሩበት ነው:: ክራሩን ደግሞ የተገረዙ ወጣቶች እና ሙሽሮች (ወንዶቹ በአብዛኛው) የሚጫወቱት እንደሆነ የቃል ታሪክ አዋቂዎቹ ይገልፃሉ:: ይሁን እንጅ ሌላውም የህብረተሰብ ክፍል ሊጫወትባቸው እንደሚችል ጨምረው ገልፀዋል::[20] እነዚህን እና ከላይ የተገለጹትን ሙዚቃዊ ትዋኔዎች በተመለከተ በቀጣዮቹ ምእራፎችም ከሌሎች ርእስ ጉዳዮች ጋር እያያዝን ወደፊት በስፋት የምንመለከታቸው ስለሆኑ ይህን በዚሁ ቋጭተን ወደ ቀጣዩ ክፍል እንሸጋገር::

### 4.1.2 ሀገረሰብ ዳንስ

ከምባቶች የማንነታቸው መገለጫ የሆነ የተዋበ ሀገረሰባዊ ዳንስ ባለቤቶች ናቸው:: በከምባቶቹ ዘንድ ዳንስ ደስታቸውን የመግለጫ እና ራሳቸውንም ሆነ የሚመለከታቸውን ዘና ማድረጊያ ነው:: የሥራ ጫና (እርሻው፣ ንግዱ፣ ወዘተ.) ቀነስ በሚልበት እና ልዩ ልዩ ክብረ በዓላት በሚኖሩባቸው ወቅቶች ለዳንስ ዋነኛ አጋጣሚዎች ተደርገው ይቆጠራሉ:: በከምባቶች ዘንድ ለመደነስ ወይም ላለመደነስ ገደብ የሚጣልበት የለም:: ለሁሉም ግልፅ እና ክፍት ነው:: ማንም መሳተፍ ይችላል:: በመሆኑም ወንዶች፣ ሴቶች፣ አዋቂዎች፣ ጐልማሶች፣ ሕፃናት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሲደንስ መመልከት ይቻላል:: በተለይም እንደመስቀል ባሉ ሃይማኖታዊ በዓላት ላይ እና ሠርግ በመሳሰሉ ልማዳዊ ትወናዎች ይህን መመልከት ይቻላል::

በከምባታ ይህን ያህል ጐልቶ የወጣና በተለይ ሊጠቀስ የሚችል የዳንስ ባለሙያ እምብዛም አይገኝም በአንዳንድ ሃይማኖታዊ ተፅእኖዎች ምክንያት የተለዩ የህብረተሰብ ክፍሎች (እንደ ፉጋ ያሉት) ሲደንሱ፣ ክርስቲያኖቹ ግን ሃይማኖታዊ ገደብ ተጥሎብናል በሚል

---

[20] አቶ አርሲዶና አቶ ወርቁ በቃለ መጠይቅ የገለጹት::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ራሳቸውን ሲያገሉ ይታያሉ:: ይሁን እንጂ በድብቅም ይሁን በሃይማኖታዊ አምልኮዎቻቸው ላይ የሚያሳዩት ዳንስ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ተመሳሳይ የሆነ የዳንስ እንቅስቃሴ መኖሩን ለመገንዘብ ይቻላል:: የከምባቶቹ የዳንስ እንቅስቃሴ ከተናጥል ይልቅ የቡድን እንቅስቃሴ የሚጐላበት ነው:: የተናጥል ዳንሰኛ ማግኘት ቀላል አይደለም:: ዳንሳቸው በቡድን የሚከወን ነው:: ማንኛውም በዳንሱ ላይ የሚሳተፍ ሰው አላፖንቹ ተብሎ ይጠራል::



ምስል 2... የኤኔሬ ጨዋታ



ምስል 3... ሆሌ ጨዋታ

የከምባታ ብሔረሰብ ዳንስ በሙዚቃ መሳሪያ ሊታጀብ፣ ያለሙዚቃ መሳሪያም ሊቀርብ ይችላል:: ዋነኛው የሙዚቃ መሳሪያቸው ‹‹ቀርቤታ›› (ከበሮ) ሲሆን እሱም ሁለት አይነት መሆኑን በቀዳሚው ክፍል ተገልጿል:: እነዚህን ከበሮዎች የሚጫወቷቸው ሰዎች ጠርቤታ አላፖንቹ ተብለው ይጠራሉ:: የከበሮ ተጫዋቾቹ አነስተኛዋን ከበሮ በጭንና በጭናቸው መካከል አድርገው፣ የሁለት እጆቻቸውን መዳፎች እያፈራረቁ ሲመቱባቸው በሚፈጠረው ቅላፄ፣ ዜማ እና ምት ነው ዳንሱ የሚከወነው:: ከሙዚቃው ምት ጋር አብሮ የሚሄድ የወንዶቹ እና የሴቶቹ የጋራ የቅብብሎሽ ድምጽ ለዳንሳዊው ትወና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው::

ብሔረሰቡ የራሱ የተለየ የዳንስ እንቅስቃሴ አለው፡፡ የዳንሱ እንቅስቃሴ አንድ ወጥ የሆነና በዝግታ፣ በተመሳሳይ ውዝዋዜና በመደጋገም የሚተወን ነው፡፡ በአመዛኙ አንገት፣ እጅና ከወገብ በላይ ያሉት የሰውነት ክፍሎች ናቸው የሚንቀሳቀሱት፣ ለትወናው የሚውሉት፡፡ በእግር የሚደረገው እንቅስቃሴ ጥቂት ነው፡፡ ዶቃ፣ ክታብ፣ ጨሌ፣ ስር፣ ቀጭን በትር፣ የነብር ቆዳ የመሳሰሉት ተለብሰው ነው ባህላዊ የሆነውን ዳንስ የሚያቀርቡት፡፡

የከምባታ የዳንስ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ የመከሰቻ አጋጣሚዎች እና ለክብረ በዓላት በሚተወኑበት ጊዜ የተለያዩ ስሞች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ፣ የመስቀል በአል ዳንስ ግፋታ ይባላል፣ በአንገት ሲከወን ጉጉለቻ ይባላል፡፡ ኤናሬ ጌጊሺ ወዘተ. በከምባታ የዳንስ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደሌሎቹ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች የመቀመጫ አካባቢ እንቅስቃሴ ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ በሁሉም ትዋኔዎች ማለት ይቻላል ከምባቶች ለአንገት እና ለከወገብ በላይ እንቅስቃሴያቸው፣ ውዝዋዜያቸው ትኩረት ይሰጡታል፡፡ እንዲሁም የቀኝ እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ በማድረግና በማንቀጥቀጥ፣ የአንገታቸውንም አንጓ እጥፍ ዘርጋ በማድረግ የሚያሳዩት አተዋወን የተለየ መለያቸው ይመስላል፡፡ ይህ ባህላዊ ውዝዋዜ የከምባቶችን ዳንስ የተለየ የሚየደርገውና ይበልጥ ሳቢ፣ ማራኪና መሳጭ እንዲሆን ያስቻለው ነው፡፡

ምስል 4 … ህብር ጨዋታ



### 4.1.3. ሀገረሰብ ድራማ

በከንባታ ብሔረሰብ የሚተወኑ ሀገረሰብ ድራማዎች ቡሁለት መልኮች የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚህም በዝርው መልክ የሚቀነቀኑና በግጥም ፣በመነባነብ መልክ የሚቀርቡት ናቸው፡፡ ዋነኛው የድራማዊ ጥበባቸው ቅርጽ ግን በምልልስ የሚቀርብ ነው፡፡ በጥናቱ እንደታየው የምልልሳቸው ይዘት በማህበራዊ ኑሯቸው የሚፈጠሩ ችግሮችን፣ ግጭቶችን ተቃርኖዎችን ስሜት በተሞላ መንገድ ያቀርባሉ፡፡ እነዚህ ናቸው ለትወናቸው ህይወትን የሚሰጡት፡፡

የከንባቶች ሀገረሰብ ድራማ ተዋኙ ብቻውን በማቀንቀን ለታዳሚዎቹ የሚያቀርብበት እና ታዳሚዎቹም በመዝለል፣ በፊታቸው ላይ የሀዘን፣ የደስታ፣ የመደመም ወይም የመዝናናት ገጽታዎችን በማሳየትና ምላሽም በመስጠት ትወናውን ያዳምቁታል። ትወናወን ለማስዋብም፣ ተዋኙ ከተፈጥሮዊ ማንነቱ በተጨማሪ የዶሮ ወይንም የሰጎን ላባዎችን ራሱ ላይ በመሰካት፣ በልብሶቹ ላይም ልዩ ልዩ መጊያጊያጫዎችን በመሰካት፣ በማንጠልጠል ለትወናው ተጨማሪ ውበት ይሰጣል። አዳማቂዎቹም ከላይ በሰፊው የተዘረዘሩትን ባህላዊ አልባሳት ለብሰው የትወናው አካልና ለትወናውም ተጨማሪ ውበት ያጎናጽፉታል።

የብሄረሰቡ ሀገረሰብ ድራማ በባህሪዉ ህዝባዊ ትዋኔ ነው። ስለሆነም ድራማው የሚቀርበው ማህበረሰቡ ሊረዳቸው በሚችላቸው ትእምርቶች ነው። እነዚህም የሚቀርቡት በታወቁ በዓላትና ክብረ በዓሎች ላይ ነው። ለምሳሌ፣ ወቅትን ጠብቀው በሚመጡ፣ እንግጫ ነቀላ፣ አበባ ለቀማ፣ አዝመራ ሲደርስ፣ በልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ በዓላት ለምሳሌ መስቀልን በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ላይ ነው።

ህዝባዊ ድራማዎቻቸው የሚተወኑት ደግሞ ትወናውን የመተዳደሪያ ሙያቸው ባደረጉ ተዋኞች (ስልጠና በወሰዱ) በመሆኑ በተለይ በተዘጋጁ ኘሮግራሞች ላይ ከተለያዩ ስፍራዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ለሚገኙ ታዳሚዎች የሚቀርብ ነው።በክልሉ በተለያዩ ደረጃዎች ተቋቁመው በሚንቀሳቀሱት የኪነት ቡድኖች የሚቀርበው ድራማ ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ዝግጅቱ የሚቀርበውም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ አዳራሽ፣ በክፍያ ወይም ያለ ክፍያ ሊሆን ይችላል። መድረኰች ቋሚ ወይም ተለዋዋጭ ናቸው። በሀገረሰብ ድራማ የታዳሚው ትኩረት በትወናው ጥበብ ላይ ነው። ትወናዊ ጥበቡ እንዴት ተተወነ፣ ማራኪ ነው፣ ቀልብን ይገዛል፣ ተዓማኒ ነው እያለ በትኩረት ይከታተለዋል። ከመልእክቱ ይልቅ ትኩረቱ ለእነዚህ ነው። ስሜቱን የገዛ እንቅስቃሴ ከተመለተ ምላሹን በጭብጨባ፣ በፉጨት፣ ይገልፃል፣ ሲነሽጠውም ባለበት ሆኖ ይቁነጠነጣል። ካልሆነም በጩኸት፣ በማጉረምረም ድምጹን ያሰማል፣ ጥሎም ሊወጣ ይችላል። አጠቃላይ የትወናው መልክ የጅል ባህሪን ተላብሶ በማሳቅ ወይም እንደ እብድ እና ዛር እንደወረደበት ሰው በማጓራትና በመንቀጥቀጥ መቅረብ፣ ልዩ ልዩ ውዝዋዜዎችን (የአካል እንቅስቃሴዎችን) በማሳየት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ታዳሚውን ለማስደሰት መሞከር፣ አንዳንዴም በዘፈን የታጀበ እንቅስቃሴ በማድረግ ለማስደነቅ መሞከር ይታዩበታል።

የከምባታ ሀገረሰብ ድራማ አተዋወን እነዚህን ሁሉ ቢያካትትም በዋነኛነት ግን ምልልሱ ይጐላበታል። ይሁን እንጂ በቀላሉ ለመለየት አዳጋች የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። ለምሳሌ ውዝዋዜ፣ ድራማ፣ ሙዚቃ በአንድነት የሚቀርቡበት አጋጣሚ ይከሰታል። አብረውም የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። ሙዚቃ ካለ ውዝዋዜ፣ መጠነኛም ቢሆን የሰውነት እንቅስቃሴ መከተሉ ሊኖር ይችላል። በሰውነት እንቅስቃሴው ደግሞ ትውናዊ የሆኑ ባህሪያት፣ በእጅ፣ በፊት፣ በአይን ልዩ የፊት ገጽታዎች በማሳየት ወዘተ. ሊከሰቱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ይህ ድራማ ነው፣ ያኛው ደግሞ ሙዚቃ ነው ለማለት አዳጋች ይሆናል። እንዲህ ያለውን ግራ መጋባት ለማስቀረት ይመስላል ሙዚቃዊ ድራማ[21] የሚለውን ስያሜ ምሁራኑ የሚሰጡት በዚህም ጥናት ዘፈኑ ሲነሳ የዳንስ እንቅስቃሴዎች የሚታዩባቸው አጋጣሚዎች አብረው ተገልፀው ይገኛሉ። ስለዳንሱ ሲወራም የድራማ ፀባዮች አንድ ላይ የተገለጹበት አጋጣሚ ይታያል። እነዚህን ሦስቱን ለያይቶ ለማቅረብ ምን ያህል አዳጋች እንደሆነ እና በሦስቱ መካከል ያለውን ትስስር[22] አስረጂ ይመስላል።

### 4.1.4. የሀገረሰብ ዘፈን፣ ዳንስ ድራማ መስተጋብር

ሀገረሰብ ሙዚቃ፣ ዳንስና ድራማ የሚዛመዱባቸው በርካታ ገፅታዎች አሏቸው። በሰው ልጅ የብቸኝነትና የአብሮነት አኗኗር ከተጀመረበት ግዜ አንስቶ አንዱ በአንደኛው ውስጥ ወይንም አንዱ ከአንደኛው ጋር ተያይዞ የሚከሰት ቃላዊ ትውናዊ ጥበብ ለመሆኑ አንዳንድ አስረጂዎችን ማንሳት ይቻላል።

ሙዚቃ ዳንስ እና ድራማ ከዜማ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። ዳንሱ ለዘፈኑ እይታዊ እና አካላዊ ቅርፅ የሚያላብሰው ነው። ዘፈኑ ሲደመጥ፣ ዳንሱ በአካላዊ እንቅስቃሴ ይተገበራል። የሚደመጠውም ሆነ የሚተገበረው ደግሞ በስርዓት በሚፈጠረው ዜማ ይሆናል። ሌላኛው ደግሞ የጋራ የሆነ ተግባራቸው ነው።

---

[21] (Loger D. Abrams, in Dorson, 1972, 355) ዳንስ ድራማ ይለዋል።
[22] (ፈቃደ, 1991, 12) ይህንን ሃሳብ ያጠናክረዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ምልልስ (dialogue) ዋነኛ ባህሪው የሆነው ድራማ፣ ከዳንሳዊ ጥበብ እና ከሙዚቃዊ ጥበብ ጋር የሚያመሳስላቸው ሁለተኛው ነጥብ የሆነው፣ ሦስቱም ጥበቦች ሙዚቃዊ ዜማን እየጠበቁ በአካላዊ እንቅስቃሴ መተግበራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አንድን መነባንብ በቅብብሎሽ የሚያቀርቡ ሁለት ሰዎች ከአንደበታቸው የሚያወጡት ድምፅ መውረድ፣ መውጣት፣ መርገብ፣ መጠንከር ወዘተ. በሚፈጥረው ሙዚቃዊ ቅላፄ እና ዜማ ላይ ተመስርቶ (ተመርቶ) ለአውዱ ተስማሚ የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ማቅረብ ይቻላል፡፡ በዚህ ወቅት የሚፈጠረው አካላዊ እንቅስቃሴ ዓላማም ተግባራዊና ጥበባዊ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

ይህ ተግባራዊና ጥበባዊ ፋይዳ ከትዋኔው ዓላማ የሚመነጭ ነው፡፡ ይህንን ለመግለፅ ይረዳ ዘንድ ለምሳሌ የሚያግዙንን የከምባታ ዘፈኖችና ዳንሶችን ጠቅለል አድርገን እንቃኝ፡፡

ምስል 5 … የግፋታ ጨዋታ



የከምባታ ብሔረሰብ ባህላዊ ጨዋታዎች በርካታ ናቸው፡፡ በመስቀል በዓል ወቅት (በመሰላ)፣ በዋዜማው እና በዕለቱ የሚጫወቷቸው ሙዚቃዎችና ዳንሶች አሉ፡፡ አንዱ ‹‹ሆሌ›› ይባላል፡፡ በመስቀል ማግስት ወይንም መስቀል በታረደ ሁለተኛና ሦስተኛ ቀናት የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡ ወንዶች አበባ በመያዝ በየቤቱ እየዞሩ የሚጨፍሩት ጨዋታ ሲሆን ትርጉሙ ‹‹በሁለት እጅህ ስፈር›› በመስቀል ስስት የለም፣ የጥጋብ ወቅት ነው ማለት ነው፡፡ ሌላኛው ጨዋታ ‹‹ግፋታ›› ይባላል፡፡ በእርግጥ ግፋታ ከመስቀል በዓል ውጪም የሚጫወቱት ህዝባዊ ዘፈን ነው፡፡ ‹‹ህብር›› ጨዋታ ማለት ሲሆን ደስታውንና ሀዘኑን፣ የደረሰበትን ጭቆናና ግፍ ወዘተ. ሁሉ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በአደንና በጅጊ፣ በአጨዳ ወቅት ሁሉ ይህንን ጨዋታ መጫወቱ የተለመደ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ‹‹በመርሺ›› በመስቀል ደመራ ወቅት ይበልጥ ደምቆ እንደሚጫወቱት የባህሉ አዋቂ የሆኑት አቶ ወልደ መስቀል በቃለመጠይቅ ወቅት ገልፀውታል፡፡ ደመራው ተለኩሶ፣ ዙሪያውን ከበው በፀሎትና በምረቃ ሁሉ የሚጫወቱት ሲሆን በዚህ ጨዋታ ወንድ ሴት አይለዩበትም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ይጫወተዋል፡፡

ሌላኛው ጨዋታ ‹‹ኤኤሬ›› ይባላል፡፡ ትርጉሙ የመስቀል ወፍ ማለት ነው፡፡ ይህች ወፍ በዓመት አንዴ የምትመጣ ሲሆን፣ የመስቀልን በዓል መድረስ እንደምታመላክት ይታመናል፡፡ ጨዋታው እንደ ወፏ ክንፍ ተጫዋቾቹ እጆቻቸውን ወደ ግራና ወደ ቀኝ በመዘርጋት ክንፍ መሰል ቅርፅ በመስራት የሚከወን እንቅስቃሴ አለው፡፡ ሌላው እና በመስቀል ማግስት የሚጫወቱት ዘፈን እና ዳንስ የሚታየው በ‹‹ባሊ ሄሌሌ›› ነው፡፡ ባሊ ሄሌሌ ማለት የበዓል ንግስት ማለት ነው፡፡ ይሄንን የሚጫወቱት ወንዶች ሲሆኑ ወንዶቹ የሴቶቹን ቀሚስ ለብሰው ነው፡፡ ወንዶች ለሴቶች ያላቸውን ክብር እንደሚያመለክት ያምኑበታል፡፡ በዚህ ጨዋታ ወንዶቹ የሴቶቹን ቀሚስ ለብሰው በየቤቱ ሴቶቹ ያዘጋጁትን ምግብና ባህላዊውን ቦርዴ እየተመገቡ እየዞሩ የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡ እነዚህ በመስቀል በዓል አከባበር ወቅት የሚስተዋሉ ሀገረሰብ ጨዋታዎች ናቸው፡፡

ሌላው የሠርግ ጨዋታ ነው፡፡ ‹‹አና ኢልቲኪ በቲኬ ሚቲ ወሬ ለሱ ኤቢቲ›› አባት እንኳን ወልደህ ለዚህ ወግ ማዕረግ ደረስክ፣ እናት እንኳን ወልደሽ ለዚህ ወግ ማእረግ ደረስሽ ማለት ነው፡፡ እናቶች ሲወልዱ የሚጫወቱት ጨዋታ ኢሎ ኢሊሊ ኢሎ፣ ኢሎ ኢላንቺ ኢሊሊ›› ወላድ እናት እንኳን ምጥሽ ቀለለ እያሉ የሚጫወቱት ጨዋታ አለ፡፡ በግርዘት ወቅትም ‹‹ሌንጃ›› የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡



ምስል 6 … የባሌ ሄሌሌ ጨዋታ

“ሌንጁ ዋሌ ንጉሣሀ፣ ለሱ ለዲቃሎ፣ ለሱ ለዲቃሎ፣ ንጉሣ ጉራ ሌንጁ ለጨዋሉ›› ከብቶች ጥጆችን ወለዱ፣ ማለት ነው፡፡ ሌንጃ የእንቁጣጣሽ ወቅት ነው፡፡ ግርዘቱ የሚደረገው በዚህ ወቅት ስለሆነና እርሻው የሚጠናቀቅበት፣ ሥራ የሚጠናቀቅበት ወቅት ስለሆነና የእረፍት ወቅት በመሆኑ እንዲሁም ከፊት ለፊትም መስቀል ስላለና በሚገባ አርፎ በደንብ ስለሚቀለብም ነው፡፡ ይህን ወቅት ለግርዘት የመረጡት፡፡ ‹‹ቦለዱ›› ሽለላ ማድረግም የተለመደ ነው፡፡ “ሱንጉ ኑጉኑ ሌጣ፣ ሌጣን ሳንሊ ለንዲገረሳ ጉንዲ ጉንጉሊ፣

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ጋቂቺ ኤረሻ ኢዩ ገንደሎ ጊልባ ሰማጋ ኡጋ ጐንዳኖ፣ ጎኒብኒን አጊ ገሊ አጐ ጉንት ኰሽማ ጡሙጋ"።

ይሄ ባል ወጣ ሲል ቤቱ የገባ ውሽማ ሚስቱን እያማገጠ እንዳለ ሲጠረጥር የሚለው ነው። የማይረባ ደካማ፣ ደበሎ ለብሶ የቁራን እሬሳ በትክሻው ላይ ተሸክሞ የእኔን የጀግናውን ቤት ደፍሮ ለማደር መጥቶ እቤት ተደብቋል። ብሎ የሚልበትና ከሚስቱ ጋር በምልልስ የሚወራረፉበት ነው። በዚህ ጊዜ፣

"ገርጂ ቆጳኑ፣ ከበር መለሉን፣ ቦዳ ኢጐኑ፣ ማጌሩ ጊደን አቤንዳ" ይላል፣ እውነትና እውሸት ዛሬ ካልለየለት የእኔ ወንድነት የዝንጀሮ ቂጥ መላጣ፣ (ጠባሳነት ነው) ይላል። ከዚያ በኋላ "ከሽንቹ ከበለቺ፣ ኰሽለቂ ጐታቲ፣ ኰሻ፣ ከሊኝ ኰለንቹ ጉቲስታ ጐታቲ" ይላል። "ከሊኝ፣ እንኩሎልታ ጉጂስ ጉበታቲ" ይላል። ትርጉሙም እዚያ ጓዳ ውስጥ እራቁቱን የተቀመጠ እንስራ አለ። እሱን ላልብሰው፣ ቅቤ ነው እሳት አምጪልኝ ወደጓዳ ልገባ፣ እሱን ላለብሰው ነው ይላታል።

እሷ ደግሞ በዚህን ጊዜ፦

ኰሻዬ አከሎሉት ቆይች ቡሪታ

ጉጂስ ዲባሜት አኒ ሜንቲቾታ

ጎጣን ጠቃ ፋሉ ጐንቺ ገበላንታክ

ጎለ ቆሉን ጡዱን ገፊ በርንጩማን ተክ

ባወራ መንኬራ ባዲ ዱሩ ቡኩሊ ቡቤን ሳራ ቆራንጬ

መማንቴን ዳገን ቀሌ። ትላለች።

ትርጉሙ እራቁቱን የተቀመጠው እንስራ ቅቤ ነው። ብርዱን (እርቅናውን) የምሸፈነው እኔ ሴቷ ነኝ። አንተ እዚሁ ሁን ወይም ጋጥህን እያየህ ጠብቅ፣ ከዚህ በተረፈ እስኪ አንዳንዴ እያወቅህ ሞኝ ሁን። ብላ ትነግረዋለች። ቀጥላም ለሡ የሚከተለውን ትመልስለታለች። ጓዳ ውስጥ ለተቀመጠው ውሽሜም ማለት ነው እንዲህ ትላለች።

‹‹ኩቺ ፉት ቢሊ ታንቲ በረንቶቲ አኩቡሉ፣ ከገጠ ኬ ሜሻን ኬ ኩሺቺ ሰርበ ፉል" ትላለች። ከዚያም "ጃሩ ከኤ፣ ጃሩ ከኤ" በማለት እሳት ታጠፋለች። ትረጓሜውም፣ እንግዲህ ይህን ያህል አስክጄሃለሁ እንግዲህ ዛሬ ተነስቶብኛል። ፈስህም ቢመጣ እንኳ ድምጽህን አጥፋ፣ ሳልም ቢመጣ አፍን፣ ትዋረዳለህ ቶሎ ብለህ ከጓዳዬ ውጣ በማለት መልዕክት ታስተላልፋለች። ውሽማዋም ከጓዳ እንዲወጣ በማሰብ ሆነ ብላ ውቃቢዬ

ተነስቶብኛል የሚል ሰበብ በመፍጠር እሳቱን ታጠፋዋለች። እየተንጕራደደችም ውቃቢዩ ተነስቶብኛል እያለች በማጓራት ባኟን፣ "ስሚታንጉን /ብላሺታን/ ጃሪ ኬኤ አማንተን ዬሀ ኢሳን ኬኤ ኢሳን ኪኤ" እንዳትነሳ፣ ወንድሞቼን የጨረሰ ዛር ነው፤ አርፈህ ቁጭ በል፣ ነገሬሃለሁ እያለች ስፍራውና በሩ በመሄድ ውሽማው እንዲወጣ ታደርጋለች። እሱ እርቃኑን ሲሮጥ፣ ‹‹ኢካን አፒፉል፣ ኢካን አፒ ፉል›› ምስህን እንካ፣ ምስህን እንካ በማለት ተከትላው እየሮጠች ልብሱን ትሰጠዋለች። በዚህ መልኩ ድራማዊ ትዋኔው ይተወናል።

ሀገረሰባዊ ዳንስ ሙዚቃውና ድራማው ሲተወን፣ የሚከተለውን ይመስላል። በግፋታ ‹‹ሁሮ ሁሮ ሆይ፣ ግፋቱ መላሉ ወገይ ሆይ-ዚዚም ቤቾ ጐ ---„ እያሉ እየተቀበሉ ጨዋታቸው በቡድን ሲሆን በቅብብሎሽ ከፊሉ ዜማውን ሲያወርድ ከፊሉ ይቀበላል። ሁሉም በእጆቻቸው ወገብ ለወገብ በመያያዝ በረድፍ በመቆም ይጫወታሉ። የድምፅ አወራረዳቸው ለስለስ እና ለዘብ የለ ነው። እንቅስቃሴያቸውም ከጉልበት በመጠኑ እስከ $45^0$ ድረስ አጠፍ በማድረግ ሲሆን ዝላይ አይታይበትም። በድምፆቻቸው የሚያወጧቸው ዜማዎችና ቅላፄዎቻቸው የሰውነታቸውን እንቅስቃሴ የሚመራው ጥበብ ነው። ከሙዚቃዊ መሳሪያ ይልቅም ይኸ ወጥ የሆነው ድምፃቸው ለትዋኔው ወሳኝነት አለው። ምክንያቱም ከድምፃቸው መለዋወጥ ጋር ተስተካክሎ ነው ውዝዋዜው የሚተወነው። በቪዲዮው ላይ እንደሚታየው ጨዋታዎቻቸው በጥቂት አባላት ወይም በበርካታ ተሳታፊዎች የሚተወን በመሆኑ የሰው ብዛት ብዙም ተፅእኖ የለውም። አፋዊ ጥበቡን /Verbal art/ ለመመልከት ከዘፈኖቹ አምስቱ ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1. ግፋታ

| | ተቀባይ |
|---|---|
| ሆሮ ሆሮ! (4) | ሆይ |
| ግፋቱ አንኔያ ወጋ ሆይ | ሆይ |
| ግፋቱ ከምባትያ ወጋ ሆያ | ሆይ |
| ዚ ---- ዘምቤቾጋ (4) | |
| ሆሎሎ ሆሎሎ ሆይ! | ሆይ |
| ሠጄ ቤቶ ሠሬዋናም ሆይ (2) | ሆይ |
| ሤሎ ባራን ሣእሊት ፍሪጦ ሆይ! | ሆይ |



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

| | |
|---|---|
| ዎግ ቤቶ ዎማንቾ ሆይ! | ሆይ |
| ዎዱ አኑክን ሄሳምቾ ሆይ! | ሆይ |
| ዚ ---- ዘምቤቾጋ (4) | |
| ጉፋማ ጉፊ ዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ጉፋንቾ ጉፋማ ጉፊዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ሆሮ ጉፋንቾ ጉፋማ ጉፊዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ሆሮ ጌዲን ዋኤም በእንዶ ዮ ሆይ! | ሆይ! |
| አሞ ዘራሮን ዋኤም በእንዶ ዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ሆሮ ዘምባቲን ዋኤም በእንዶ ዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ሆዮ ሆዮ ሆዮቤ ሆዮ ዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ዚ ---- ዘምቤቾጋ (4) | |
| አኔ አኔ አኔ አኔ ዬ ሆይ! (2) | |
| ሆሮ ሆሮ ጤአዮ በእንዶ ዮ ሆይ! | ሆይ! |
| መሳል ሱልሶች ሜጤ ቆጢሲዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ሱሱግ ሴሊች ሜጤ ጉቢሲ ዮ ሆይ! | ሆይ! |
| ዚ ---- ዘምቤቾጋ (4) | |
| ኮ ያአ መራም ፋሹ ኮሬኤ ዮ (2) | ሆይ! |
| ኮ ያአ መራም ቡላ ኮሬኤ ዮ | ሆይ! |
| ዚ ---- ዘምቤቾጋ (4) | |

## Gifaata የንብር ጨዋታ

| | ተቀባይ |
|---|---|
| በለው፣ በለው ሆይ! (4) | ሆይ! |
| ንብር የአባታችን ወግ ነው፣ | ሆይ! |
| ንብር የከምባታ ወግ ነው። | ሆይ! |
| ... እንደ እንዝርት (4) | |
| ሆ በለው፣ ሆ በለው ሆይ! (4) | ሆይ! |
| የሠላሣው የመስተዳድር ክፍሎች የመሪ ልጅ ባለመሣሪያ፣ | ሆይ! |
| በ‹‹ሜሎ›› ፈረስ ተቀምጠህ ሂድ ለግልቢያ። | ሆይ! |
| የወግ ልጅ ጨዋ ነው፣ | ሆይ! |

ቀድሞም አባትህ ባለታሪክ ነው፡፡ ሆይ!

--- እንደ እንዝርት (4)

መዝፈኑን ዝፈን ሆይ! ሆይ!

ዘፋኝ፣ መዝፈኑን ዝፈን ሆይ! ሆይ!

በለው ዘፋኝ፣ መዝፈኑ ዝፈን ሆይ! ሆይ!

በለው በግድ መጥተን የለም ወይ? ሆይ! ሆይ!

እማ አበባ ይዘን መጥተን የለም ወይ? ሆይ! ሆይ!

በለው ዘንባባ ይዘን መጥተን የለም ወይ? ሆይ! ሆይ!

በለው፣ በል በለው፣ በለው በል በለው ሆይ! ሆይ!

------------ እንደ እንዝርት (4)

ወይኔ፣ ወይኔ፣ ወይኔ፣ ወይኔ፣ ሆይ! ሆይ!

በለው፣ በለው ጨዋታው እያማረ አይደለም ወይ? ሆይ! ሆይ!

ከመስቀል ክትፎ አንዴ አጉርሽኝ ሆይ! ሆይ!

ከሀይለኛ ቦርዴ አንዴ ፉት በይልኝ ሆይ! ሆይ!

------------ እንደ እንዝርት (4)

ወደ ስብሰባ እሄዳለሁ ፈረስ ጫንልኝ፣ ሆይ!

ወደ ስብሰባ እሄዳለሁ በቅሎ ጫንልኝ፣ ሆይ!

------------ እንደ እንዝርት (4)

## 2. ሆሌ ሆሌ

ተቀባይ

ሆሌ ሆሌ ያሆ! (4) ---------------------------------------------------- ያሆ

ዎጌ መሰላ ያሆ! ------------------------------------------------- ያሆ

ኤመን ዋልትኔ ያሆ!------------------------------------------------------ ያሆ

ማኒ ግዚ ምሸረቻ /መሳሉ ዋሎ ------------------------------------------ ያሆ

ማጠ ጉሙ ጉንጁት /ህግያን ሜኩ አሪቱ ፉሎ------------------------ ያሆ

ሃሮ ዎጉ ዱቢ /ጡሚ ኢታ ------------------------------------------- ያሆ

ዊማ በጅጉ ደላ /እሁን ኔሣ ሁንዲንከኔ ------------------------------ ያሆ

ሆሌ ሆሌ ያሆ (4) ------------------------------------ ያሆ

በሬ አሪቾ ቦብራ መጠቅስ ---------------------------------------------- ያሆ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ባቀ አገንቾ /ቱንሱታ ጫክስ ---------------------------------------------- ያሆ

ባድኔ ጐማ /ጤና አንሽስ ---------------------------------------------- ያሆ

አንሽቾ ጤና /ኡለታ ሙጥስ ---------------------------------------------- ያሆ

ኢልን እንቱንታ /አቶቲን ደቀንስ ---------------------------------------- ያሆ

አንጋ ለሜን /ሆናንጋ በራትስ ------------------------------------------ ያሆ

መሰላ ገሬ /ምጌ አያና ------------------------------------------------ ያሆ

መሪሾ ገዳ /ዱቢ. ምጠና ---------------------------------------------- ያሆ

ሆሌ ሆሌ ያሆ ያሆ (4) -------------------------------- ያሆ

## Hollee - እፈሡ

እፈሱ፣ እፈሱ (4) ------------------------------------------------------ ያሆ

የዐውደ ዓመት መስቀል እንኳን መጣ፣ ------------------------------ ያሆ

ለሰዎችና ለእንስሳት የምሥራች መስቀል መጣ፣ --------------------- ያሆ

ክረምት፣ ዳመናና ጭጋግ አልፎ ብሩህ ፀሐይ ወጣ። ---------------- ያሆ

አዲሡ ዓመት የሀብት፣ የሠላምና የፍቅር ይሁንል፣ ---------------- ያሆ

ሙሉ የደስታ ዘመን ይሁን - ለሁላችን። ---------------------------- ያሆ

------------------- እፈሡ፣እፈሡ፣ (4)

የፀሐይ ብርሃን አየርን አኩራራ፣ ------------------------------------ ያሆ

ብሩህ ጨረቃ ጨለማን አብራ። ---------------------------------------- ያሆ

የአገራችን ዳመና ዝናምን ምቹ አድርግ፣ ----------------------------- ያሆ

ምቹ ዝናም መሬትን ታደግ። ----------------------------------------- ያሆ

ደርሰን እንድንበላ ከምርት አገናኘን፣ ------------------------------- ያሆ

በሁለት እጃችን እንድናፍሰው አበራክትልን። ------------------------- ያሆ

መስቀል እውነተኛ በዓል የዐውድ ዓመት፣ --------------------------- ያሆ

ደመራው የፍስሃና የሀብት ሥኬት። ------------------------------------ ያሆ

እፈሱ፣ እፈሱ (4)

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 3. ኤነሬ

ምስል 7 ኤነሬ



ኤነሬ ግግሸ (5)

መሣል ምሽራቻ መን መጫን ሀሻሽ፡፡

በድኔ ሠማን ቡርይ በሪ ጪቾ፣

በጅጐ አያኒ ምሽራቻ ምናደቢ ኩላንቾ፣

ሆ! ይ ፋል መሪሾን ገዱ ጉፌ ግፋቾ

ሀንጠዙ አንጄእ አደሉ ዘራሮ ፊቾ፣

ማንደሪያ መሣላ መ ዘቾዳ ኩ ማሉ፣

መኑ አፎ ሼማች ዎጊን እቿ ሜሼሉ፡፡

### ትርጉም

የመስቀል ወፍ ሆይ ላባሽን አርገብግቢ (5)

በአገራችን ሰማይ የባህርማዶ ወፍ ብረሪ፣

የደስታን በዓል የምሥራች ለማህበረሰቡ ንገሪ፡፡

ሆ! ብለሽ ውጪ ሕዝቡ ደመራ ዘፈነ፣ ጎብር ተጫወተ፣

አደይ አበባ ፈካ፣ አበበ፣ ከሴ ጥሩ መዓዛ ሸተተ፡፡

የወግ መስቀል ነው - ምን ቢከሣ ሥጋው፣

ሰዎች ሠንጋ አርደው - ተከፋፍለው የበሉት ሥጋ ጮማ ነው፡፡

## 4. ጐሪታ ጡጄ

| | ተቀባይ |
|---|---|
| አና ኤመን ሀሹ እልት በልጥት ኬዕምት፣ ------------------------------ | ጐርታ ጡጅዬ |
| አገኖት ጐሬ ላሉታ ኢልት፡፡ ----------------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| ኢማ እልሌስ አትን አቅ በጅጉታ፣ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| ኤመን ኢልት ጡድ አስክ በጅጉታ፣ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| አባ ኤመን ሀሹ ጐርታ ጡጅ ዬ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| አና ኤመን ሀሹ ጐርታ ጡጅ ዬ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| ኢማ ኤመን ሀሹ ጐርታ ጡጅ ዬ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| ቦኮ ኤመን ሀሹ ጐርታ ጡጅ ዬ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| አና ኢመን ሀሹ ጐርታ ጡጅ ዬ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |
| ኢማ ኤመን ሀሹ ጐርታ ጡጅ ዬ ------------------------------------- | ጐርታ ጡጅዬ |

አገኖቱ አብኑ ሆሪችን ብርት ------------------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

እሌን ጐሪታ ኢሿ ሄሉ በጅጉት------------------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

ቦሎቹ ጐሪታ ሸለት ሻምታ ------------------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

ብርዕኔ ዘኩዕኔ ፊታ ላሉታ ------------------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

እልት እይት አንሰት ቀንሶት ------------------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

እትስ አግስ ሀንቀፍ አንሸት ------------------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

ሌዕሰ ኢማ ኩን በጅጉታ ------------------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

እሌን ጐሪታ ኢሉ ዊጤን ላሉታ እቷ ------------------------------------ ጐርታ ጡጅዬ

አና ኤመን ሀሹ (4)

አባ ኤመን ሀሹ (4)

ትርጉም

ለወግ ለማዕረግ ድረሱ!

አባት፣ እንኳን ወልደህ ኮራህ፣ ከበርክ፣
ለሐሴት፣ ወግ፣ ፍሬ ደረስክ፡፡
እናት፣ እልል በዩ አንቺው ተቀበይ ይህንን ደስታ፣
እንኳን ወልደሽ አዩሽ የልጆችሽን ደስታ፡፡

አባ፣ እንኳን ለወግ ለማዕረግ ደረሱ!
አባት፣ እንኳን ለወግ ለማዕረግ ደረሱ!
እናት፣ እንኳን ለወግ ለማዕረግ ደረሱ!
ቤተሰብ፣ እንኳን ለወግ ለማዕረግ ደረሳችሁ፡፡

ሀሴትና ክብር ከሁሉም ነገር ቀዳሚ ነው፣
ወልደው ለወግ መድረስ ተድላና ደስታ ነው፣
ሠርግ ወግ ነው - ባህላዊ ጨዋታም ምቹ ነው፣
ዙሪያችን በሙሉ አበባና ፍሬ ነው፡፡
ወልዳ፣ ተሸክማ፣ አግታና አጥብታ
አብልታ፣ አጠጥታ፣ አቅፋና አጥባ
ላሣዳገችው እናት ይህ ደስታ ነው፣
ወልደው ለወግ መድረስ ዘርተው ፍሬ እንደመብላት ነው፡፡

እናት፣ እንኳን ደስ አለዎት (4)

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አባት፣ እንኳን ደስ አለዎት (4)

### 5. ባሊ ሄሌሌ

ባሊ ሄሌሌ (2)
ዊማን ጤአን ምርት ጬንቁሌ
ዋጆ ቡሪን አቅ ምሶሌ
ባሊ ሄሌሌ ምጌ መሳሌ
በሬን ክት ሤሉ ምንሾ ጡቅሌ ቆጥት ቁርጨእ ቆንጥ ፊትሌ
… ባሊ ሄሌሌ (4)

### ትርጉም

### የበዓል ንግስት

የበዓል ንግስት (2)
ከሞላውና ከጐደለው ቀድተሽ ጨልጪ፣
(የቅቤ እቁብ) ከማህበር ቅቤ ወስደሽ ጠጪ፡፡
የበዓል ንግስት የመስቀል የዐውደ ዓመት፣
ቀን ቦርዴ አጠልዩ በወንጠፍት፣
ከቆጥ ጋር ታረቂ የዋልታ ሽመሊት፣
ጐርሠሽ ዋጪ የቋንጣ ምንቸት፡፡
የበዓል ንግስት (2)

### 6. WEESITA - ዌስታ እንሰት

ዌሴ፣ ዌሴ፣ ዌሴ፣ ሠናን ሹኔኖስ፣
ሠሤ ቀረፌኖሴ፣ ጐሩ ቡቲች በዕሴ፣

ሃጊ መጤ ዌሴ፣ ለሊ መኒ ዌሴ፡፡
ሃላንቹክ ማረባ፣ ቦርክቹክ ምንጣፉ፣
ምደርቹክ ሙስማራ፡፡
ቡዕሊን ሜሬሪኒ፣ ጐጆን ቀጠናኒ፣




ምስል 8 የቃል ግጥም መነባንብ በአቶ ደስታ ሲቀርብ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ገቴ አሱሳኒ፣ ገሌ ሸሜሲኒ ጮጳሩ ሾሌናን፣
ሠእ በቆ ቡዲን፣ ጨበሬማ ሞቆን፣
ጠቃኤን ቆጤኖዳ፣ ሠሞች ስነጣ ኢልት፣ ግድሴ ዌሴ፡፡
ቆጥት ኢንጩእ ከምባት ኦሶ፣ ቀሠክ በዕቀኡን፣
ዬን ህትታ እሄኖሴ፣
ኢንጫ ኤመዳ አሊች ቢለኖ፣ ፈይመቲ ደገንታ፡፡
ዌስት ኪሣምታ፣ ማንደሪን በህሩታ፣
ማጠቅት ሆጉምቡታ፣ መጠ አጐ ዎአ ዘከቲቲ ማጣታ፣
ዘከቲቲ አገናን፣ ሆረን ሠገቡምቡታ፣
ለመላ ዎጌ ሞሊ፣ አንገታ አቱምቡታ፣
ዘኒኒ ካቢኒ፣ ቆረበንት ሄአታ፣
አራትቹ ዎቆማ፣ ኣዚንተሴ ፋሉ ሃዕይቱምቡታ፣
መን ቦክ ከልቲን፣ ቀሱ ኢትቱምቡታ፡፡
ገትታ ገፊሪች፣ ገጉሜን ያርታታ፣
አንገታ ሎከታ፣ ኪሲንን ዮታ፣
ቄስ ዌቴችጋ፣ ዊሊሌን ሌአታ፡፡

## ትርጉም[23]

እንሰት

እንሰት፣ እንሰት፣ እንሰት፣ በሰኔ ይኰተኰታል፣
ሦስቴ ቅጠሏን ቆርጠው ይመለምሏታል፣
ረሃብን ከአገር አጥፊ ነሽ፣
ለበጋና ክረምት፣ ለከብትና ሰው ጠቃሚ ነሽ፣
ከደረቁ ግንድሽ የሚዘጋጀው ‹‹ሐለሞ›› መሐረብ ነው፣
ቅርንጫፍሽ ‹‹ቦርኬ›› ምንጣፍ ነው
ወደሮሽ (ገመድሽ) ምስማር ነው፡፡
በቡዕላ፣ ከልዩና ከከረመ ቆጮ በተዘጋጀው፣
በጐመንና በብስል ከራሚ ቅቤ (ጐመን በቅቤ) ‹‹ጮጳሮ›› ሠርተው፣

---

[23] ትርጉም በወርቁ ጊጆባ

ከላም ቀንድ በተሠራው ማንኪያ አንሥተው ሲጉርሡ፣
ከአናት እስከ ተረከዝ ድረስ በእርካታ ይራሡ፡፡
ጉረሳችሁ ተንጠራሩ የከምባታ ልጆች፣ ውጋታችሁ ይወገድ፣
ብለው እንደዚህ ይሆኑላታል -- በግድ፣
ሲንጠራሩ ለሰውነት ይቀላል - ጤናም ይገኛል በልምምድ፡፡
እንሰት ባለኪስ ናት፣ በማእረግም የበኩር ነች፤
ስታጠራቅም አይታወቅባትም፣ በክረምት ወደ አካሏ የገባውን ውሃ ለበጋ ትደብቃለች
በየካቲት ወር (በበጋ) ጭራሽ አትጠማም፣
ላሠባት ዓመት ድርቅ እጇን አትሠጥም፡፡
በደንና በካብ ተጠብቃ ትኖራለች ሁሌም፣
መንገድ በማሳዋ ውስጥ እንዲወጣ አትሻም፣
በሌላ ቤተሰብ መጥረቢያ ማሳዋ እንዲኰተኰት አትወድም፡፡
ጓሮን ከመልቀቅ እራስዋ ትጮኻለች፣
እጅና እግሯ ኪስ ያላት ነች፣
እንደ አይብ ማጥንት በጭስ ታዳጊ ነች፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት ግፋታ፣ ኤኔሬ፣ ሆሌ እና ባሊ ሄሌሌ በከምባታ ብሔረሰብ እጅግ የታወቁና የተወደዱ ዜማዎቻቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ዜማዎች በሙሉ ማለት ይቻላል በቅብብሎሽ የሚተወኑ፣ እርስ በእርሳቸው በመያያዝ፣ ወንዶች ከወንዶች፣ ሴቶች ከሴቶች በተቃራኒ አቅጣጫ በረድፍ በመቆም የሚጫወታቸው፣ ቅብብሎሹ በተመሳሳይ ቅርፅ የሚቀጥል - ወጥ መሆናቸው ከጥናቱ ይታያል፡፡ በባህላዊው የከምባቶች የሙዚቃ መሳሪያ ከበሮ (ቀርቤታ) እየታጀበ እና ከተዋኞቹ ተፈጥሯዊ ድምፅ ብቻ በሚወጣው ዜማ እየታጀበ እና እየተመራ መቅረቡም ትወናውን የተለየ ያደርገዋል፡፡ ዳንሳዊ እንቅስቃሴው በአጠቃላይ ማለት ይቻላል በሙዚቃዊው ዜማ ቅንብር ላይ የሚደገፍ ነው፡፡

ይህ በአንድ በኩል ዜማ ከድምፅ ጋር የተያያዘ መሆኑን ሲያመለክት በተጨማሪም ጆሮገብ ድምፅ በእንቅስቃሴ የሚደገፍ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በሌላም በኩል ሙዚቃ ለድራማም ሆነ ለዳንሱ የሚያበረክተውን የማይናቅ አስተዋፅኦ ወይም የእርስ በርስ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ዝምድና ይመሰክራል። የእነዚህ ሦስት ጥበቦች ግንኙነት በሚከተለው መንገድ ይገለፃል። የከምባታ ህገረሰብ ትውን ጥበባት በዳንሱ፣ በሙዚቃው እና በድራማው እንደሚታየው በሁለት መሠረታዊ ዓላማዎች የሚተወኑ ናቸው። እነዚህንም ለሃይማኖታዊ እና ለመዝናኛ ብለን መፈረጅ እንችላለን። ለሃይማኖታዊ ተግባር የምንላቸው እንደ ግፋታ፣ ኤኔሬ የመሳሰሉት ሲሆኑ በምልልስ የሚቀርቡት፣ በመነባንብ መልክ የሚተወኑት ‹‹ቦለዱ›› የመሳሰሉት ደግሞ ተዝናኖታዊ ናቸው። ሃይማኖታዊ ዓላማ ይዘው የሚተወኑት መጠነኛ ገደብ ቢኖራቸውም ለቅዳሴያዊ ስርዓቱ ሲባሉ የሚዜሙ ናቸው። ተዝናኖታዊ ዓላማቸው የጐላ አይሆንም። ለተዝናኖት ሲባሉ የሚዜሙትን ከተመለከትን ግን በሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅበው በአብዛኛው ለማዝናኛነት ተግባር ሲባል የሚቀርቡ ናቸው። ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ዜማቸው ረገብ፣ ለስለስ ያለ፣ ሲሆን ተዝናኖታዊ የሆኑትን ስንመለከት ግን ፈጠን የማለት ባህሪይ ይታይባቸዋል። እንቅስቃሴያቸውም በተመሳሳይ ስልት የተቃኘ ነው። በከምባታ የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸውን በተለይ ከበሮዎቻቸውን የሚጫወቷቸው ፉጋዎች መሆናቸው፣ እነዚህ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውም ሆኑ ሌሎች ከበሮዎቹ ከሃይማኖታዊው ስርዓት በኘሮቴስታንቶቹ ዘንድ እንዲገለሉ እና እንዳይቀላቀሉ መደረጉ በእንቅስቃሴው የሚኖራቸው አሉታዊ ተፅእኖ የዚህ አረጋጋጭ ነው። በህዘን ስርዓቶቻቸው ላይም እነዚሁ ሰዎችና ከበሮዎቻቸው ተፈልገው ስርዓቱን እንዲያደምቁ ይደረጋሉ። ይህም ስሜቶቻቸውን ያለገደብ እንዲያወጡ ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ ከፉጋዎቹ ጋር አብረው በአንድ (በተመሳሳይ) ዕቃ እንኳን እንዲመገቡ አይደረግም። ለትዋኔው ግን ይፈለጋሉ። ህገረሰባዊ ትወናዎቹን ለመተወን እውነተኞቹን ተዋኞች መፈለግ፣ ያለ እነሱም ሊሆን ሊሳካም እንደማይችል በከምባቶች ዘንድ በሚገባ የታወቀ ነው። የፉጋዎቹ ልዩ ችሎታ ለዚህ ሲባል ይፈለጋል።

Bauman እንደሚለው ትወና ጥበባዊ ድርጊትን እና ፎክሎራዊ ትግበራን የሚያመለክት ነው። ትዋኔያዊ ሁኔታው ተዋኙን፣ ጥበባዊውን ቅርፅ፣ ታዳሚ፣ እና መቼትን ይሻል። እነዚህ ላይ ነው ትወናው የሚያደራው።[24] ከላይ በቀረቡት የከምባታ ብሔረሰብ አራት ዜማዎች ላይ እነዚህ ይስተዋላሉ። በዜማዎቹ ውስጥ የተሰደሩት ቃላት ከሚባሉበት

[24] Bauman, 1984, 4 — The term performance has been used to convey a dual sense of artistic action the doing of folklore-and artistic event-the performance situation, involving performer, art form, audience and setting-both of which are basis to develop performance approach.



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አጋጣሚ ይልቅ በውስጣቸው ያዘሉት ፍቺ እምቅነት፣ ቀልዳዊ ባህሪ ያላቸው የሚመስሉት ምልልሶችም ከድራማዊ ባህሪያቸው ባሻገር በውስጣቸው ያገቱቱ ሴሰኝነትን የመኰነን፣ ባእድ አምልኮን፣ ከባእድ መናፍስት ጋር በተያያዘ የህብረተሰቡን እምነትና አመለካከት፣ እንዲሁም የኑሮውን ፍልስፍና የሚያመለክቱት ድብቅ መልእክቶች ከማዝናናቱ ባለፈ የሚታዩ ናቸው። ምስላ፣ እና ትርጓሜ አሰጣጣቸውንም ስንመለከት ለትወናው ከሚሰጡት ውበት ባለፈ በውስጣቸው ያለውን ሀሳብ ጥልቅነት አመላካች ናቸው። ተዋኙ በተፈጠሮው በተቸረው ችሎታ፣ ጥበባዊ ፋይዳ የላቸውን ትውኖች ሲተውን፣ ታዳሚው አድምጦ፣ ሲያጣጥም፣ ተቀብሎ ሲያስተጋባ፣ ተመልክቶ ሲጫወት፣ በተፈጥሯዊ መቼት ሲተውንም መመልከት ይቻላል። ይህ ከጥናቱ አባሪነት በድምፅና በምስል ተደግፎ ቀርቧል።

በሌላም በኩል Bauman የትወና ቁልፍ ነገሮች ናቸው የሚላቸውን ልዩ ኮድ፣ ዘይቤያዊ የቋንቋ አጠቃቀም፣ አቻዊ ቅንብር፣ የተለዩ ስነልሳናዊ ቅርፆች፣ ልዩ ቀመሮች፣ ልማዳዊነት እና የተመሳሰሉትን[25] አያይዘን መመልከት እንችላለን።

ለምሳሌ ልዩ ኮድ ለሚለው ውሽማን ከእንስራ ጋር አመሳስለው በምልልሳቸው የተጠቀሙበትን ሂደት፣ ኤኔሬ የተሰኘውን የመስቀል ወፍ የምትሰጠው የመልካም ዘመን፣ ጊዜ አብሳሪ ትእምርትነቷ፣ በዜማ የሚቀርቡት ግጥሞች በሀረግ፣ ተመጣጣኝ (አቻዊ) ቅርፃቸው ድግግሞሹ የመሳሰሉትን ሁሉ ማንሳት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ በመነባንብ መልክ የቀረበውን እና ስለ እንስት ታሪክ እና ጠቀሜታ የሚተርከውን የአቶ ደስታን መነባንብ ከገጽ 51 ላይ መመልከት ይቻላል።

ግጥሙ በዜማው፣ ስለ እንስት በሚሰጠው ዝርዝር እና ገጣሚው በቃሉ የሚያነበንበው በመሆኑ የገጣሚውን ጥበባዊ የአተዋወን ብቃት ያመለክታል። ይህ ከ30 ደቂቃዎች በላይ የሚፈጀው ግጥም የቀረበው በቃል ነው። ገጣሚውም አይነስውር ከመሆኑ በተጨማሪ በግብርና የሚተዳደር እና ያለ ክፍያ ሰዎች በተሰበሰቡበት የሚያነበንብ የቃል ግጥም ገጣሚ ነው። በግጥሙ ውስጥ እንሰት ለከምባቶቹ የሚሰጠው ጠቀሜታ በንፅፅር ቀርቧል። እንሰትን ከብስማር፣ ከማሃረብ፣ ከልብስ፣ ከምንጣፍ እና ከሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ካሏቸው ነገሮች ጋር እያነፃፀረ በዘይቤያዊ መልኩ ያቀረበ ቃላዊ ትዋኔ

[25] Bauman, 1984፣ 16-17

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ነው። በዚህ ቃላዊ ትዋኔ የተዋኙ እንቅስቃሴ፣ የቃላት ማቀናበር ችሎታውንና፣ ታዳሚዎቹን ከማስደመሙ ባሻገር የሚያስጨብጣቸውም ቁምነገሮችን በቃል ትዋኔውን ያስተላልፋል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተገለጸዉ የከምባታ ብሔረሰብ ሙዚቃ፣ ዳንስ፣ ድራማና በምልልስ መልክ የቀረቡት ቃላዊ ትወናዎች ሁሉ የሚያመሳስሉቸው ነጥቦች አሉ። የመጀመሪያው ሁሉም ማለት ይቻላል በዜማ ታጅበው የሚቀርቡ፣ ዜማዊ ቅላፄም የተላበሱ ሆነው ይታያሉ። ሁሉም ማለት ይቻላል በአካላዊ እንቅስቃሴ ታጅበው የሚቀርቡ እንጂ እንቅስቃሴ አልባዎች አይደሉም። በሦስተኛው ደረጃ ከተመለከትን ደግሞ ህብር የተላበሱና በቅብብሎሽ መልክ የሚቀርቡቱ የሚበዙ ሲሆን፣ በተናጠል ወይም በአንድ ተዋኝና በሌሎች ተቀባዮች አጀብ የሚቀርብ ትውን ጥበብ በከምባታ እምብዛም አለመገኘቱ ነው።

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ሦስቱም የህገረሰብ ትውን ጥበባት አተዋወን በተመሳሳይ መልኩ ከወገብ በላይ ባሉት የሰውነት ክፍሎች እንቅስቃሴ መተወናቸው በአብዛኛው የሚያመሳስሉቸው ነጥቦች ናቸው። በሁሉም አተዋወኖች ላይ የሚስተዋለው ሌላው ነጥብ የከምባቶቹ የተፈጥሮ ድምፅ በትወናው ከፍተኛ ስፍራ መያዙ ነው። ከነዚህ አምስት ነጥቦች በተጨማሪ ሙዚቃዎቻቸውን ሲጫወቷቸው፣ ዳንሳቸውንም ሲያቀርቡ ሆነ በምልልስ የተሞሉ ድራማዊ ትውኖችን ሲተውኑ እንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ በክብ መልክ ወይም በዙር መልክ የሚተወኑ ሆነው መገኘታቸው የተለየ ፀባያቸው ሆኖ ተገኝቷል። ግፋታን ሲጫወቱት ወገብ ለወገብ ተያይዘው፣ ወንዶቹ በአንድ በኩል ግማሽ ክብ ሰርተው ሲሆን ሴቶቹ ደግሞ ከፊት ለፊታቸው ወገብ ለወገብ ተያይዘው ሌላ ግማሽ ክብ ሰርተው ነው። ይሄ የተለየ ባህሪው ነው። በኢኔሬ ጨዋታ ላይም በረድፍ ወይም በመስመር ተጠጋግተው በመቆም እጆቻቸውን ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ በመዘርጋት፣ ወደ ላይና ወደ ታች እያፈራረቁ በማወዛወዝ ልክ በአየር ላይ እንደምትንሳፈፍ ወፍ በማንዣበብ መልክ ነው የሚተውኑት። ይህም ያንኑ የክብነት ባህሪ ሳይለቅ መሆኑ በጥናቱ ወቅት ታይቷል። ባሌ ሄሌሌ የሚባለውን ጨዋታ ሲጫወቱትም በተመሳሳይ መልኩ በመያያዝ፣ በረድፍ ፊትና ኋላ በመከታተልና ዙር በመስራት ነው። በዚህም ልዩነት አልታየም። ከነዚህ ምሳሌዎች በመነሳት የከምባታ ብሔረሰብ ባህላዊና ሃገረሰባዊ ትወና በቅርጹ ክባዊ ነው ማለት ይቻላል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

በአጠቃላይ የከምባቶቹ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መከሰቻ ፀዋትው (genres) አስመልክቶ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው አንዱ በአንዱ ወይም አንዱ ከአንደኛው ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ነው። ሙዚቃው በዳንሱ ይታገዛል፣ ይተወናልም። ዳንሱም በድራማዊ ትእይንቶች ሊተወን ይችላል። ስለዚህ ብቻ ብቻቸውን የቆሙ ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው ተደጋጋፊነት አላቸው ማለት ነው። ከዚህ አንፃር በከምባቶቹ ዘንድ የሚበዛው የሙዚቃዊ ድራማ መልክ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በአጠቃላይ ሲታዩ የሚከተሉት ማህበራዊ ተግባራት አሏቸው። በምዕራፍ አራት ውስጥ እንደታየው በመጀመሪያ ስለብሔረሰቡ ባህል መረጃ ከመስጠት ባሻገር የባህሉን ዝርዝር ገፅታዎች መረጃ ይሰጣሉ። የብሔረሰቡን አኗኗር፣ ማህበራዊ ህይወት፣ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ምኞቱን ተስፋውን፣ ቁጭቱን ወዘተ. ያሳያሉ። በሁለተኛ ደረጃም ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ልማዳዊ ስርዓቱን፣ ዋጋ የተሰጣቸውን እሴቶቻቸውንም ይገልፃሉ። ምን ያመልካሉ፣ ለምን ያመልካሉ፣ ምን ያከብራሉ፣ ለምን ያከብራሉ፣ እንዴት ያከብራሉ፣ ለእያንዳንዱ ባህላዊ ቅርስ የሰጡትን ዋጋ እና ከበሬታም የማመልከት ችሎታ አላቸው። በሦስትኛ ደረጃም ህፃናቱን፣ ለባህሉ አዲስ የሆኑና ባህሉን ተቀብለው ለመኖር ለተስማሙ መጤ ወገኖችም የብሔረሰቡን ታሪክ፣ አመጣጥ፣ አኗኗር፣ የማህበራዊ ኑሮ መሰረቶቻቸውን፣ መልካምና ክፉ ተግባራት የሚሏቸውን ሁሉ ለማስተማር ይጠቅማሉ። የስነምግባር ደንቦችንና ግብረገባዊነትን ያስተምሩባቸዋል።

የተጣላ የሚያስታርቁበት፣ የወደደን የሚያጣምሩበት፣ ያጠፋን የሚቀጡበት፣ የተሳሳተን የሚመልሱበት የራሳቸውን ስጋዊም ሆነ መንፈሳዊ መርሆዎች መስበኪያም ናቸው። ታዋቂ ጀግኖቻቸውን በመጥራት እንዳይረሱ የሚያደርጉበት፣ የተጋድሎ ታሪካቸውን በማውሳት አደራ ተረካቢዎች ሆነው እንዲቀጥሉ የሚመክሩበት፣ የቁጥር ስሌት፣ የእርሻ ጥበብ፣ የእጅ ሙያ፣ የጠንካራነትን ምስጢር፣ ወዘተ. ይማማሩባቸዋል። አታላይነትን፣ ኢተዓማኒነት፣ ስንፍናን፣ ንፉግነትን ወዘተ. እያነሱ በትውን ጥበባቱ አማካኝነት ለመስበክም ይጠቀሙባቸዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የከምባታ ብሔረሰብ በቀደመው ዘመን የፈጠራቸውና ጠብቆ ለማቆየት የሞከራቸው የሀገረሰብ ዳንስ፣ የሀገረሰብ ሙዚቃ፣ እና ልዩ ልዩ ልማዶቹ የህልውናቸው አሻራ የተመሰረተው በትዋኔዎቻቸው ላይ ነው፡፡ ህዝቡ ዘፈኖቹን ሲዘፍን፣ አንዳንድ ትእይንቶችን ሲተውን እንደታየው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያቸው በሆነው በከበሮ በመታገዝ፣ የሀገረሰብ ልብሱን ወይንም ዘወትራዊ ልብሱን ለብሶ ሲጫወት የጥንቱን የውዝዋዜ ስልቱን ላለመልቀቅ ተጠንቅቆ ነው፡፡ የመልእክቶቹ ይዘት ከየወቅቱ ሁኔታ፣ ከፖለቲካው፣ ከኢኮኖሚያዊው፣ ከማህበራዊው እሴቶቹ ጋር እንዲጠጣሙ ለማድረግ ቢሞከርም የውዝዋዜና የትወናውም ስልቱ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡

ይህ የሆነውም በትዋኔያቸው አማካይነት ባህሉን ለማስረፅ በመሞከራቸው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የትውን ጥበባቱ ሌላኛው ተግባር ይህ ባህልን የማስረፅ ተልእኮ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ቀጥለን ደግሞ ከሃይማኖታዊ ሰርዓቶችና ከልማዶች አንፃር ትወና ምን መልክ እንዳለው እንመልከት፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ሀገረሰባዊ ትወና በልዩ ልዩ ሃይማኖቶች፣ ልማዶችና ስርዓቶች

ይህ ምዕራፍ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱን ከልዩ ልዩ ልማዶችና ስርዓቶች አንፃር ያቀርባል፡፡ሀገረሰባዊ ትወና በልዩ ልዩ መንገዶች ሊከሰት ይችላል:: ይህንን አስመልክተው ከተሰነዘሩት ምሑራዊ አስተያየቶች ውስጥ ሙያው ልዩ ልዩ የሃይማኖት ስርዓቶችን ለምሳሌ የመስቀል ስርዓት፣ የልጆች ጨዋታዎችን፣ የለቅሶና የሠርግ ስነስርዓቶች፣ ... ከህፃናት ጨዋታዎች፣ ከልደት፣ ከግዝረት፣ ከሰርግ ... ወዘተ.[26] ጋር የያንዳንዳቸው የተናጥል ባህርይ እና የጋራ ጉዳይ እያነሱ ማጥናት እንደሚቻል የሚዘረዝረው የፈቃደ ገለፃ ይጠቅሳል::

ይህንኑ መሠረት በማድረግም በዚህ ክፍል ሀገር በቀል ሃይማኖትና ትወና፣ ታሪካዊ ሃይማኖትና ትወና፣ የህፃናት ጨዋታዎችና ትወና፣ የልደት፣ የግርዘት፣ የሠርግ፣ የለቅሶ ወቅት አተዋወኖችን ቀጥለን እንመለከታለን::

### 5.1 ፀዋትወ ሃይማኖት

ሃይማኖት በተወሰኑ እምነቶችና አስተሳሰቦች፣ ላይ የሚመሰረት፣ በአንድ ቁስ፣ ሰው፣ በማይታይ ፍጥረት፣ ልዕለ ተፈጥሮ በሆነ አንዳች ኃይል፣ የተቀደሰ ወይም መለኮታዊ ነው በሚባል ነገር፣ ላይ እምነትን ማሳደር እና በተወሰኑ የሥነ ምግባር መርሆዎች፣ ልምዶች፣ እሴቶች፣ ተቋማት፣ ልማዶች እና ከእምነቱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ልዩ ልዩ ስርዓቶች የሚመራ ነው:: በመሆኑም ስለ ጽንሰ ሀሳቡ መሠረታዊ ነገሮችንና ለዚህ ጥናት በሚያመች መልኩ ገለፃ ለመስጠትም እንዲቻል በመጠኑ ዘርዘር አድርጐ ማየቱ ተገቢ ስለሚመስል ቀጥሎ ቀርቧል::

ከጥንት ጀምሮ ሃይማኖትን ለመበየን የተሞከረ ሲሆን አብዛኞቹ ብያኔዎች በአንድ በኩል ቁርጥ ያለ ብያኔ ላለመስጠት፣ በሌላ መልኩም በአጠቃላይ ፍቺውን በማመልከት ላይ የተወሰኑ ናቸው:: ጥቂቶቹ ቀመራዊ፣ ቀኖናዊ ብያኔዎችን ሲጠቀሙ፣ ሌሎች ደግሞ ስሜትን የሚነካ፣ ከአስተውሎት እና ከግብረገባዊ ባህርያቱ አንፃር ለመበየን የሚሞከሩ ናቸው:: የስነ ህብረተሰብ እና የስነ ሰብ አጥኚዎች ደግሞ ሃይማኖትን ባህል

---

[26] ፈቃደ፣ 1991፣ 12-13

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

እንዳዳበራቸው ረቂቅ የሃሳብ ክምችቶች፣ እሴቶች፣ ወይም ልምዶች አድርገው ይቆጥሯቸዋል::

በአጠቃላይ፣ በሁሉም ደረጃዎች፣ በሚታወቁ ባህሎች ሁሉ ሃይማኖትን አስመልክተው የተሰጡት ብየኤዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ያረጋገጡት ህያዋንን ሁሉ ወደ መኖር ያመጣቸውና የመተዳዳሪያ ስርዓትን ያበጀላቸው አንድ ልእለ ኃይል መኖሩን ነው:: ይብዛም ይነስም አንድ ባህል ለባህርይ ግንባታ ያለውን አስተዋጽኦ ስናነሳ በውስጡ ሃይማኖታዊ ቅርጽ እንዳለ ያሳያል:: ሃይማኖት በተለያየ ቅርፅ ቢገኝም እንኳን በዙሪያችን አንድ እሴት መሆኑን ነው ብያኤዎቹ የሚያመለክቱት::

በኢትዮጵያ በተለይም ይህ ጥናት በሚያተኩርበት ብሔረሰብ እና ከርእስ ነገሩ ጋርም በተያያዘ መልኩ ለመተንተን ይቻል ዘንድ የሀገረሰባዊ ሃይማኖት፣የታሪካዊ እና የባህል ሃይማኖት ምንነትን ደግሞ ቀጥለን በመጠኑ እንመልከት::

ሃገረሰብ ሃይማኖቶች የሚባሉት በማህበረሰብ የእለት ተእለት ህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ ልዩ ልዩ ክስተቶችን ለመቋቋም የሚረዱ ህዝባዊ የእምነት ስርዓቶችና ልምዶች ናቸው:: እነዚህ በልዩ ልዩ አውዶች ውስጥ ከልማዳዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሃይማኖቶች ጋር እየተቀላቀሉ ሊታዩ የሚችሉ ሁኔታዎች ሁሉ ናቸው በሃገረሰባዊ ሃይማኖትነት የሚፈረጁት::

ሃገረሰብ ሃይማኖት በውስጡ እምነትን፣ 'ባዕድ አምልኮን' እና ልማዳዊ ትዋኤዎችን የሚይዝ ሲሆን፣ አፋዊ በሆነ መልኩ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው:: ከታሪካዊ ሃይማኖቶች የሚለየውም የሃይማኖቱ መስራቾች፣ ጀማሪዎች፣ የአስተምህሮቱ ሊቃውንት እና የተደራጁና ታዋቂነት የተሰጣቸው ካህናት፣ ወይንም የእምነት አባቶች ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ ስለሌሉት ነው:: አንዳንዴ ከታዋቂዎቹ ታሪካዊ ሃይማኖቶች የተወሰዱ (የተቀዱ) ልምምዶችን ስለሚወስዱም ሃገረሰብ ክርስትና፣ ሃገረሰብ እስላም የመሳሰሉ ስያሜዎች በሰለጠኑት የአውሮፓና የእስላም ሀገሮች ውስጥ ይሰጧቸዋል::

ሀገረሰብ ሃይማኖት ከዚህም በተጨማሪ የህዝብን ፍላጐቶች ለማንፀባረቂያነት የሚውሉ ባህላዊ ልምምዶችንም ያካትታል:: የልማድ ክርስቲያኖች (የልማድ እስላሞች) ተብለው



ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

የሚጠሩና ሃይማኖታዊ ስርዓቶቻቸው የሚያሂቸውን ትዋኔዎች ማለትም መደበኛ የአምልኮ ስርዓቶችን የማይከታተሉ፣ በየትኛውም ቤተ እምነት ያልታቀፉ፣ በየትኛውም ማህበረ ምእመናን አባል ያልሆኑ፣ በሃይማኖታዊው የጋብቻ፣ የቀብር፣ የጥምቀት ስርዓቶችም የማይሳተፉ፣ የስም ክርስቲያን ወይም የስም እስላሞች የመሳሰሉት ሁሉ በዚህ ስር እንደሚካተቱ ይገለፃል::

ሀገረሰብ ሃይማኖት በተራ ሰዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች ቁጥጥር ነፃ የሆኑ፣ ከሃይማኖታዊ መምህራን ትምህርቶች የራቁና በሀገረሰባዊ ባህል ብቻ የሚመሩ ወገኖች ሁሉ የሚጠሩበት ስያሜም ነው::ታሪካዊ የሚባሉት ሃይማኖቶች በስርዓት የተቀረፀ ዶክትሪን፣ ተቋምና ትምህርት ያሏቸው ሲሆኑ፣ ሀገረሰብ ሃይማኖት ግን የእነዚህ ሁኔታዎች በስርዓት ያለመኖሩ ሁኔታና የእምነቱ አስተማሪዎችም እንደ ባለሙያ ያለመታየታቸው ነገር እንደ አንድ መለያ ይጠቀሳል::

ሀገረሰብ ሃይማኖት የሰዎችን መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚመልስ፣ ግቡም ለህሙማን ፈውስን ማምጣት፣ ወይም እድል ፈንታቸውን (መሞት፣ መትረፍ) ትንቢት መናገርን ያካትታል:: ብዙዎቹ እንዲህ ያሉት ሃይማኖታዊ ስርዓቶች፣ መስዋእት ከማቅረብ ጋር የተያያዙ ክዋኔዎችን የያዙ፣ ተፈጥሯዊ ሃይማኖታዊ ስርዓቶች ናቸው:: አንዳንዴም ነገን የሚያሳይ መለኮታዊ ተውህቦ እንዳላቸው ተደርገው ይቆጠራሉ:: በዚህም በትእንግርታዊ ስርዓትና በሀገረሰብ ሃይማኖት መካከል ሀቀኛ የመለያ መስመር ማስቀመጡ አዳጋች ይሆናል::

በሀገረሰብ ሃይማኖት ውስጥ የሚታዩ ነገሮችን ስንመለከት አዶ ከብሬን[27] የመሳሰሉ ነገሮችን ስንመለከት ከባእድ መናፍስት ጋር ያለውን የእምነት ትስስር እናያለን:: ለምሳሌም ያህል ስለ ‹‹ቡዳ›› ያለው እምነት፣ ከጥንቆላ፣ ከአጋንንት እና ከእርግማን ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች፣ እንስሳት አዝመራን ወዘተ. የመመረቅ ስርዓት፣ የማህፀንን ርጥብነት የተመለከቱ ምርቃቶች፣ ልማዳዊ የትንግርት ስርዓቶች፣ የምስጋና ፀሎቶች፣ የአያት፣መናፍስትን አምልኮዎች፣ ሁሉ ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚታዩ ናቸው:: በተጨማሪም ክፉ ነፍሳትን (ለምሳሌ እባብ) መያዝ፣ መስዋእት ማቅረብ፣ ለሃይማኖታዊ

---

[27] ፈቃደ, 1991, 12



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ስርዓቶች የሚደረጉ ጌጣጌጦች[28] በቤት ውስጥ (ደጅ) የሚደረጉ ሃይማኖታዊ የጥበብ ሥራዎች፣ የትንቢት እና የህልም ፍቺዎችን ከመጪው ሁኔታ ጋር እያስተያዩ መተርጐም የመሳሰሉት ሁሉ ከሀገረሰብ ሃይማኖት ጋር የሚጠኑ ነገሮች ናቸው:: እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ከከምባታ ሀገር በቀል ትውን ጥበባት ጋር እያስተያዩ ለመመልከትና ትንታኔ ለመስጠት ከርእስ ነገሩ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ነው ይህን ያህል ገለፃ የቀረበው:: በመሆኑም ከዚህ በላይ የቀረቡትን መሠረታዊ የሃይማኖት እሳቤዎች መነሻ በማድረግ ሀገር በቀል ሃይማኖቶችና ትወናቸውን እንመልከት::

### 5.1.1 ሀገር በቀል ሃይማኖትና ትወና

አምበሪቾ ተራራ ለከምባቶች ከፍተኛ ትርጉም አለው:: የሀገረሰብ ሃይማኖታቸውም ከሱ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው:: ከጠላት ወረራ የተሸሸጉበት፣[29] የገዢዎች መንበር የነበረ፣ እንደተቀደሰ ስፍራ የሚመለከቱትና ‹‹የቅዱሳኑ›› ማረፊያ ነበረ ብለው የሚያምኑትም ስፍራ ነው::

አምበሪቾ ለከምባቶች ሀገር በቀል ሀገረሰባዊ ሃይማኖት መነሻ ነው:: በድሮ ዘመን ከምባቶች ጠዋት ሲነሱ ፊታቸውን ወደ አምበሪቾ መልሰው ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ሌሊቱን በሰላም ስላሳደረችው ፀሎት ያደርጉ ነበር:: ምስጋናቸውንም ያቀርቡ ነበር:: ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የቃል ታሪክ አዋቂዎቹ አቶ ኡታሎ ኦጄቴ፣ አቶ ኤርሲዶ ሚከሮ እንደሚሉትና ለዚህ ሀገረሰባዊ እምነት አስረጂ ነው ብለው የሚያቀርቡትም በአምበሪቾ ተራራ ላይ በሚገኝ ዋሻ ውስጥ የክርስቶስ ግማደ መስቀል ተደብቋል የሚል ነው:: ሄሮደስ ኢየሱስን ሊያጠፋው በፈለገ ጊዜ ማርያም ይዛው መጥታ የተሸሸገችው እዚህ ተራራ ላይ ነው:: ስለዚህ ይህ ቦታ መስዋእት ለማቅረቢያና ለፀሎት የተቀደሰ ስፍራ ሆኗል የሚል እምነት ማህበረሰቡ አዳብሯል::

በአምበሪቾ ተራራ ላይ እንደተለየ ቅዱስ ቦታ ተደርጐ የሚቆጠረው ሜዳ ‹‹ክቶሲ ፊዶ›› ከሀገር በቀል ሃይማኖቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው:: በከምባትኛ የዚህ ትርጉም የአምላክ ቤት፣ ወይም ቤተ መቅደስ፣ ወይም ደጃፍ እንደማለት ነው:: የሚሉ ቃል ታሪክ አዋቂዎች ቢኖሩም ሁሉም ግን በዚህ አባባል አይስማሙም:: ለምሳሌ አቶ

---

[28] ዶቃ፣ ጨሌ፣ አልቦ፣ አንባር፣ የመሳሰሉትና በልብስ ላይ፣ በአንገት በእጅ በእግር በመሳሰሉ የሰውነት አካላት ላይ የሚንጠለጠሉ፣ የሚለኩ፣ የሚጠበቁ ነገሮችን ሁሉ ያካትታል:: ለምሳሌ በእጅ ሳር መያዝ፣ ልምላሜ፣ እርጥበትን፣ በረከትን ከመጥራት ጋር ይያያዛል::

[29] 16ኛው ክ.ዘመን የግራኝ ወረራ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ኤርሲዶ ሚኮሮ የተባሉ የብሔረሰቡ ቃል ታሪክ አዋቂ ክቶሲ ማለት ‹‹ክርስቶስ›› ማለት ነው ይላሉ፣ ‹‹ክቶሲ እውነተኛ አምላክ ነው፤ ሌሎቹ ግን ያዳላሉ፣ ማማለጃ ይቀበላሉ፤ እሱ ግን እንዲህ አይደለም ሲሉም ይከራከራሉ፡፡ ለእሳቸውና እሳቸውን ለመሳሰሉት ብዙዎች ክቶሲ የአይሁዱ ክርስቶስ ማለት ነው፡፡ ይህ ‹‹ክቶሲ ፊዶ›› የተባለ ሜዳማ መሬት እንደ ቅዱስ ስፍራ የሚቆጠር በመሆኑም አይታረስም፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ በዓመት አንድ ጊዜ ይከበር የነበረ የአምልኮ ስርዓት ይካሄድ እንደነበረም የታሪኩ አዋቂዎች ይገልፃሉ፡፡ በዚህ እለት በከምባቶች ዘንድ ታዋቂ የሆነውን የግፋታ ጨዋታ በመጫወት ከየአቅጣጫውና ከየግዛቱ ወደ ተራራው አናት ይጉርፋሉ፡፡ በዚህ ቀን ግፋታን ሲጫወቱት የሚዜሙት ግጥሞች ቀደም ሲል ከተመለከትናቸው እና ከመስቀል በዓል ጋር ተያይዘው ከሚዜሙት በይዘታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡

ዜማውን በቅብብል የሚጫወቱት ሲሆን በአንድ ወገን የተሰበሰቡትና የተያያዙት ወገኖች ‹‹ሠጂ አባ ፎሉ ኪሃ›› ሲሉ ‹‹ጉበኒ ፎሉ ኪሃ›› በማለት ሌሎቹ በመመለስ ነው፡፡ ትርጉሙም ስልጣን ሁሉ ያንተ በመሆኑ ከዓመት ዓመት አደረስከን፣ የ30 በሮች ጌታ ሕይወታችን ያንተ ነው ሲሉ የጉበና አባት ነፍሳችን ያንተ ነው በማለት ነው፡፡ ይህን አምልኮ የሚቀበለው ሰው አበሰሪቾ እንዲሁም መገናንቾ አምላኪዎቹ እንደደረሱ፣ ጨዋታቸውን እያሞቁ ጭፈራውን እያቀለጡ ሲያደምቁት እሡ በመሃል እየጨፈረ መንፈሱን ያነቃቃል፡፡[30] የተነቃቃው መንፈሱ እየመራውም (እየነዳውም) በእሳት ላይ መንከባለል፣ መራመድ ትንቢቶችን መናገር፣ ቀረብኝ ጐደለብኝ የሚለውን ምሱን እንዲያቀርቡለት ማዘዝን፣ የወደዳትን ሴት እንዲያመጡለት፣ መናገርን ጨምሮ፣ ትእዛዛትን እና መመሪያዎችንም ያስተላልፋል፡፡ ይመርቃል ይራገማል፣ ይፈራል ይከበራልም፡፡

ወላጆች ልጅ ሲወልዱ ልጃቸው ጤናማ ሆኖ እንዲያድግ የሚያስመርቁት፣ አበሴሪቾ ዘንድ ወስደው ነው፡፡ በጋብቻ የሚጣመሩ ጉብሎችም ከጋብቻው በፊትም ሆነ በኋላ እዚያ ሄደው ጋብቻው ተመርቆ ይሁንታ የሚሰጠው በእሱ ነው፡፡ ሴት ከሆነችም መገናንቾ በእርሷ እርሻቸው እንዲባረክ፣ ከብቶቻቸው እንዲበዙም ለምርቃት ወደ አዋቂው ተመላኪ መሄዱ የግድ ነው፡፡ እንዲሁም፣ የተጣሉትን፣ ንበረት ወስዶ የካዳቸውን፣ ያጠቃቸውን ሁሉ ለማስረገም ወደዚህ መሄዱ የተለመደ ነበር፡፡ ዛሬ ዛሬ

---

[30] በወቅቱ የሚገኙት አባሰሪቾ ሃይማኖታዊ ክዋኔዎቻቸውን በምስል ለመቅረጽም ሆነ በቃል መጠይቅ ድምጻቸው እንዲቀዳ ፈቃደኛ ስላልነበሩ ከዚህ ጥናት ጋር በአባሪነት ማቅረብ አልተቻለም



ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

ግን ከፕሮቴስታንቱ እምነት መስረፅ የተነሳ እየቀረ እንደሆነ የቃል ታሪክ አዋቂዎቹ አቶ ወርቁ ጌጂባ፣ አቶ ቀልቢሶ መኮ ይገልፃሉ፡፡

በዚህ በአምበርቾ ተራራ ላይ የሚቀርበውን የአምልኮ ስርዓት ጨርሰው ወደሰፈራቸው ሲመለሱ ከአባሴራቾ ግቢ የሚገኘውን የጥድ ዛፍ ቅርንጫፍ በመቁረጥ ይዘው ወደ መንደሮቻቸው ይመለሳሉ፡፡ ይሄ የተመላኪውን አዋቂ ሰው በረከት ይዞ እንደመመለስ ሲቆጠር፣ በሰፈር ለቀረው ሰው ሁሉ እንደበረከት የሚቆጠር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተመረጠ ሰው ለንግስና የሚቀባበት ‹‹የቃል ኪዳን›› ድንጋይ ‹‹ሀድሪ ከኑ›› ተጠቃሹ ሀገር በቀል ሀገረሰብ ሃይማኖት ነበር፡፡ በዚህ ሰውን ሊያሾልክ የሚችል ቀዳዳ አለው በሚባለው ቀዳዳ ውስጥ ለንግስና የሚቀባው ሰው ሾልኮ እንዲያልፍ ይደረግና ከሚቀባው ተመላኪ ሰው ከአባሴራቾ እጅ በሚወርድለት የንግስ ቅባት መቀባት፣ ለዘላለም፣ ለዘር ዘር የሚፀና ቃለ ኪዳን በመሃላ የሚገባበት እና አምልኮአዊ ስርዓት መተወኛም ነው፡፡ በከምባታ ብሔረሰብ ከሚከበሩት ሀገር በቀል ሀገረሰብ ሃይማኖቶች መካከል ‹‹ፋንዳኖ›› እምነት አንዱ ነበር፡፡ የዚህ ሃይማኖት ካህናት የነበሩት ሰዎች ዝናብን የማዝነብ ትእንግርታዊ ሃይል ነበራቸው ተብለው ይታመኑ የነበሩ ናቸው፡፡ ከሰባቱ ሰማያት ጋር የተያያዘው እምነት፣ ‹‹ክቶሳ›› ከቅዱሳኑ እና ከመላእክቱ ጋር በክብር ሥፍራ ተቀምጠበታል የሚባሉት ሁሉ ከከምባታ ሀገረሰብ እምነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡

ለሙታን ቅድመ አያቶች መስዋእት ማቅረብ፣ ምግብ እና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን በልዩ ልዩ ቦታዎች ማኖር፣ መናፍስቶቻቸውን ለማስደሰት መሞከሩ ሁሉ ከዚህ ጋር አብረው የሚታዩ አምልኳዊ ትውኖች ናቸው፡፡

በከምባታ የዚህ እምነት ካህን ‹‹መገናኛ›› ይበላል፡፡ ይህ ሰው የከምባታ መንፈሳዊ መሪ፣ መስዋእት አቀራቢ፣ ፈዋሻቸው ተደርጎ ይታመናል፡፡ ሊቀ ካህኑም አባሰራቾ ተብሎ ይጠራል፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ ከ19ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ ወደ ክልሉ የገባውና ገገር የነበረው የአማራው ክፍል እንዳሰረፃቸው የሚታመኑት ቃልቻ የመሳሰሉት አምልኮታዊ ክዋኔዎች ሁሉ ተቀላቀለው ይገኙ እንደነበር የቃል ታሪክ አዋቂዎቹ አቶ ኤርሲዶ ሚኮሮ፣ አቶ ኡታሎ ኡጄቶ፣ አቶ ቀልቢሶ መኮ በቃለመጠይቁ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከጊቤ ወንዝ እና ከባሌ አካባቢ እንደገቡ የሚታመነው የኦሮሞዎች ሀገረሰባዊ አምልኮዎች፣ ከእስልምና መስፋፋት ጋር ተጎዳኝተው ከ19ኛው ክ/ዘመን

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

2ኛው አጋማሽ ጀምሮ እንደገቡ ይገለፃሉ፡፡ በእነዚህ ሁሉ የተቀላቀሉ ሀገረሰባዊ ክርስትና እና ሀገረሰባዊ እስልምና ሃይማኖቶች ከከምባቶቹ ሀገር በቀል ሃይማኖቶች ጋር ተቀላቅለው ይመለኩ እንደነበር ይገለፃል፡፡

### 5.1.2 ታሪካዊ ሃይማኖትና ትወና

በከምባቶች ባሕል ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ደምቆ የሚከበረው ሃይማኖታዊ በዓል የመስቀል (መሰላ) በዓል ነው:: የመስቀል በዓል አከባበር ከሚኖረው ሃይማኖታዊና ትወናዊ ፋይዳ አንፃር የከምባታን ብሔረሰብ አተዋወንና አከባበር ከዚህ በታች ለማሳየት ይሞክራል::

የመሰላ በዓል በከምባቶች ዘንድ ሲከበር በትወናው ላይ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያካፍላል:: ወንዶች፣ ሴቶች፣ አዋቂዎች፣ ጎልማሶች፣ ሕፃናት ወዘተ. ተሳታፊ ናቸው:: ከሃይማኖትም አንፃር ብናየው ክርስቲያኑም እስላሙም የሀገረሰብ ሃይማኖት አማኒው፣ እምነት የለሹ ሁሉ በሚገርም ሁኔታ ሲካፈሉበት ይታያል::

የከምባታ ብሔረሰብ የመስቀል በዓልን ከሁሉም በዓላት አስበልጦ ስለሚወደውና ስለሚያከብረው ዘመናትንና እድሜን ሳይቀር የሚቆጥረው በመስቀል ነው:: ለምሳሌ አንድን ሰው እድሜህ ስንት ነው ለማለት ‹‹ከተወለድክ ስንት መስቀል ሆኖሃል›› ተብሎ ይጠየቃል:: ከፍ ሲልም ደግሞ የመስቀል በዓል የዘመን መለወጫም ቀን ተደርጐ ነው የሚቆጠረው:: ምክንያቶቻቸውም በክረምት ወራት ያሳለፈውን የችግር ወቅት (የምግብ እጥረቱ፣ ዝናቡ፣ ብርዱ ...) አልፎ ከመከራው ወደ ብርሃኑ - ወደ ደስታ ወቅት እንደመሸጋገሪያ በዓል አድርገው ስለሚወስዱት ነው::

እንደ ከምባቶቹ መስቀል ለሁሉም እኩል ነው:: እንስሶችም ሰዎችም በመስቀል ይጠግባሉና:: ከብቶች ለሁለት ወራት ያህል ተለይተው ከተተወላቸው ሣር በልተው ይጠግባሉ:: ሰውም ለበዓሉ ሲቀለቡለት የነበሩት ከብቶች አርዶ በመብላት ይጠግባል:: አጠቃላይ በከምባቶች የመሰላ በዓል አከባበር ከዝግጅት እስከ ፍፃሜው የሚከተለውን ይመስላል::

በከምባቶች ዘንድ በድሮ ጊዜ የዘመን መለወጫ ተደርጐ ይከበር የነበረው የመስከረም አንድ ቀን በአል እየቀረ ያለ ይመስላል:: ከዚህ ይልቅ እለቱ ወይንም በዓሉ ‹‹ሴንጅ ባር››



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ተብሎ ተሰይሟል:: ትርጓሜውም የእንግጫ እለት እንደማለት ነው:: በከምባቶች ዘንድ ይህ እለት የሚከበረው ወጣቶች (ልጆች) በቡድን በቡድን በመሆን ተሰብስበው እንገጫ የተባለውን ሣር ለመንቀል ወደ ዱር ይወጣሉ::

በዚህም እለት

| በከምባትኛ | በአማርኛ |
|---|---|
| ‹‹ሆሌ›› ‹‹ሆሌ›› ያሆ | ‹‹እሰይ እሰይ›› ‹‹ያሆ›› |
| መሣሉ ኢልቤ ያሆ | ‹‹መስቀል ደረሰ›› ‹‹ያሆ›› |
| በጁቃሙን ያሆ | ደስ ይበለን ‹‹ያሆ›› |

እያሉ ሀገረሰባዊውን ጨዎታቸውን እየተወኑ ነው::

እረኞች ችቦ ሰርተው ለወላጆች የሚሰጡበት፣ እንግጫ የተባለ ሳር ነቅለው በአናታቸውና በቤት ምሰሶ ላይ የሚያስሩበት በመሆኑ ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ የሚከበረው የእርድ በአላቸው አመላካች ትእምርት ተደርጐም ይወሰዳል::

በከምባቶች ዘንድ ሌንጃ ወይም እንግጫውን ለመንቀል የሄዱት ልጆች ወደ ቤት እስከሚመለሱ ድረስ እናቶች የእንሰት ቡላ ያነኩሩና ከተፈረፈረ በኋላ በቅቤና በቅመማቅመም አሳምረው ሰርተው ይጠብቋቸዋል:: ልጆቹም የተዘጋጀላቸውን ምግብ በልተው እንደጨረሱ የቤቱን ድርሻ እንገጫ ምሰሶ ስር አስቀምጠው ይወጣሉ::
እነሱ ከወጡ በኋላ የቤቱ አባወራ (እሱ ከሌለ ታላቅ የሆነው ወንድ ልጅ) ተነቅሎ የመጣውን ሌንጃ ወይም እንግጫ ሦስትዮሽ ገምዶ በምሰሶ ላይ ከፍ አድርጐ ጠምጥሞ እያሰረ ተመስገን! ለዚህ ያበቃን አምላክ የከርሞ ሰው ይበለን! አገራችንንና መንግሥታችንን ይጠብቅልን እያለ ለቤቱና ለአገሩ መልካም ምኞቱን በፀሎት ያሳርጋል:: በዚህ ወቅት የሚታየው ትወናም የሚከተለው ነው። ምርቃቱን የሚቀበሉ ሁሉ የሁለት እጆቻቸውን መዳፎች ወደ ላይ በመገልበጥ ይቆማሉ መራቂው ሰውም የተመራቂዎቹን ሰዎች እጆች ተራ በተራ በመያዝ በእያንዳንዳቸው እጅ ላይ ምራቁን እንትፍ እንትፍ ያደርጋል። ተመራቂዎቹም ዝቅ በማለት የመራቂውን ሰው እጅ በመሳም ምርቃቱን መቀበላቸውን አሜን፣አሜን በማለት ያረጋግጣሉ።

እንግጫ በምሰሶ ላይ ከታሰረ በኋላ የሚቀጥለው ትወና ይፈፀማል:: በአባት ወይም እሱ ከሌላ በአንጋፋ ልጅ በራፍ በባሕሉ አጠራር ‹‹ዱሊ አሮን›› /በእርድ በራፍ/ ስድስት



ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ለስድስት እየሆኑ ይሰበሰባሉ:: በዚህ እለት የሚበላው ቀድሞ ለመስቀል ታርዶ በቅርጫ የገባው ሥጋ ለቤቱ በተለይ የተሰጠው ‹‹አቾራ›› የተባለው በጨው ታሽቶ፣ ተዘልዝሎ፣ ደርቆ በቃጫ ተጠቅልሎ የተቀመጠው ሲሆን፣ ተቀቅሎ ነው:: በደንብ ተቀቅሎ እየተከተፈ ከቀረበ በኋላ አባት (ታላቅ የሆነው ልጅ) ምርቃት ካደረሰ በኋላ ነው ምግቡ የሚበላው:: ከዚያም ምን አይነት ሠንጋ፣ በምን ያህል ብር እንደሚገዙ ይወያያሉ:: ገንዘቡን ለመሰብሰብም ቀን ከቆረጡ በኋላ ‹‹ግሪ ቀሣንቾ›› ደመራ የማቆም ስርዓት ይቀጥላል::

ለደመራ ዝግጅት ወጣቶች ወደ ጫካ ሄደው ‹‹ሀንጠዞ›› (ኮሰረት መሰል ወይም ከሴ) እንደጭራሮ ያለ እንጨት ያመጣሉ:: በእድሜ ጠና ያሉት ደግሞ ያልተመለመለ የደመራ ምሰሶ ያቆማሉ:: ወጣቶች ያመጡትንም ጭራሮ ‹‹ሐንጦዞ›› እንዳይነድ አጥብቀው ያስሩታል:: ከዚያም ለመስቀል ሰሞን የሚሆን እንጨት ፈልጠው በየበራፎቻቸው ይከምራሉ:: ምንም አይነት ችግር ቢገጥም እንኳን ከዚህ እንጨት ያለ ባለቤቱ ፈቃድ መውሰድ አይቻልም:: የመስቀልን ነገር ብወስድ መስቀል ይቀስፈኛል ብለው ስለሚያምኑና ስለሚፈሩ ነው:: በዚህ ሰሞን የከምባታ ምርቃቱም ሆነ እርግማኑ ከመስቀል ጋር አያይዞ ነው:: ለምሣሌ ሌንጃ ወይንም እንግጫ ከታሰረ፣ ከዘመን መለወጫ በኋላ ለመራገም የፈለገ ሲራገም ‹‹መስቀል ይፍረድብህ፣ እውነት ለመናገር መስቀል ይህን የደረሰውን አያብላህ /አያድርስህ/ ይላል:: ከሰው ቢጣላም በህግ አምላክ የማለት ያህል በመስቀል ይሁንብህ ይላል::

ሴቶቹ ደግሞ የመስቀል በዓል አከባበራቸው እንደሚከተለው ነው:: በባሕሉ የሴቶቹ መስቀል ከወንዶቹ ቀደም ብሎ ይደርጋል:: ሴቶቹ በአማታቸው ቤት፣ እሱ ከሌለም በባለቤታቸው ታላቅ ወንድም ቤት፣ በሌንጃ እለት ይሰበሰባሉ:: ቡና ይፈላል:: አማት ወይም የባለቤት ታላቅ ወንድም አምላካቸውን አመስግነው ለመስቀል ተብሎ ተፍቆ ከተቀመጠው ቆጮ ውስጥ ‹‹ለአተካኖ›› ተብሎ የተቀመጠውን ‹‹ሜራሮ›› /ነጩ የቆጮ ክፍል/ አውጥተው ከፊሎቹ ሲጨምቁ ቀሪዎቹ ይቆረጣሉ:: ከመካከላቸው በእድሜ ጠና ያሉት ሴት የተቆረጠውን ቆጮ በንጹህ የኮባ ቅጠልና ወፍቾ ያስራሉ:: ይህም የታሰረው ቆጮ በባህሉ አጠራር ‹‹ሽፌ›› ይባላል:: ሽፌ ከታሰረበት እስከሚፈታበት ቀን ድረስ ልጆች ይቀመጡበታል:: በእርድ እለት የሚጠጣ ቦርዴ፣ ጠላም ይጠመቃል:: በዚህ ሰሞን ውሃ መጠጣት ነውር ነው:: የሴቶቹ መስቀል ከሁለት ቀናት ቀደም ተብሎ

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

ይጀመራል:: አማት ያላትም ከሆነ የአማት ውቃቢ /ወጣ/ ብለው አተካና ይሠራሉ:: የራሷን ውቃቢ /ወጣ/ እርድ እንደ ነገ ሆኖ ማምሻውን አተካና ይሰራል::የአተካና አሰራር የሚከተለውን ይመስላል:: ከ15 ቀናት በፊት ቆጮ ተቆርጦ የታሰረው ይፈታና እንዲደቅ ከተደረገ በኋላ በወንፊት ይነፋል:: ደቃቅ የሆነው ይነከራል:: የተነከረው በወተትና በቅቤ ብቻ እየታሸ ይሠራል:: ካለ፣ በወተት፣ በአይብና በቅቤ ተደርጐ ነው የሚታሸው:: ለዚህ ወቅት የሚሆን ወተት ከሌለም፣ ጐረቤቶች ለመስጠት ይሻማሉ:: ምክንየቱም መስቀል ከቤቴ ወተት አይነሳኝም ብለው ስለሚያምኑና ባህሉም ግድ ስለሚላቸው ነው::

በከምባታ የመስከረም ወር ከጠባ በኋላ የህብረተሰቡ ጨዋታው፣ መልካም ምኞቱ ሁሉ ስለመስቀል ብቻ እንደሆነ የሀገር ሽማግሌዎች ይገልፃሉ:: ሲመራረቁም ሆነ ሲረጋገሙ መስቀል ማእከላዊ ሆኖ ነው:: የልጆች ጨዋታዎችና ዜማዎችም በመስቀል መንፈስ የተቃኙ፣ ስለ መስቀል የሚቀሰቅሱ ናቸው:: ውስጣዊ ሃሳባቸው ግን መስቀል ደርሷልና ጥሩ ሠንጋ ይገዛ በሚል ማሳሰቢያ መሰል ማስተላለፍም ጭምር ነው:: የራስን ሠንጋ ማወደሱ፣ የሠራተኛውንም እያንቋሸሹ፣ እያጥላሉ ያዜማሉ፤ ይዘፍናሉ:: ለምሳሌ:-

| አውራጁ | ተቀባዩ |
|---|---|
| ሆሆ ላሌ ወይ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| ሣዳም ኡሮን ሠንጋሃ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| ሊራንሶ ኡሮን ልጃሃ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| ወሌቦ ኡሮን ሆልቼታ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| ቡፌብ ኡሮን ቡትቼ | ሆሆ ላሌ ወይ |

የአማርኛ አቻው

| | |
|---|---|
| ሆሆ ላሌ ሆይ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| በሣዳም በራፍ ሠንጋ፣ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| በሊራንሶ በራፍ መሲና፣ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| በወሌቦ በራፍ በግ | ሆሆ ላሌ ወይ |
| በቡፌቦ በራፍ ግልገል ይታረዳል:: | ሆሆ ላሌ ወይ |

በግጥሞቹ እንደሚታየው ክዋኔው ሀብታም የሆነው ሰንጋ በማረዱ፣ ደሃ የሆነውም ግልገል በማረድ፣ የፊተኛው ሲወደስ፣ ሲሞገስ የኋለኛው ደግሞ ዝቅ ተደርጐ ሲታይ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በእንቅስቀሴያቸውም መወራረፉን ተከትሎ መኮፈስ ወይም መሸማቀቅን ያሳያሉ። እንደ ሀገር ሽማግሌዎቹ ገለፃ ከሆነ ከመስከረም 1-16 ያሉት ቀናት የሠንጋ ማፈላለጊያ ቀናት ናቸው። በቁጥር ከ4-6 የሚደርሱ ተቃራጮች (‹‹ሼማታ››) በሚሰበስቡት ብር መጠንና ባሉት ተቃራጮች ብዛት ሠንጋ አፈላልገው ይገዛሉ። ያላቸው በቤታቸው ሊቀልቡ (ሊያስቀልቡ) ይችላሉ። መስከረም 15 እና 16 ቀናት በየአካባቢው ‹‹በቦዳ›› የመስቀል ገበያ ይቆማል። በነዚህ ቀናት የከብት ቀረጥ ሁሉ ይነሳል። የሚገዙት ከብቶችም የመስቀልነታቸው እንዲለይ በጀርባቸው ላይ እበት ይቀባሉ። ሻጮች ‹‹አፎ ኢሉ መሣሉ ሜሼሉ›› ይላሉ። መስቀል ለመብላት አደረሳችሁ፤ ከብቱም የሰባ ይሁንላችሁ ብለው ይመርቃሉ። ገዢዎቹም ‹‹ከእናንተ ጋር›› በማለት ምላሽ ይሰጣሉ።

በእጦት፣ በተጫራቾች ያለመስማማት፣ በልዩ ልዩ ጥል የተነሳም ከብት ያልገዙ ካሉ በዘመድ አዝማድ፣ በጕረቤትም ቢሆን ተዋጥቶ፣ የተጣሉትም መስከረም 16 ምሽቱን ታርቀው በእርድ እለት ወደሚቆመው ገበያ (‹‹ለጦ›› ይባላል) በመሄድ ተገዝቶ እንዲመጣ ይደረጋል። በዚህ እለት ሠንጋ ለሚገዙ ሰዎች ማህበረሰቡ የተለመደውን አባባል ‹‹ኤራም ሠንጋ ዱላኖ፣ ኤራሙቡ ወዴማ ዱላኖ›› በጊዜ የተመካከሩ ሠንጋ ያርዳሉ። ያልተመካከሩ እርጉዝ ላም ያርዳሉ በማለት ይቀላለዳሉ።

መስከረም 17 ቀን ለእርድ የተዘጋጀው ሠንጋ ወደ ውጭ ሲወጣ የከምባቶች ባህላዊ ምግብ የሆነው የቡላ ፍርፍር ይወጣል። ከቤተሰቡ በእድሜ ታላቅ የሆነው ሰው ተገቢውን ምርቃት አድርጎ ሠንጋውን ሲጥል፣ በቦታው ለተገኘ ሰው ሁሉ የቡላው ፍርፍር ተሰጥቶ ይበላል። ከሠንጋውም ከየብልቱ የተቀነጣጠበ ስጋ ይጠበስና ከበሉ በኋላ ስጋውን ተከፋፍለው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። ስጋውን ወደ የቤታቸው ካደረሱት በኋላም ምሽቱን ወደሚከበረው (12 ሰአት) ደመራ ‹‹ግራቀሣንቾ›› ይሄዳሉ ወንዶች ብቻ ናቸው የሚሄዱት ደመራው በእድሜ ባለፀጋው ከተለኰሰ በኋላም እሳቱን እየዞሩ ይጨፍራሉ። እንዲህ:-

| አውጪ | ተቀባይ |
|---|---|
| ሆ … ሆ ይዬቤ | ሆ .......... ይ |
| መሣላሃ ኤማን ኢልሾኔ | ሆ .......... ይ |
| መሪሾ ኑሩማ ኑሪ | ሆ .......... ይ |
| መሣለሃ ኤመን ኢልሾኔ | ሆ .......... ይ |

ወጋንካስ ኤመን ቆራቦኔ ሆ ........... ይ

ወጕስ ጡምቢ እሁ ሆ ........... ይ

ትርጉሙ

ሆ ...... ሆ በሉ ሆ ........... ይ

መስቀልን እንኳን አደረሰን ሆ ........... ይ

ደመራ ሆይ ፍስሃ ሁን ሆ ........... ይ

መስቀልን እንኳን አደረሰን ሆ ........... ይ

ዓመቱን እንኳን ጠበቀን ሆ ........... ይ

አዲሱ ዓመት የሰላም ይሁን ሆ ........... ይ

ከዚህ በኋላ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወይም የአካባቢው የጉሣ መሪ፣ ህብረተሰቡን፣ አካባቢውንና ሀገሩን መርቆ ይለያያሉ:: ሁለተኛው ቀን መስከረም 18 ‹‹ቢ.ቃንቺ ባር›› የክፍፍል ቀን፣ ተብሎ ይጠራል:: ክፍፍሉ ከአዋቂ ሰው ከተፈፀመ በኋላ፣ ከሦስተኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሳምንት ሊዘልቅ ይችላል። ይበላል፣ ይጠጣል:: ገበያ አይወጣም:: ዘመድ ዘመዱን፣ ሙሽሮችም ወደየቤተሰቦቻቸው በመሄድ ወላጆቻቸውን የሚጠይቁበት ስጦታ የሚለዋወጡበት፣ የሚመራረቁበትም ጊዜ ይሆናል::

በሌላ በኩል ስንመለከተው ደግሞ ለየት ያሉ ትዋኔዎች እንዳሉበት ይስተዋላል:: የመስቀል በዓል የእርድ እለት ከመከበሩ ሁለት ሳምንት ያህል ቀደም ብለው ስለበዓሉ ቀን ለብሔረሰቡ አባላት የሚገለጽበት መንገድ አለ:: ይኸውም ከብሔረሰቡ አባል መካከል አንድ ሰው በበትር ላይ ስልቻ ሰክቶ በገበያ መካከል በመዞር የሚያሳይበት ስርዓት ነው:: ይህንን ሰው ገበያተኛው እንደተመለከተ አንድ ሊተላለፍለት የተፈለገ መልእክት እንዳለ ይገነዘባል:: ወዲያውኑ የብሔረሰቡ መሰብሰቢያ ወደ ሆነው ደገሌ ዛፍ ያመራሉ:: በዚያም ወማ (ንጉሡ ኮራፋራ) የጉሳ መሪው ይጠብቋቸዋል:: ህዝቡ መሰብሰቡን ይመለከቱና በመቆም የጨለማ፣ የረሃብ፣ የጉርፍ፣ የነጉድጓድና የጭንቀት ወቅት ማለፉን፣ ያበስራሉ ለዚህ ያበቃቸውን አምላክም ያመሰግናሉ:: ዘመኑም የሰላም፣ የጤናና የሥራ ዘመን እንዲሆን ይመኛሉ:: አያይዘውም የመስቀል በዓል የሚከበርበትን ቀን በማወጅ፣ የሚበላው ምግብ ሁሉ እንዲስማማቸው መርቀውና ፀልየው ያሰናብቷቸዋል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ወማ ወይም ኮራፋራው የመስቀልን በዓል መከበሪያ ቀን የሚያውጁበት ምክንያት አለ:: የዚህ ምክንያቱም ለጠምባሮዎች ቀኑን የሚወስኑላቸው ጨረቃን በመቁጠር የመወሰኑ ሃላፊነት በጕሳ መሪዎቹ ጉባኤ ‹‹ቶቤ›› የሚወሰን በመሆኑ ነው:: ውሳኔው ለህዝቡ የሚደርሰውም በቶቤው የበላይ ሰብሳቢ ወማ በመሆኑ ጭምር ነው:: ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ትዋኔ ከግንኙነት ወይም ከተግባቦት አኳያ በከምባቶቹ ምን መልክ እንዳለው አመላካች ነው::

የመስቀል በዓል አከባበር በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚተወኑ ተግባራትም አሏቸው:: የመጀመሪያው ተግባር የዱልኦ ወይም የእርድ በዓል ከመድረሱ ከ6 ወር እስከ አንድ ዓመት በፊት ከብቶችን ለቀላቢዎች የመስጠቱ ተግባር ነው:: የሰንጋ አቀላለቡ ስርዓት በሁለት መንገዶች ይፈፀማል:: አንደኛው ባለበሬው በሬውን ለቀላቢው ከመስጠቱ በፊት የሚያስገምትበት መንገድ ነው:: በሬውን ከገዛው የገዛበትን ዋጋ በመግለፅ፣ ትርፉ ለጋራ ብሎ ይሰጠዋል:: ሁለተኛው መንገድ ባለበሬው ለበሬው ቀላቢ ከ6 ወራት - 1 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ በየወሩ ይህንን ያህል እኔ እሰጣለሁ ብሎ በሚገባው ውል መሰረት በሬውን ለቀላቢው የሚሰጥበት መንገድ ነው:: የተቀለበው ሰንጋም ‹‹ማንቹ›› በሁለት መንገዶች ሊሸጥ ይችላል:: አንደኛው እጅ በእጅ ሁለተኛው በዱቤ:: በዱቤ የሚሸጥ ከሆነ ከመስቀል በዓል በኋላ 4 ወራት ቆይቶ በጥር ወር ላይ ነው::
በዚህ ብሔረሰብ የመስቀል ሃይማኖታዊ በዓል እለት ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከጨረቃ መኖር አለመኖር ጋር በአዋቂዎች ተጠንቶ የሚወሰን ነበር:: ጨረቃ መኖሯ ከታወቀ በዓሉ ‹‹አፍቾ››[31] (ቅዳሜ) እንዲከበር ይደረጋል:: ጨረቃ በሌለችበት በዓሉ ከተከበረ ህመምና የተለያዩ ችግሮች ይከሰታሉ ተብሎ ስለሚታመንና ስለሚፈራ ነው ጨረቃን መፈለጉ:: የዱልኦ በዓል ከቅዳሜ ቀን ውጪ እንዲከበርም አይፈቀድም:: ስለሆነም በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች መስከረም 17 ሀሙስ ቢውልና በዓሉ ቢከበር እዚህ ግን ከሀሙስ ቀጥሎ በሚውለው ቅዳሜ እንዲከበር ባህሉ የግድ ይላል:: እንዲሁም በሌሎች ክልሎች በዓሉ ሰኞ ቢውል እዚህ ግን ከሰኞ በፊት በሚውለው ቅዳሜ በዓሉ እንዲከበር ይወሰናል::

በዚህ ብሔረሰብ የመስቀል በዓል ከሚከበርበት እለተ - ቅዳሜ በፊት ባሉት ቀናት የሚከበሩ ሌሎች በዓላት አሉ:: ለዚህ ይመስላል ቅዳሜን ለመስቀል በዓል የተውት::

[31] ጨረቃን የመጠበቁ ስርዓተ አምልኮ አሁን አሁን እየቀረ ነው::



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ለምሳሌ ሀሙስ ቀን ጨፎ ሀሙሳ ተብሎ ይጠራል:: ይህ እለት የተቀለቡ ሰንጋዎች ወደ ገበያ የሚወጡበት፣ ጠላ፣ ጠጅ፣ ቦርዴ፣ ሴሎ፣ የመሳሰሉት ባህላዊ መጠጦች የሚጠመቁበት (የሚጣሉበት) እለት ነው:: በጨፎ ሀሙሳ የተገናኙ ጓደኞሞች ወይም ዘመዳሞች ስለሰንጋ መግዛት ሳይወያዩ አያልፉም:: ዓርብ እለት ያካታ ሲበል፣ ምርጥ ቆጮ በወተትና በቅቤ በቅመማቅመም አብዶ የሚዘጋጅበት እለት ነው:: ይህ ምግብ አተካኖ የሚባለው ነው::

የእርድ እለት ስርዓቱ እንደሚከተለው ቀርቧል:: ለበዓሉ የተገዛው ማንቹ (ሰንጋ) በቤተሰቡ መሃል እንዲቆም ይደረጋል:: አባወራው (አንጋፋ ወንድ ልጅ) የአያት ቅድማያቶቹን ጦር በመያዝ እንዲመርቅ ይደረጋል::

**በከምባትኛ**

‹‹ሀጤማሩን አራማሩን መሰንቾ

መጮጭ ማቲቾ መጮጭ

ሞላ መጮጭ›› እያለ ነው የሚመርቀው::

**በአማርኛው**

ሀጢያታችንን ይቅር በል፣ ማረን፣

ምድራችን ትባረክ፣

ዛፎቹ ይሰሙ፣

ሞላ ይሰማ፣

ነገሥታቱም ይሰሙ ... ማለት እንደሆነ የሀገር ሽማግሌዎቹ ያስረዳሉ::

ከዚህ ምርቃት በኋላ ማንቹ ከቅድመ አያት በተወረሰው ጦር ይባረካል:: የባረከው ሰውም የማንቹን ደም በቅጠል እየነከረ ወደ ግራ፣ ወደ ቀኝ በአካባቢው (ለመናፍስቱ) ይረጫል:: በመቀጠልም ባለቤቱን፣ ልጆቹን፣ በመቀጠልም የቤቱን በር፣ ምሰሶውን፣ ደፉን፣ መቃኑን ደም ይቀባል:: ተቋራጮቹም በየተራ ተመሳሳይ ተግባራትን ይፈፅማሉ:: ለእነሱ ይህ ከመፅሃፍ ቅዱስ /ዘፀ. 12: 12/ ጋር ይመሳሰላል:: ከዚያም ተቃራጮች ድርሻ ድርሻቸውን ይዘው ከሄዱ በኋላ በቤቱ አባወራ የሚከተለው ይተወናል:: የቤቱ አባወራ ከቤቱ በህይወት ከሌሉ ከሥጋው ጥቂት ሙዳ፣ ከቡላ ፍርፍር የተወሰነ፣ ከሴሎ በጠርሙስ፣ በመውሰድ በቤቱ ምሰሶ ስር ይኖራል:: የአባቱ አዋይ /ውቃቢ/



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እንዳይቀየመው መንፈሱ እንዳይራብ፣ እንዳያዝን - ይልቁን እንዲደሰት በማለት ነው፡፡ ይህ የአያት መንፈስ አምልኮ፡፡ ከሁለት ቀናት ቆይታ በኂላም ከቤቱ ምሰሶ ስር ይነሳና ሥጋው ይጠበሳል፤ ቡና ይፈላል፣ እጣኑ ይጨሳል፣ ጉረቤት ይጠራል፤ ከዚያም ይበላል፡፡ ሴሎውም ይጠጣል፡፡ ይህ አብይ አምልኳዊ ስርዓት ሳይተወን አባወራው ከቤቱ ወደየትም ለመሄድ አይችልም፡፡ አዋያ መክሰና ይቆጣሉና፡፡

ከደመራው መልስ፣ ቅዳሜ ማታ የሚተወን ሌላ ስርዓትም አለ፡፡ ይህም በችቦ መልክ የሚዘጋጀው ጭራሮ ‹‹ኡሜሳ›› በቤት ውስጥ የማያያዝ ስርዓት ነው፡፡ ትወናው በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በእሳት የተያያዘውን ኡሜሳ አባወራው በመያዝ ‹‹ሴጦፋሊ››፣ ‹‹ሴጦፋሊ›› እያለ ወደ ውጪ ይወጣል፡፡ ክፉ መንፈስ ከቤታችን /ከሃገራችን/ ውጣ የሚል መልእክት አለው ይላሉ - የሀገር ሽማግሌዎቹ፡፡ የሚነደውንም ኡሜሳ ወስዶ በእለቱ ሌላ ትዋኔ የተተናወነበት ደመራ ላይ ወስዶ ‹‹ማሪሾ›› ላይ ይጥለዋል፡፡ ደመራው /‹‹ማሪሾው››/ ነዶ ሲያልቅ በስፍራው የተገኙ ሰዎች ከደመራው ቋሚ እንጨት ላይ ቅርፊቱን ለመውሰድ ይሻማሉ፡፡ ቅርፊቱን ያገኘ ሰው ወደ ቤቱ ይዞት ይሄዳል፡፡ ይህ ቅርፊት በባሕሉ እምነት መሠረት አሮጌው ዓመት በአዲስ መተካቱን አመላካች ትእምርት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እንዲሁም እንደ ታላቅ ስጦታም ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በደመራው እለት ይህንን ቅርፊት ወስዶ ወደ ቤቱ የሄደው ሰው በጣም ለሚወደው ወንድሙ ሚስት በስጣታ መልክ በመስጠት ለወንድሙ ያለውን ጥልቅ ፍቅርና ለዋርሳው ያለውንም ከበሬታ እንደመግለጫ ይጠቀምበታል፡፡

በማግስቱ እሁድ እለት ‹‹የጨጵሳ›› ሥርዓት መተወኛ ነው፡፡ በዚህ ትወና አባቱ ከመስቀል በዓል በፊት የሞተበት ሰው በሌሊት በመነሳት ወተትና ማር በመያዝ ወደ አባቱ የመቃብር ስፍራ ይሄዳል፡፡ በከርሰ መቃብሩ ላይም ወተትና ማሩን እያፈሰሰ የዘር ማንዘሩን ሙታን መንፈስ እየጠራ የአባቴ መንፈስ፣ ከአያቴ፣ ከቅድመ አያቴ ከቅምቅም አያቴ እና ከምንጅላቴ ጋር እንዲሁም ከእነ እከሌ ጋር አብረህ ተቋደስ እያለ ይማፀናል፡፡ ይፀልያል፡፡ በበዓሉ እለት ከጉኑ ባለመገኘታቸው የተሰማውን ጥልቅ ሀዘንም ይገልፅላቸዋል፡፡ ልጅ ሳይወልድ የሞተ አስከሬንም ከአባቱ ጉን አርፎ ይሆናል ብሎ ስለሚታመን በሳር ከወተትና ከማሩ ወደ ግራም ወደ ቀኝም በመርጨት አንተም ጠጥተህ መርቀኝ እያለ ይማፀናል - የሙታኑን መንፈስ፡፡ ወደ ጨረቃና ፀሃይም በመርጨት ዘመኑን የሰላም ዓመት እንዲያደርጉለት ይለማመናቸዋል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ከመስቀል በዓል ማግስት ህዝቡ ሁሉ የሚለዋወጠው ሰላምታ ከወትሮው የሚለይ ትወና ይታይበታል:: ሁለት ሰዎች በመንገድ ላይ ሲገናኙ ‹‹ኢዮሀ›› እያሉ በአንድ እግራቸው መሬት እረግጠው ሌላኛው መሬት ሳይነካ ከፍ አድርገው እየዘለሉ ቀዳሚው ሰው ‹‹ባሊ ሔሌሌ›› ሲል ቀጣዩ ሰው ደግሞ ‹‹ባሉ ሔአ ቀጣ ሒኢ›› ብሎ ይመልሳል:: ወዳጄ ዐውዳመቱን ሞልተህ ኑር፣ ምላሹም የዐውዳመቱን ያክል እድሜ ይኑርህ የሚል ነው::

ቀጣዮቹ ሰባት ቀናት ገበያ የሚኬድበት፣ ዘመድ ወዳጅ የሚጠያየቅበት፣ ተበልቶ ተጠጥቶ የሚጨፈርበት ነው:: ወጣቶችም የሚተጫጩበት፣ የተጋቡትም ስጦታዎች የሚለዋወጡባቸው ቀናት ናቸው:: ስጦታዎችም የሚለዋወጡባቸው ቀናት ናቸው:: ከስጦታዎች ዋናው አበባ ሲሆን ‹‹አሮሴ›› ወይም ‹‹ከምቦ›› በመባል ይጠሩታል:: የከምባታ ጠንባሮ ዞን መስቀል ይሄ ነው:: የተለየ ዝግጅት የሚደረግበት፣ ለየት ያለ አምልኳዊ ስርዓት ያለው፣ ምርቃቱ፣ እርግማኑ፣ ዜማው ጭፍሮው ሁሉ ከሌሎቹ በዓላት በተለየ የሚጐላበት፤ሰውም እንስሳውም በልዩ የሚጠግብበት፤ ሕያዋኑ፣ ሙታናቸውን እያሰቡ የመንፈስ አምልኮና ምልጃ የሚያቀርቡበት፤ ጨረቃና ፀሃይም ሳይቀሩ የደንቡን ልመና የሚሰሙበት፣ የሚቀበሉበት የሚታሰቡበትም ሃይማኖታዊ በዓል ነው:: ሀገር በቀሉ፣ ከታሪካዊው ሃይማኖት መሳ ለመሳ መድረክ የሚይዙበት፣ ሰው ሁሉ እኩል የሚታይበትም በዓለ ሃይማኖት ነው - መስቀል:: ለዚህም ነው በጥናቱ ሰፊ ቦታ ተሰጥቶት የቀረበው::

## 5.2 የልጆች ጨዋታዎችና ትወና

ከከምባታ ሀገረሰባዊ ትወናዎች መከሰቻ አንዱ የልጆች ጨዋታ ነው። በባህሉ የልጆች ጨዋታ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ባህልን ከመጠበቅ፣ ምግባርን ከማስተማር፣ ቋንቋ ከማዳበር፣ ከማስተማር አንፃርም ያላቸው አስተዋፅኦ ተጠቃሽ ነው። ባህላዊው የልጆች ጨዋታዎች አንዳንዶቹ አካላዊ እንቅስቃሴን የሚሹ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በዜማ ብቻ ወይም በዜማና እንቅስቃሴ ታጅበው የሚተወኑ ናቸው። ከእነዚህ ጨዋታዎች ውስጥ ሁለቱ ቀጥለው ቀርበዋል።

### 5.2.1 ደነባ /Danaba'a/

ይህ ጨዋታ የሚተወነው በቤት ወስጥ ሲሆን፣ በአብዛኛው ሁለትና ከዚያ በላይ በመሆን ነው፡፡ ይህን ጨዋታ ለመጫወት የአተር ወይም የባቄላ ቆሎ ያስፈልጋል፡፡ ከቆሎው በተጨማሪ ቡና ማፍላት ይጠበቃል፡፡ ቆሎው የቡና ቁርስ ማለት ነው፡፡

ልጆች የአተር ቆሎ በተሰጣቸው ቁጥር ‹‹ደነባ›› በማለት ወንዶች ከወንዶች ጋር ሴቶችም ከሴቶች ጋር በመሆን በቤት ውስጥ በተቀመጡበት ስፍራ ሆነው ቢያንስ ቢያንስ ሁለት-ሁለት በመሆን ይተውናሉ፡፡ አንድ ልጅ የተወሰኑ የአተር ፍሬዎችን በእጁ መዳፍ ውስጥ ደብቆ በመያዝ ‹‹ደነባ›› በማለት ሁለት እጆቹን ጨበጥ አድርጐ ለጓደኛው ያቀርባል፡፡ በዚህን ጊዜ ከሁለቱ እጆቹ አተሩ ያለበትን እጅ በመገመት መታ ያደርጋል፡፡ ይህ ነው ማለቱ ነው /አግቼዋለሁ/፡፡ ግምቱ ትክክል ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ተቃራኒው የተነካውን እጁን ከፈት ሲያደርግ አተር ያለበት ከሆነ አንዲትም ፍሬ ሳያስቀር ለጓደኛው ያስረክባል፡፡ ነገር ግን የተነካው እጅ ባዶ ከሆነ አተሩ ተደብቆበት የነበረውን እጅ ከፍቶ ፍሬዎቹን በመቁጠር ያሳየዋል፡፡ የተረታው ልጅም የተቆጠረውን ያህል ከኪሱ አውጥቶ ይሰጠዋል፡፡ እንደ ባህሉ ከ1-10 ያሉ የአተር ፍሬዎችን እንዲሰጠው ይገደዳል፡፡ በዚህ አይነት መንገድ አንዱ ተጨዋች የሌላኛውን ተጨዋች የአተር ፍሬዎች እስከሚያስጨርሰው ድረስ ጨዋታውን ይቀጥላሉ፡፡ አንዳንዴ የአተሩ ማለቅ ያሳሰበው ተጨዋች በመሀሉ ጨዋታው እንዲቋረጥ ሊጠይቅና ጨዋታው ሊቋረጥ ይችላል፡፡ በጨዋታው ማስገደድ የለም፡፡ ከጨዋታው በኋላ ብዙ የአተር ፍሬ የሰበሰበው ልጅ አብረውት ለተቀመጡት ጓደኞቹ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የመስጠት ግዴታ የለበትም፡፡ በባህሉ የተለመደው ግን በመካከላቸው ፍቅርን፣ ወዳጅነትን ለማጠናከር ሲባል የተገኘውን ተከፋፍለው ይበላሉ፡፡ በጨዋታው ልጆች ቁጥሮችን መማርና መገመት እንዲችሉ ይረዳቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ‹‹ደነባ›› በውስጡ የማትረፍ እና የመክሰር ሃሳብን የያዘ በመሆኑ ልጆቹን ያስደስታቸዋል፡፡ ለማትረፍ በሚያደርጉት ጥረትም ተመልካቾችን ያዝናናሉ፡፡ በዚህ ጨዋታ አስርና ከዚያ በላይ የሆኑ የአተር ፍሬዎችን ያገኘው ልጅ ‹‹ለሉ›› /ከብቶች/ አፈራ፣ ከበረ ብለው ሲያወድሱት፣ ከዚያ በታች ያገኘው ለጅ ደግሞ ‹‹ዌእከተ›› /ጥጆች/ ያዘ በሚል ስያሜ ይጠራራሉ፡፡ ጥቂት ያገኘው የበለጠ ለማግኘት ሲል የሚያሳየው መኮፈስ መኩራራት፣

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ለጨዋታው ውበት የሚሰጥ ሲሆን በራስ መተማመናቸውንም ከማዳበር እና ባህሉን ከመጠበቁ አንፃር ትወናው የራሱ ፋይዳ አለው።

### 5.2.2 ኣዴ /Ade'e/

የከምባታ ልጆች ኣዴ የሚሉትን ጨዋታ የሚጫወቱት ከብት በሚጠብቁበት መስክ ነው። ጨዋታውን በሚከተለው መንገድ ይጫወቱታል። ከብሳና ዛፍ ቅጠል ቀንጥሰው በመጠቅለል፣ ከእንሰት ተክል ደግሞ ገመድ ቆርጠው ትንሽ ድቡልቡል ኳስ ይሰራሉ። ከዚያም ኳሷን በክትክታ ላይ ያስሯታል። ከዚህ በኋላ በኳሱ ዙሪያ ክብ ሰርተው በመቆም እየዞሩ የሚከተለውን ዜማ እያሰሙ ይጫወታሉ።

በከምባትኛ

አዲያ ሆ! ሆ ሐ ሆ

አረንያ ሆ! ሆ ሐ ሆ

አቂ ፎግ ከዲ ጠቅይ ...

ልጆቹ ይህንን እያዜሙ የኳሷን ዙሪያ በሚዞሩበት ጊዜ አንዱ ኳሷን ለመያዝ ጎንበስ ሲል ተዘጋጅተው የሚጠብቁት ጓደኞቹ ታፋውን ረገጥ ያደርጋሉ በዚህን ጊዜ ትቶ ከሌሎቹ ጋር እያዜመ ክብ መዞሩን ይቀጥላል። እንደገና አዘናግቶ ከመቅፅበት ኳሷን ለመያዝ የሚሞክረው ሁሉ በሌሎቹ እርግጫን መቅመሱ አይቀርም። በዚህ አይነት ጨዋታው በዜማ እየታጀበ፣ እየተሟሟቀ ይቀጥላል። ሲደክማቸው እያረፉ፣ እየተቀላለዱ፣ እያረፉ፣ እያዜሙ፣ ይቀጥላሉ። ድካም ሲሰማቸው ወይም እርግጫው ሲበዛባቸው፣ ጨዋታውን ማቋረጥ ይችላሉ። ያልደከማቸውና ጠንካሮቹ ጨዋታውን ይቀጥላሉ። የትዋኔው ማህበራዊ ፋይዳ ልጆች ጠንካራ እንዲሆኑ፣ ደፋሮችና ጀግኖች ሆነው እራሳቸውንና ሀገራቸውን ከጠላት ለመጠበቅ እንዲችሉ ማስተማሩ ነው። የወላጆቻቸውና የብሔረሰቡን ሀብት ተጠንቅቀው እንዲጠብቁና ሳይዘናጉ ጠላታቸውን እንዲመለከቱት መማማሪያ ነው።

## 5.3 የልደት ወቅት አተዋወን

በከምባታ ብሔረሰብ የልደት ወቅት ትወና የሚጀምረው ከህፃኑ መወለድ አስቀድሞ ነው። ነፍሰጡር የሆነችው ሴት ገና መፀነሷን እንዳወቀች በሰላም ከተገላገለች በኋላ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ለሚኖረው የቄኔፋ በዓል ምግብ ማጣፈጫ፣ ለሚወለደው ህፃን መታቀፊያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ አልባሳት በቅድሚያ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡

ቆጮ፣ ቡላ፣ በሽኮ፣ የተባሉትን ምግቦች ለመታረሻዋና ለቤተሰቡም አባላት አስቀድማ ታዘጋጃለች፡፡ ለህፃኑ መቀበያ እና እንደ ሽንት ጨርቅነት የሚያገለግሉት ‹‹ሀለም›› የሚባለውን ዝግጅት፣ ከእንሰት ኮባ የሚዘጋጀው የእንሰቱ ውስጠኛው ክፍል ‹‹ወፍቾ›› አስቀድማ ማዘጋጀት ይጠበቅባታል፡፡ በዚህ ዝግጅት የነፍሰጡሯ ወዳጆች፣ ጓደኞችና ቤተሰቦች በቅርብ በመሆን ሊረዷት ይችላሉ፡፡ አብረው ማዜሙና መጫወቱም የተለመደ ነው፡፡

ነፍሰ ጡሯ በሰላም ትገላገል ዘንድም፣ ባህላዊ አዋላጆችን እና በእድሜ የበሰሉ እናቶች አራሷን ዙሪያዋን ከበው ‹‹ማረሚ›› … ‹‹ማረሚ›› በማለት ምጧ እንዲቀል፣ በሰላምም እንድትገላገል ወደ አማላጂቱ፣ እና ወደ አምላካቸው ይማፀኑላታል፣ በፀሎት ያግዟታል፡፡ በጨዋታም፣ በጭብጨባም ጭንቀቷን እንዳታስብ ለማድረግ ያዜሙላታል፡፡ ባልየውም ሆነ ሌሎች ወንዶች በቤቱ ውስጥ፣ በአቅራቢያው እንዲገኙ ባህሉ ስለማይፈቅድላቸው በውጭ ሆነው በቤቱ ዙሪያ እየተንጕራደዱ ያስባሉ፣ የቻሉም ፈጣሪያቸውን ይማፀናሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ሴቲቱ በሰላም እንደተገላገለች አዋላጇ ህፃኑን ‹‹በሀለሞ›› ቅጠል ጠቅልላ በማንሳት የሀለሞ ቅጠል ማስነክስና ቅቤ የማላስ ተግባር ትፈፅማለች፡፡ በዚህ ጊዜም በቤቱ ውስጥ ሲማፀኑ የቆዩት ሴቶች በደጅ ለሚገኙት ወንዶች (ቤተዘመዶች) ለባልየውም ጭምር በሰላም መገላገሏን ለማብሰር እንደባህሉ ደንብ፣ የተወለደውን ህፃን ፆታ በሚያመለክቱ እልልታዎች መጠን ያበስራሉ፡፡ በባህሉ መሰረት ወንድ ልጅ ከተወለደ ስምንት ጊዜ ሴት ልጅ ከተወለደችም አራት ጊዜ እልል ማለት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የእልልታው ቁጥር ምን ትርጓሜ እንዳለው ለማስረዳት የማይችሉት ቃል ታሪክ አዋቂዎች በባህሉ እንዲህ እንዲሆን ስለተለመደ መሆኑን ብቻ ይገልጻሉ፡፡ ድርጊቱ ይህ ነው የሚባል የጠለቀ ትእምርታዊ ፋይዳ አለው ለማለት ባይቻልም፣ ወንዶች ከሴቶች ይልቅ እጥፍ መብት ያላቸው መሆኑን ሳያመለክት እንደማይቀር መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የእልልታው መጠን የቱንም ያህል ቢበዛ ወይም ቢያንስ ለሴቶች እልል ከሚባለው የወንዶቹ በእጥፍ በልጦ ይታያልና ነው፡፡ ይሄ የወንዶችን በከምባታ ባህል ውስጥ የወንዶችን የንብረት፣ የሀብት የመሬት፣ የስልጣን፣ የወራሽነት መብትና የበላይነትን የሚያመለክት፣ መሆኑን መገመት ስህተት አይደለም፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ከተወለደው አዲስ ህፃን አቀባበል አኳያም የእንግዴ ልጁን የማስወገዱ ስርዓት ወንድ ከተወለደ በወንዶች፣ ሴት ከተወለደችም በሴቶች የሚፈፀም ነው፡፡ እንዲሁም በአራሷ ምንጣፍ ላይ የሚጎዘጉዙት ‹‹ቦርኪቾ›› የእንስቱ ጠንካራው ክፍል አነጣጠፍ ስርዓትም የተለያየ ነው፡፡ የተወለደው ወንድ ከሆነ ስምንት፣ ሴት ከሆነችም ቁጥሩ ሰባት ይሆናል፡፡ በምንም መልኩ እኩል አይደረግም፡፡ ከወሊድ በኋላ ከሚፈፀሙት ስርዓቶች ሌላው የቅቤ መቀባት ስርዓት ነው፡፡ አራሷን ባለቤቷን፣ ህፃኑን፣ በቤቱ ውስጥ የሚገኙት ሰዎች ሁሉ ቅቤ እንዲቀቡ ይደረጋል፡፡ ይህ የመልካም ስሜት መገለጫ፣ የልምላሜ፣ የማህፀን እርጥብነት ተምሳሌት የሆነው ስርዓት ሴቶቹ ታፋዎቻቸውን ወይንም ጭኖቻቸውን በመተምተም፣ በማጨብጨብ መልክ የሚታጀብና በዜማም የሚደገፍ በመሆኑ ተውኔታዊነት ይታይበታል፡፡ ከዚያም በትዕይንቱ ‹‹ሀዞ›› የሚሉትን ገንፎ በመብላት፣ ባህላዊውን መጠጥ ‹‹ቦርዴ›› በመጐንጨት፣ ታዳሚው ሁሉ ደስታውን የሚጋራበት ስርዓት ይከናወናል፡፡ አራሷ ከወለደች እስከ አራት ቀናት ቆይታ የእጥበት ስርዓት ‹‹ወበጣ›› ይከናወናል፡፡ በዚህ አተዋወን የሚሳተፉት በሙሉ ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ ሴቶቹ ከዱር እየቀነጣጠቡ በእንስራ ውስጥ አጭቀው የቀቀሉትን ወበጣ የተባለ ቅጠል በመጭመቅ የአራሷን መላ ሰውነት ካጠቧት በኋላ ንፁህ እንድትሆን ያደርጓታል፡፡ ከዚያም ከዚህ የእጥበት ስርዓት በኋላ የሚበላውን ‹‹በሽኮ›› የተሰኘ ምግብ ይመገባሉ፡፡

ከዚህ በኋላ አራሷን የማረስ ረጅሙ ስርዓት ይቀጥላል፡፡ ይህ የማረስ ትወና የሚተወነው ከምባቶቹ ‹‹ጂጂራ›› ብለው የሚጠሩትና በእንጨት፣ በኬሻ፣ እና ሌጦ በቅደም ተከተል ተረብርቦ በሚዘጋጅ አልጋ ላይ አራሷ እንድትተኛ በማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ይህ ጂጂራ በቤቱ ውስጥ ከሚነደው እሳት አጠገብ ከፍ ተደርጐ እንዲቀመጥ በማድረግ እሳቱን እንዲነድ ያደርጉታል፡፡ ይህም አራሷን እንዲሞቃትና ምቾት እንዲሰማት ለማድረግ ነው፡፡ የአተራረሱን ስርዓት ልዩ የሚያደርጉት ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ሴቲቱ የወለደችው ህፃን ወንድ ከሆነ የመታረሻ ወቅቷ ረገርም ሲሆን የተወለደችው ደግሞ ሴት ከሆነች የመታረሻ ወቅቷ ማጠሩ ናቸው፡፡ ሌላኛው ደግሞ የተወለደው ህፃን ወንድ ከሆነና የህፃኑ አባት ሃብታም ከሆነ ለስርዓቱ የሚያርደው ሰንጋ ሊሆን ሲችል፣ ሴት ከተወለደችለት ግን በጠቦት ብቻ ሊያልፍ መቻሉ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አራሷ በዚህ ወቅት ለመፀዳዳት ወደ ደጅ በምትወጣበት ጊዜ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

(በተለይም በምሽት ነው) በእጇ ስለት መያዝና ወንድ ልጅ አብሯት እንዲከተላት ማድረጉ የተለመደ ነው፡፡ ምክንያቱም እርኩሳን መናፍስት ሊጠናወቷት ይችላሉ ተብለው ስለሚታመኑና ስለቱ ከተያዘ እና ወንድ ልጅ አብሯት ካለ ግን አይደርስብንም ብለው ማመናቸው እንደሆነ ይገለፃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከአራሷ ራስጌ ጂጂራው ላይ ስለት ማስቀመጡም ለተመሳሳይ ዓላማ የተለመደ ነገር ነው፡፡

ምስል 9 … የልደት ወቅት ተጫዋቾች



ከወሊድ ጋር በተያያዘ ሌላው የሴቶቹ ልዩ ትወና የሚስተዋለው በ‹‹ቄኔፋ›› ላይ ነው፡፡ ይህ ስርዓት በሴቶቹ ብቻ የሚተወን፣ ሴቶችን ብቻ የሚያሳትፍ በመሆኑ ይለያል፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ ሴቶቹ ከፀነሱበት ጊዜ ጀምሮ በ‹‹ሉጉሞ›› የቅቤ ማጠራቀሚያ ጮጮ ያጠራቀሙትን ቅቤ፣ ቆጮ እና ባህላዊ መጠጣቸውን ቦርዴ፣ (ጠላም ይቻላል) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ተጋባገኖችም እንደአቅማቸው መጠነኛ መዋጮ ያወጣሉ፡፡ በዚህ መልኩ በሚዘጋጀው ምግብ እና መጠጥ እየተመገቡና እየጠጡ፣ ይዝናናሉ፡፡ ዝግጅቱም የጊዜ ገደብ የማይጣልበት ሲሆን ከአኩለ ቀን እስከ አዳር ሊዘልቅ ይችላል፡፡ በዚህ ስርዓት ሴቶቹ ማናቸውንም ግላዊ፣ ማህበራዊ፣ ወሲባዊ ነገሮች ሁሉ ሳይቀሩ እያነሱ የሚጫወቱበት፣ የሚዝናኑበት፣ የሚቀልዱ የሚያሾፉበት ነፃ አጋጣሚ በመሆኑ የተለየ ቦታ ይሰጡታል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ተውኔታዊ ትእይንቶች ይስተዋላሉ፡፡ ነፃነታቸውን ያለገደብ ስለሚጠቀሙበት፣ ሞቅ ሲላቸው ለቀቅ ዘና ያሉ ነገሮችን ሁሉ እያነሱ ይሳሳቃሉ፡፡ የወሲብ ገጠመኞቻቸውን ሳይቀር አስመስለው በመተወን ጭምር ይጫወታሉ፡፡ ያስደሰቷቸውን የሚያደንቁበት፣ የሚያወድሱበት፣ ያሳዘናቸውንና ያስከፉቸውን የሚወርፉበት አጋጣሚም ነው፤ ቄነፋ፡፡ በዚህ አጋጣሚ የተጣሉና የተቀያየሙ ሴቶች ይታረቃሉ፡፡ ቅራኔያቸውንም ይፈታሉ፡፡ እርስ በርሳቸውም የሚመሰጋገኑበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ወንዶች አይሳተፉም በስህተት እንኳን ቢገኙ ገንዘብ ሳይከፍሉ፣ ወይም ከብት ሳያርዱ አይለቋቸውም፡፡

ሴቶቹ በዚህ ወቅት የሚጫወቱት የሚከተለውን ዘፈን በመዝፈን ነው፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

እላንቾ ለምባንቾ /በባንቾ/

አጐድ ጠቲን ለምባንቾ

እላንቾ በባንቾ አጐድ ጠቲን ሄለሜ፣

አሞሄ ጋል ጪሊን ሐማሜ፡፡

ሀበርቹሴ ሀቀ ፈፅች፣

ሀላንቹሴ ዌሾ ሆሲች፣

ዳድ ኤመን ማርቶ - ጠጦች፡፡

አዋሻ ባራ ዘረዮቤ፣

ኮምቦ ሌሌቤ ከድዮቤ፡፡

እላንቹታ፣ ማስት ዊንት ኢልቱሴ፣

አያት፣ አያኑ ሄሉ ሀንቀፉን፣

አብን ጐሪታ ኤመን ኢልሾሴ፡፡

አያን! በጅግ ጠጠበ ሂፅርቱን፣

እላንቹታ፣ ከፍሴ ጪሊን አብጨቀንቱን፣

ጊራ ብሬ ጅጅራን ቆረድት ኦስኡን፡፡

ትርጉም

ወላድ ሆይ! በአንገትሽ ላይ ባለው ዛጐል ኩሪ፣

ባለመዳዘዋ ወላድ ባለዛጐል

እምዬ፣ ባቀፍሽው ሕፃን በልጅጊ (አሽቺ)

ለምለሙ የእንሰት ቅጠልና

ደረቁ የእንሰት ነጭ ርብርብ ‹‹ሐለሞ››

በእንጨትና በእንሰት ላይ ከሚቀሩ

ሕፃን ልጅ ተወልዶ፣ እንኳን ማርያም ማረችሽ፡፡

አዋሽ ላይ ሊነጋጋ ነው፣

ለመስቀል አበባዋ እየተዘፈነላት ነው፡፡

ለወላዱዋ ፍጹም ምርቃት ይድረሳት፣

ፀጋ፣ መንፈስና ተድላ ይክበቧት፣

ለክብርና ለወግ እንኳን አደረሳት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ፀጋዋ! ተደስተ መቀነቷን ትፍታ፡፡
ወላዷ በጉያዋ ሕፃን ትሚሚቅ
በምድጃ አቅራቢያ ባለው የአራስ መኝታ ላይ በጥንቃቄ ትተኛ፡፡

በዘፈኑ ክፉ ሳይገጥማት፣ ክፉ ሳይነካት በሰላም ተገላገለች እያሉ ይጫወታሉ፡፡ ይህን ጨዋታ በሚጫወቱበት ጊዜ ሴቶቹ ብቻ ተርተውን በረድፍ ይቆማሉ፡፡ ከመካከላቸው አንዷ መሪ አቀንቃኟ፣ ትንሽ ከበሮ (ቀርቤታ) በጉልበቶቿ መሀከል ይዛ ትቆማለች፡፡ ከዚያ ከበሮውን እየመታች ከላይ የቀረበውን ዜማ ጠብቀው በአንድ ላይ ሲያዜሙ ተቀባዮቹ በየመሃሉ ‹‹ሴሪ .. ሴሪ›› በማለት ተቀብለው ያዜማሉ፡፡ አተዋወናቸውን ስንመለከት ከከበሮውና ከሴቶች በሚፈልቀው አንድ ወጥ ዜማ እየተመሩ ጉልበታቸውን $45^0$ ድረስ እኪታጠፍ ድረስ ወደ መሬት በለሆሳስ ዝቅ በማለት ነው፡፡ አንገቶቻቸውንና ትከሻዎቻቸውንም ወደፊት እና ወደ ኋላ በማመላለስ በመስበቅ አይነት የተለየ ትዕይንት እያሳዩ ወደ መሬት ደርሰው እንደገና ወደ ላይ ይነሳሉ፡፡ በዚህ ዓይነት በመደጋገም እና በመመላለስ ሲተውኑ በእልልታ ድምፅ ታጅበው ነው፡፡

## 5.4 የግርዘት ወቅት አተዋወን

በከምባታ ብሔረሰብ ግርዘት ከሠርግ ያልተናነሰ ዝግጅት የሚጠይቅ ሥርዓት አለው፡፡ ወጣቶቹ ከልጅነት የእድሜ እርከን የተሻገሩበት፣ ለአካለ መጠን የደረሱበትና ወንዶቹ ወደ ቁምጣ ሴቶቹም ወደ ቀሚስ ‹‹ለንዳ›› መልበስ መሸጋገሪያቸውን የሚያበስርበት፣ ለጋብቻም ብቁ መሆናቸውን የሚያሳውቁበት ሥርዓት ነው፡፡
ይህ ሥርዓት ከዘመን መለወጫ (የሴንጃ) ስርዓት ጋር አብሮ የሚከናወን በመሆኑም በዓልነቱን እጥፍ ክብር የሚያስጠው ነው፡፡ በባህሉ ወጣት ሴቶች ከእድሜ እኩያዎቻቸውና ከፆታ ጓደኞቻቸው ወይም ከተቃራኒ ፆታዎቻቸው ጋር ለመገናኘት፣ ለመጨዋወት፣ ለመቀራረብና ለመተጫጨትም የሚፈቀድላቸው ይህ የግርዘት ሥርዓት ከተፈፀመ በኋላ ነው፡፡ ምክንያቱም ያልተገረዙ ወጣቶች ወሲባዊ ስሜታቸው ያልሰከነ ነው ብለው ስለሚያስቡና ከጋብቻ በፊት በሚያደርጉት ቅርርብ እንዳይሰናከሉ፣ ባህል እንዳያረክሱ ስለሚፈራ ነው፡፡ ከተገረዙ በኋላ ግን ይሰክናሉ ተብሎ ስለሚታመን መጠነኛ ነፃነት ያገኛሉ፡፡ ስለሆነም ለግርዘት ትኩረት ተሰጥቶት፣ ለረጅም ጊዜም ዝግጅት ተደርጐበት ነው ስርዓቱ የሚፈፀመው፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በከምባታ የግርዘት ስርዓት የሚፈፀምበት ወቅት እንደ አስገራዡ ቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ አቅም የሚወሰን ነው፡፡ በኢኮኖሚያዊ አቅማቸው ጠንከር ያሉት ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ዝግጅት በማድረግ ከሀምሌ ወር ጀምሮ ስርዓቱን ያደርጋሉ፡፡ አቅማቸው ደከም ያለው ግን ለግርዘቱ ሌላ ተጨማሪ እርድ ላለማድረግና ለመስቀል በዓል የግድ እርድ ስለሚደረግ ከዚሁ ጋር አያይዞ ማድረግን ይመርጣሉ፡፡ በዚህ መልኩ ዝግጅት የተደረገበት ግርዘት የሚፈፀመው ወጣቶቹ እድሜያቸው በአማካይ ወንዶቹ ከ15-20 ሴቶቹ ደግሞ ከ14-16 ዓመት ባለው ጊዜ ይሆናል፡፡

ለግርዘት የተዘጋጀው ወጣት እድሜው ከፍ ያለ በመሆኑም የእድሜ እኩዮቹ ሁሉ ግርዘቱ እስከሚፈፀምበት እለት ድረስ በጭፈራ እና በዜማ ሲያበረታቱት ይቆያሉ፡፡ ይህ ወቅት ከ2 ሳምንት እስከ 1 ወር ሊዘልቅ ይችላል፡፡ የተገራዡ ወጣት ቤተሰቦች በቂ ምግብና መጠጥ የማዘጋጀት አቅም ካላቸውም ጨፋሪዎቹ ወጣቶች በልጁ ቤት ያንን ያህል ቀናት በማደርም ጭምር ሊዘፍኑና ሊጨፍሩ ይችላሉ፡፡ አቅሙ የሌለው ሰው ግን በአንድ ሳምንት ውስጥ ስርዓቱን ሊፈፅም ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ ለዚህ ጊዜ የሚሆን የተለየ ምግብ ሳይሆን መደበኛ የሆነውን የቤቱ ምግብ እና ቡና አፍልቶ መጠጣትን ብቻ ሊያካትት ይችላል፡፡ ለተገራዥ ሰው ግን የተለየ ምግብ ይዘጋጅለታል፡፡ ምክንያቱም ከግርዘቱ በኋላ ለሚጠበቅበት ባህላዊ ጨዋታና ውድድር ጠንክሮ እንዲገኝ፣ ቁስሉም በቶሎ ሽሮለት እንዲበረታ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡ የግርዘቱ ስርዓትም በሚፈፀምበት እለት ተገራዡ ወጣት ኮሶ /ጨሞ/ እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ ይኸ የሚሆነውም አንድም ተገራዡ በግርዘቱ ወቅት እንዳያስቸግር ጉልበቱን ለማድከም፣ ወይም በግርዘቱ ወቅት ተስቶት ከሆዱ አንዳች ነገር እንዳይወጣና እራሱንም ሆነ ቤተሰቡን እንዳያሳፍር ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን የኮሶ መጠጣት ስርዓት የሚፈፅመው ተገራዡ ብቻ ሳይሆን አይኑን እንዲይዝ የሚደረገውና በኋላም ሚዜው ሊሆን የሚችለው ጓደኛው ናቸው፡፡

ኮሶውንና ከከምባቶች ባህላዊ መጠጥ አንዱ የሆነውን ‹‹ሴሎ›› የተሰኘውን ከገብስ የሚዘጋጅ ጠላ በማቀላቀል ሲሰጣቸው ሁለቱም ድርሻ ድርሻቸውን ይዘው በቤቱ ውስጥ በተሰበሰቡት ሰዎች ፊት ይቆማሉ፡፡ በዚህም ወቅት የቤተሰቦቻቸውን ምርቃት ይቀበላሉ፣

‹‹መገላሴ ሀፉፎች ፊእ፣
ጊዳ ሀንት ፋል ...››
ከክፉ ህመም ይሰውርህ፣

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

ቁስሉን ቀለል ያድርግልህ እንደማለት ነው፡፡

በተጨማሪም ‹‹ኢርፎ›› የቃል መግባትና የስጦታ ጥያቄ ከቤተሰቡ ይጠየቃል፡፡ በዚህን ወቅት የሚሰበሰቡት ስጦታዎች ሁሉ ከብቱ፣ ሰንጋው ወዘተ. ለሰርጉም ሊሆኑ እንደሚችሉ በቃል ታሪክ አዋቂዎቹ ይገለፃል፡፡

ከዚህ በኋላ የተሰጣቸውን ሴሎ ከቀመሱና ካስቀመጡት በኋላ ኮሶውን በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርገው እንዲጠጡት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ከፈፀሙ በኋላ

‹‹ጤሞ አሌ ፍሾ፣

ጤሞ ደእሊት ፋሽ ...››

ኮሶ ቶሎ አሸረው፣ አትቆይበት እያሉ ያበረታቷቸዋል፡፡

በመቀጠልም ኮሶው ተመልሶ እንዳይወጣና በቶሎ ወደ ሰውነቱ ለመግባት እንዲችል ቤተሰቡ ሁሉ በአንድነት ‹‹ሁርቡ ... ሸባ፣ ሸባ›› እያሉ በመዝለልና በመጨፈር አንድም የዝምታውን፣ የምሬቱን፣ ድባብ ለመግፈፍ፣ አንድም ዘና፣ ለማድረግና በድል መጠናቀቁን ለማመልከት ይሞክራሉ፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ - ከስዓታት በኋላ ተገራዡ የመገረዣ ስፍራውን ይይዛል፡፡ አብሮት ኮሶ የጠጣውን ጓደኛው ዓይኖች በጨርቅ በመሸፈን (ዓይኖቹን በመያዝ) ሲተባበር፣ ሌሎች የፈረጠሙ ጐረምሶች ደግሞ የተገራዡን እግሮች ግራና ቀኝ ወጥረው በመያዝ ለገራዡ ሰው ያዘጋጁለትና ግርዘቱ ይፈፀማል፡፡ ግርዘቱ እየተፈፀመ መሆኑን ለማመልከት እና የተገራዡን ጩኸትም እንዳይሰማ ለማገድ ጎረምሶቹ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ‹‹ሜ ... ባባንት›› እስቲ ትፈራና የሚሉትን ዘፈናቸውን በመጫወት ይጨፍራሉ፡፡

በዚህ መልኩ ግርዘቱ እንደተፈፀመ ተገራዡን ወደተዘጋጀለት መኝታ በመውሰድ ያስተኙታል፡፡ እስከ አምስት ቀናት ከቆየበት መኝታ ላይም ይነሳና በተለይ ወደተዘጋጀለት ክፍል - የማገገሚያ ክፍል - እንዲገባ ይደረግና ለእሱ በተለይ የተዘጋጀለትን ምርጥ ምርጡን ምግብ እንዲመገብና በቶሎ እንዲያገግም እንክብካቤ ይደረግለታል፡፡ በዚህ ልዩ እንክብካቤ ወቅት ከወላጆቹ ‹‹ሙላ››፣ ‹‹ሀንቀሎ››፣ ጭኮ እና ቦርዴ የመሳሰሉ ባህላዊ ምግቦች በጥሩ ሁኔታ ተዘጋጅተው ይቀርቡለትና ይመገባል፡፡ በእድሜ እኩዮቹና በጓደኞቹ ደግሞ የተለያዩ ስጣታዎችን እያመጡለት ይጠይቁታል፡፡ ይጐበኙታል፡፡ ሴቶቹ ሎሚ በማምጣት ይሰጡታል፡፡ ይኼ የመመራረጫ ወቅትም ይመስላል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በዚህ ዓይነት እንክብካቤ የሚቆየው እስከ ጥቅምት ወር ድረስ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሀሉ ባለው የመስቀል በዓልም ምክንያት በሚደረገው እርድ የሚገባው ስጋ በዛ ያለ ስለሚሆን ቶሎ ለማገገም እንዲረዳው ሲባለ ነው ይህን ያህል መቆየቱ፡፡ ከዚህ ቆይታ በኂላ ግርዘኞቹ ወደ ውጪ የሚወጡበትና ከጓደኞቻቸው ጋር መተያየት፣ ከሴቶች ጋር የሚፈላለጉበት አጋጣሚ ይጠብቃቸዋል፡፡ ሴቶቹ ስንደዶ ለቀማ ይወጣሉ፡፡ በልባቸውም የሚለክፏቸውንና አፍቃሪያቸውን የወደፊት ውሃ አጣጪያቸው ሊሆን የሚችለውን ጎረምሳ እያሰቡ ነው፡፡ ወንደቹም ‹‹ገሚሻ›› ለሚባለው ውድድር የሚዘጋጁበት ትግልና ጥልፍልፍ የሚለማመዱበት ወቅት ይመጣል፡፡ በዚህ ውድድር ግርዘኞቹ የሚሞገሱበት፣ ጥንካሬያቸው የሚመሰከርበት እና የሚመሰገኑበት ወቅት እንደሆነ ይገለፃል፡፡ የኃይለ ዳንኤል ጽሁፍ (1986፣ 320) እንደሚያመለክተውም ወንዶቹ ግርዘኞች ሴቶች ግርዘኞችን የሚጐነታትሉባቸው የ‹‹ሉባ›› ጨዋታ አለ፡፡ በዚህ ጨዋታ ወንዶቹ በአውራጁ መሪነት የሚጫወቱት ሲሆን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| አውጪው | ተቀባዮች |
|---|---|
| <u>በከምባትኛ</u> | <u>በከምባትኛ</u> |
| ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ሀይ ሉባ ዩሐማሜ ሉቢችዬ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ባጁ ዋልቶዳ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ባጂታ ደዶዳ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ሎሚታ አቶዳ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ሾንኮሪን በሉዩ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| <u>በአማርኛ</u> | <u>በአማርኛ</u> |
| ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ሉባ እሹቴ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ሳዱላዋ ብትመጣ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ከላሣ ተሰርታ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ሎሚ ብትሰጠኝ | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |
| ደግሞ ሸንኮራም | ሀይ ሉባ፣ ሀይ ሉባ |

ምንጭ፣ ፍሬሀይወት፣ 1997

በዚህ እና በለሎችም የግርዘት ጨዋታዎች የሚታየው ትወና ከዚህ በፊት ከተመለከትነው አተዋወን ብዙም የሚለይ አይደለም፡፡ በጥልፍልፍ ጨዋታ ጊዜ የሚታየው ጨዋታ ግን በመጠኑ ልዩነት አለው፡፡ ወንዶች ልጆች ሙሉ ቁጥር 8-8 ወይም 6-6 ሆነው በተቃራኒ አቅጣጫዎች እንዲሰለፉ ይደረጋል፡፡ በሁለቱ ተፋላሚዎች መካከል ላይ ድንበር እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ ከዚያ ያንን መለያ መስመር ሳያልፉ የተቃራኒውን ቡድን አባል በመያዝ ታግሎ ወደራሱ ክልል እንዲመጣ ማድረግና መጣልን ያካተተ ጨዋታ ነው፡፡ የተቃራኒው ቡድን አባል መስመሩን እንዳለፈና ተጠልፎ እንደወደቀ የጨዋታው አሸናፊ ታውቆ መጠላለፉ ያበቃል፡፡

ምስል 10 የግርዛት ወቅት አጨዋወት



በሌላም መልኩም በትር መስል በመሃከላቸው በማድረግ የሚጫወቱት የትግል አይነት አለ፡፡ በዚህ ጨዋታ ተቃራኒዎቹ ቡድኖች ለበትሯ ቀርበው ይቆሙና ‹‹እኸ … እኸ… እኸ …እኸ›› በማለት ከወገባቸው ዝቅ በማለት ወደ በትሯ ያጐነብሳሉ፡፡ በአንድ እጃቸውም ወደ በትሯ በማመልከት ድንበራ … ድንበራ … ሂባ … ሂባ …በማለት አንደኛው ወገን ሌላኛው በማዘናጋት ጠልፎ ለማምጣትና ለመጣል የሚደረግ ፉክክር ነው፡፡ በዚህ ጨዋታ ጠንካራ፣ ብልጥ የሆነውና በግርዘቱ ወቅት በሚገባ የተቀለበው ተገራዥ ይለይበታል፡፡ ታዳሚውም ትእይንቱን በማየት የሚደሰትበትና የሚዝናናበት በመሆኑ ተወዳጅ የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ ውድድር አሸናፊውም ሆነ ተሸናፊው ተሳስቀው፣ ተቀላልደው የሚለያዩበትን እንጂ ቂም አይያያዙበትም፡፡

### 5.5 የሠርግ ወቅት አተዋወን

በከምባታ ብሔረሰብ ውስጥ ትዳር በልዩ ልዩ መንገዶች እንደሚፈፀም ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ዋናዎቹ አራቱ ‹‹ቆርሲሽታ››፣ በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተና በወግ በማእረግ የሚፈፀም፣ ‹‹ሄረንቻ››፣ በስምምነት ወይም ተባብሎ ተያይዞ በመጥፋት



ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

የሚፈፀም የኩብለላ ጋብቻ፣ ‹‹ሜዱ›› ጠለፋ እና ‹‹ረጊታ›› ውርስ የሚባሉት ናቸው፡፡ (ፍሬህይወት፣ 1997፣ 104) ፍሬህይወት በዚህ ጥናቱ ውስጥ እነዚህን ከነባህሪያቸው ዘርዝሮ አቅርቧቸዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ይህንን ደግሞ ከማቅረቡ ይልቅ ትወናቸው ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡

የሠርግ ወቅት ዳንሶች፣ በአጠቃላይ ሲታዩ ዜማዊ ቅላፄያቸውን ከአካላዊ እንቅስቃሴና ውዝዋዜ ጋር አቀናብረው የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍልም የከምባቶቹን መለያና የጋራ የሆኑ ባህሪያቸውን፣ ፍቺዎቻቸውንም ለማመልከት ጥረት ይደረጋል፡፡

በከምባታ የሠርግ ወቅት ዳንሶች ላይ የውዝዋዜው አይነት፣ የሚቀርብበት ጊዜ፣ ተዋኞቹ፣ የሚተውኑበት ሁኔታ፣ የትዋኔው ደጋፊዎች፣ የውዝዋዜው ስልቶች እና አፋዊ ወይም አካላዊ ምላሽ እና የሙዚቃ መሳሪያዎቹ ድጋፍ አብረው የሚታዩ ነገሮች ናቸው፡፡ በሠርጉ ወቅት የሚተወኑት ዳንሶች የዳንሱን፣ እና የማህበረሰቡን አፋዊ ቋንቋ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ የሚቀርቡትም ለተወዛዋዦቹ ለራሳቸው እርካታ፣ ለተሳታፊዎቹ ወይም ለታዳሚዎቹ ደስታን ለማጉናፀፍ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ለልእለ ሃይላቱና ለፈጣሪዎቻቸውም ደስታቸውን መግለጫ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሀገረሰባዊውን የሠርግ ወቅት ዘፈን፣ ዳንስና ትእይንት ከተመለከትን ልእለ ሃይላቱንና የመንፈሳዊውን ዓለም ሃያላን ለማስደሰት የሚቀርቡበት አጋጣሚም አለ፡፡ ምክንያቱም በሀገረሰብ እምነቱ መሰረት ሚስትን (ባልን) ፣ ልጅን፣ ሃብትን፣ ወዘተ.የሚሰጡ ተደርገው የሚቆጠሩት እነዚሁ ሃይላት በመሆናቸው በትወናውም ላይ ይህ ይንፀባረቃል፡፡ ትወናዎቻቸውም የተቀደሱ ናቸው የሚባሉትን እነዚህን ሃይላት እና በዙሪያቸው የታደሙትን የማህበረሰቡን አባላት የሚያገናኙ ተደርገው ይታያሉ፡፡

ስለሆነም በሀገረሰባዊ ሠርግ አተዋወን ላይ ሁለት መሠረታዊ ተግባራት ሲፈፀሙ ይታያሉ፡፡ እነዚህም ትእንግርታዊ ተግባራትና ማህበራዊ ተግባራት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ደናሾቹ የተለያዩ የአደናነስ ክሂሎችንና አካላዊ ብቃትን አሳይተው ታዳሚዎቻቸውን ሁሉ ሲያስጨፍሩ ይስተዋላሉ፡፡ በከምባቶቹ ባህል ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሠርግ ወቅት አጨፋፈርን በማሳየት ረገድ በተለይ ከወንዶቹ ብዙ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ወንዶቹ በውዝዋዜዎቻቸው ውስጥ ወንዳዊ ተግባራትን፣

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በተለይም ወሲባዊ ሁኔታዎችን አመላካች የሆኑ ተምሳሌታዊ እንቅስቃሴዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋልና ነው፡፡በዚህ ወቅት ትወናቸው ወንዶቹ ወገባቸዉን ወደፊት ወደኋላ ወሰድ መለስ በማድረግ፣አንገታቸውንና ትከሻቸውን ደግሞ በመስበቅና በማርገፍገፍ እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ ከመቀመጫቸው አካባቢ ውዝዋዜ ጋር አስተካክለዉ ከግብረ ስጋዊ ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ ሲጨርሱም አንድ እግራቸውን በማንሳትና መቀመጫቸውን ወደፊት በመወርወር ነው፡፡ ሴቶቹም አንገታቸዉን ወደቀኝ ቀለስ በማድረግ፣ዓይኖቻቸውን በማስለምለም፣አንገታቸውን በለሆሳስ በማንቀሳቀስ የሚመለከታቸውን ተመስጦ ውስጥ እንዲገባ ያደርጉታል፡፡

ሀገረሰባዊ የሰርግ ስነስርዓት ላይ ለሙሽራዋ የሚቀርበው የሠርግ ወቅት ዳቦ የተለየ ትርጓሜ ያለው ነገር ነው፡፡ ይህ ዳቦ በተለይ የሚጋገር ሆኖ፣ በልዩ እቃ የሚቀርብ ነው፡፡ ቅርጹ ክብ ሲሆን የፀሃይ ትእምርት ነው፡፡ ተምሳሌቱም መራባትን፣ መፀነስንና መውለድን፣ ለተጣማሪዎቹ ጥንዶችም የደስታ እና የብልፅግና ዘመን መመኘትን ያመለክታል፡፡ ፀሀይ ክብ ሆና ከአንደኛው አድማስ ስተወጣ፣ ካለመኖር - ወደ መኖር፣ ካለመታየት ወደ መታየት፣ ያላት ገፅታ ብሩህነት ነው ተምሳሌቱን ያጕላው፡፡ በሌላም በኩል ዳቦው የተፈጥሯዊውን የዘር-መተካት ሂደት ዳግም ፈጠራ ሂደት - መራባትን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

በዚህ ወቅት በሚጨፈረው ዳንስ ላይ ዋናዎቹ ተዋናያን ያገቡ ሴቶች ናቸው፡፡ ትወናቸውም መዝለልን፣ በክብ መስመር መዞርን፣ ያካትታል፡፡ ልክ የዳቦው ሊጥ ሲቦካ ከታች ወደላይ እየነፋ እንደሚሄደው ያለ ትእንግርት ነው የሚጨፈረው፡፡ ይህ ከታች ወደላይ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ከምባቶቹ ልጅ ሲወለድም እንደሚጫወቱቱ አስቀድሞ የተገለፀ ጉዳይ ነው፡፡ እንደዚህ ያለውን እንቅስቃሴ ነው ከትእንግርታዊ ተግባር ጋር እያስተያየን ለማየት የሞከርነው፡፡ ይህንን እንቅስቃሴ አምንተዊ አድርገን ከተረጐምነው፣ ሰው ከፈጣሪው ጋር፣ ሰው ከልእለ ፍጡራን ሃይላት ጋር፣ ያለውን ግንኙነት የሚወክሉ አድርገን መውሰድ እንችላለን፡፡

ሌላኛው ዓይነት ትእንግርታዊ ዳንስ በሠርጉ የዋዜማ ምሽት የሚተወነው ነው፡፡ በዚህ ምሽት ሙሽሪትን ሚዜዎቿ ከበዋት እሷን መሃል አድርገው በቤቱ ውስጥ እየዞሩ የሚጫወቱት ነው፡፡ ይህንንም ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ ከተመለከትነው ሙሽሪትን ከከበቧትና ሊተናኰሏት ይችላሉ ከሚባለው ሁሉ የመከላከል፣ የመጠበቅ፣ የመጋረድ

ተግባር ጋር ልናያይዘው እንችላለን፡፡ በተጨማሪም የጫጉላዋ ማለትም ሙሽሪትን ቀድሞ ከነበረችበት የድንግልና ህይወት የምትለይበት፣ ዘሯን ቀብራ ከቆየችበት የብቻነት ህይወት የምትላቀቅበትም ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ በአንፃሩም ከወላዱ ማህበረሰብ የምትቀላቀልበት፣ የእሷ ዳግም ልደትም ነው፡፡ በእርግጥ በሃይማኖታዊው ስርዓትም በቤተክርስቲያን የሚፈፀመው የተክሊል ጋብቻ፣ የሻማ ማጥፋትና ማብራት ስርዓቱ የተጣማሪዎቹን ጥንዶች ፅምረት የሚያመለክት ተምሳሌት ተደርጐ ከዚህ ጋር ሊተያይ የሚችል ነው፡፡ ከዚህ ባሻገርም የማህበረሰቡን ድጋፍ፣ ለጋብቻ ያለውን ከበሬታና ጥበቃ አመላካች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡በጫጉላው ምሽት የሚተወነው ሌላው ትእይንት ሙሽሮችን በመሀል አድርገው የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡ በዚህ ጨዋታም ሁሉም ዙሪያቸውን ከበው እየጨፈሩ፣ ሙሽሮችን ይሸኛሉ፡፡

በከምባታ ሀገረሰባዊ የሠርግ ስርዓት ላይ ዳንሱ በሠርጉ እለት፣ ምሽቱንና ተከታዩ ቀን ድረስ የሚዘልቅ እንደሆነ የታሪኩ አዋቂዎች ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ በመሀሉ አነስተኛ እረፍት እየተደረገ ነው፡፡ በአጫጭሮቹ እረፍቶች መሀከልም የምግብና የመጠጥ መስተንግዶው አይቋረጥም፡፡ በድሮ ጊዜ ባህላዊው መጠጥ ሴሎ ብቻ ይቀርብ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ በጨዋታዎቻቸውም ወላጆችን መመረቅና ማወደስ የተለመደ ነው፡፡ በዚህ የተደሰቱ ወላጆችም አፀፋውን ሽልማትና ምርቃት ያቀርባሉ፡፡

ኤል! ስር! ኢትልክበቡ!

እንቁታ ኢትሌን ጦፍ!

(ውለጂ፣ ክበጂ ላምነትሽ ይሽተት፣

ጥርስሽን በላምነት ጨርሺ) እያሉ ይመርቃሉ፡፡ ሁሉንም፡፡

በጫጉላው ቤት የሚደረገውን ግብግብ ለማፈንና በተጓዳኝም ደስታቸውን ለመግለፅ ሙሽራውና ሙሽሪት የሚገኙበትን ‹‹ቆንቆኖ›› ጫጉላ ቤት በሩን በመክበበ አይ ‹‹መኒ ሻለታ!›› ‹‹ኒመኒ ሽለታ›› አይ የሰው ጨዋታ! የኛ ሰው ጨዋታ እያሉ ያዜማሉ፣ ይጨፍራሉም፡፡

ከምባቶች የሠርግ ዘፈኖቻቸውን የሚያቀርቡትና የሚደንሱት በቀለበት ቅርፅ ክብ ሠርተው ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሽሮቹን በሰዎቹ መካከል ያደርጓቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ደናሽ በግራው እና በቀኙ ካሉት ተጫዋቾች ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ ወይም አንደኛው በሌላኛው ትከሻ ላይ እጁን በማሳረፍ፣ ወይም አንደኛው የአንደኛውን ወገብ በእጆቹ በመያዝ ነው፡፡ ይህ በአንድ በኩል አንዱ ለሌላኛው ያለውን ፍቅር፣ አሳቢነት፣ የመንፈስ

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

አንድነት ሲያመለክት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ለሙሽሮቹ ያላቸውን ድጋፍ፣ እነሱን ለመጠበቅ፣ ለመርዳት፣ ለመጋረድ ያላቸውን ፍላጐት አመለካች ነዉ። ቀለበቱ በሌላ መልኩ ከተተረጐመ በቀለበቱ ውስጥ ያሉት ከቀለበቱ ውጪ ከሚገኙት የተለዩ መሆኑን እነሱ ግን የተዋሀዱ የተሳሰሩ መሆኑን የሚያመለክት ተደርጐ የሚተረጎም ነው። እንዲሁም በክቡ ውስጥ የሚገኘው ስፍራ እንደተቀደሰ ስፍራ ተደርጐም ሊወሰድ ይችላል። ‹‹ጋብቻ ክቡር ነው›› የሚለው የመፅሃፍ ቅዱስ ጥቅስም ከዚህ ጋር ይተያያል።

በዚህ ዝግጅት ላይ የታደሙ የሰርጉ እድምተኞች ሁሉ የሚመሰክሩት ሙሽሪት በሠርግ ወቅት ትእይንት ላይ የሁሉም ዓይን ማረፊያ መሆኗን ነው። ሁሉም ትወናዎች ሙሽሪት አምራና ተውባ፣ በልዩ ሁኔታ ደምቃ፣ በአጀብ ተሞልታ፣ ወደ ሌላ ህይወት፣ ወደመራባት ህይወት፣ መሸጋገሯን የሚያበስሩበት አጋጣሚ ተደርጐ ይወሰዳል።በሠርጉ እለት ሙሽሪት ራሷን ለባሏ ካስረከበችበት ሰዓት አንስቶ በባሏ ስልጣን ቁጥጥር ስር መግባቷን፣ ከዚህ በኋላ የእናት የአባት ቤት ቀርቶ ከባሎቿ ወገኖች ጋር የምትቆጠርበት ሥርዓት መጀመሩን አብሳሪም ናቸው። ሙሽሪት የመጀመሪያ ልጇን እስከምትወልድ ድረስም በቆንቆኖ ውስጥ እየተቀለበች የጎጆ መውጫዋን ማሟላት ይጠበቅባታል። ራስን የመቻል የመጀመሪያ እርምጃ። ከዚያም የባሏን ወገኖች ስሞች በማጥናት፣ የቤቱን ስርዓት በመማር ተግባር ትጠመዳለች ማለት ነው።

### 5.6 በሀዘን ወቅት አተዋወን

የከምባታ ብሔረሰብ ከሞት ወቅት ጋር የተያያዘውና የሀዘን ስርዓቶቹ የመተወኛ አጋጣሚ የሚጀምረው የብሔረሰቡ አባል የሆነው ሰው ለሞት በሚያበቃው አስጊ ሁኔታ ላይ ከወደቀበት ጊዜ አንስቶ ነው። ከምባቶች ለሞት የሚያበቃው ነው ብለው በሚያስቡት ደረጃ ላይ የደረሰን ሰው ዝም ብለው አያዩትም። ይልቁንስ የኑዛዜ ስርዓት እንዲፈፅም ያደርጉታል። ይህንን የኑዛዜ ሥርዓት የሚፈፅሙትም አንድም በታማሚው በራሱ ጥያቄ መሠረት አልያም በዘመድ አዝማድና በቅርብ ወዳጆቹ ጥያቄ - ጉትጐታ - መሠረት ሊሆን ይችላል። ታማሚው ራሱ አስቦበት የኑዛዜ ስርዓቱን መፈፀም እፈልጋለሁ ብሎ ካሳወቀ ቤተዘመዶቹንና የቤቱን ሰዎች እንዲሰበሰቡለት ይጠይቃል። በጥያቄው መሠረትም ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ ከስጋ ልጆቹ እስከ ማደጎ ልጆቹ፤ ይምጡልኝ ያላቸው ሰዎች ሁሉ እንዲሰበሰቡለት ይደረጋል። ለዚህ ስርዓት

ማስፈፀሚያም ባህሉ የሚያዘው ማር ለተናዛዡ ሰው ይቀርብለታል፡፡ ከዚያም ከዚህ የሚከተለውን ምርቃት ይሰጣል፡፡

| በከምባትኛ | በአማርኛ |
|---|---|
| እሩ ባዱ ጡማ እሁን | - አገር ሠላም ይሁን |
| ጡሚ ጤና ጡሚ አርቹታ አሱ | - የሠላም ዝናብና ፀሀይ ይስጠን |
| ጐሩ ከልመት በኡ | - ረሃብና እርዛት ይጥፉ |
| ኤሳች አባ ሄኢዬ | - ከእኔ የበለጠ እድሜ ይስጣችሁ |
| እለ ጠቅዬ ፍካኒዬ | - ውለዱ ክበዱ በልጽጉ |
| እልቴንታ ሌኡ፣ ጠቅወቴንታ ሆሩ | - ልጆቻችሁ ይደጉ ርቢያችሁ ይብዛ |
| ገንሹ ደሙሚት በኡ | - ጉንፋንና ራስ ምታት ይጥፉ |

በማለት ምርቃትን ያወርዳል፡፡ ተመራቂዎቹም አሜን፣ አሜን በማለት ይቀበሉታል፡፡ ይህንን ለመቀበል የማይችል አራስ ልጅ ካለ ወላጆች /ታላላቆቹ/ እንዲቀበሉለት ይደረጋል፡፡ ምርቃቱን ከሰጠ በኋላ በመቀጠል የነበረውን ሀብት በህይወት ላሉት ወራሾቹ ክፍፍል ያደርጋል፡፡ ለዚህም እማኝ የሚሆኑትን፣ ተዓማኒነት ያላቸውን አረጋውያንና የእምነት አባቶች በማቆም ነው፡፡ ከዚያም ለእራሱ የቀብር ስነስርዓት ማስፈፀሚያ የሚያስበውን ያህል ያስቀርና ክፍፍሉን ያደርጋል፡፡ በዚህ ክፍፍል ወቅት ሴቶቹ ወራሾች ከመሬት ድልድል ውስጥ አይገቡም፡፡ በውርስም የሚተላለፍላቸው መሬት የለም፡፡ መሬት ለወንዶቹ ብቻ የተተወ ነው፡፡

በመጨረሻም ኑዛዜውን ሲያጠናቅቅ ውርስ የተሰጣቸውን ወራሾችን በሙሉ በሽማግሌዎቹ እና በእምነት አባቶች ፊት እንዲቆሙ በማድረግ እሡ በሰጣቸውና በተናዘዘላቸው መሠረት ተከባብረውና ተስማምተው እንዲኖሩ አደራ በማለት ቃል እንዲገቡለት ያደርጋቸዋል፡፡ ቃላቸውን እንደሰጡትም የገቡትን ቃል አፍርሰው ቢገኑ፣ የእሱ እጣ እንዲደርስባቸው በመራገም ኑዛዜውን ያፀናል፡፡ ይህንን ከፈፀመ በኋላ በቀብሩ ሥነስርዓት ላይ የሚገኙት እንግዶች እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸው፣ የቀብሩ ስርዓትም እንዴት መፈፀም እንዳለበት ያስረዳል፡፡ ከዚያም ህዝቡን ይመርቃል፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ የተገኙት አረጋውያንና የእምነት አባቶችም በተራቸው አምላክ ምህረቱን እንዲለግሰው በመመኘት ይሰናበቱታል፡፡ ህይወቱ እንዳለፈችም የግርዘት ስርዓት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

እንዲፈፀምለት ይደረጋል፡፡ ይህ ከተከናወነ በኂላ ቀጣዩ ሂደት የለቅሶ መላላክ ስርዓት ነው፡፡

ምስል 11 ጌዳ ነጋሪዎች



ምስል 12 ባህላዊ ቀረርት



ታማሚው ሰው ነፍሱና ስጋው ከተለያየችበት ጊዜ አንስቶ በተቻለ ፍጥነት ዘመድ አዝማዶቹ ሁሉ እንዲሰሙ መደረግ አለበት፡፡ ምክንያቱም የዘመዳቸውን ሞት ያልሰሙት ዘመዶች የሚበሉት ምግብ የ‹‹ደም ምግብ›› ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ የለቅሶ መላላክ ስርዓት በሁለት መንገድ ሊፈፀም ይችላል፡፡ የመጀመሪያው በሟቹ ሰው የአካባቢው እድር /ሙርቴ ሄራ/ አማካይነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሟቹ ጀግና ወይም ታዋቂ ሰው ከሆነ ከሙርቲ ሄራው በተጨማሪ ‹‹ለሳኖ›› በሚባሉት የመርዶ አዋጅ ነጋሪዎች አማካይነት ነው፡፡

ሙርቲ ሄራው የመላላኩን ሃላፊነት ተቀብሎ በሩቁ ለሚገኙ የሟች ዘመዶች መርዶ ነጋሪ ይልካል፡፡ ለቀብሩ የሚመጡ እንግዶችን መቀበል፣ ለመስተንግዶ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሁሉ የማሰናዳት፣ መመገብና የሟችን ቤተሰብና ቤተዘመድ የመንከባከብ ሃላፊነትም ጭምር አለበት፡፡ ለሳኖ የሚባሉት ደግሞ በየአካባቢውና በተጐራባች ቀበሌዎች፣ በገበያዎችና ህዝብ መሰብሰቢያዎች እየዞሩ እንዲያውጁ ይደረጋል፡፡ ‹‹ለሳኖ›› የሚባሉት ሰዎች የሚመረጡት ከሟች ጐሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ከሌላ ጐሣ ወገን ሊሆኑም ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሽለላ፣ በፉከራና በዘር ሀረግ ቆጠራ ታዋቂ ሊሆኑ የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም ለሳኖዎች የሚቹን የዘር ግንድ፣ የሀብቱን ብዛት፣ የፈፀማቸውን ጀብዱዎችና የነበረውን ስልጣን ሁሉ እየዘረዘሩ መንገር ስለሚጠበቅባቸው ነው፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

ለሳኖ የሚባሉት ሰዎች በባህሉ መሰረት በፈረስ ላይ ተቀምጠው፣ የነብር ቆዳ ለምድ ለብሰው፣ እና የንስር ላባ በፀጉራቸው ላይ በመሰካት፣ ጋሻና ጦሩን በመያዝ ነው ለቅሳውን የሚያውጁት። ለቅሶውን ለማወጅ በፉከራና በሽለላ እንደሄዱት ሁሉ ሲመለሱም በሽለላና በፉከራ ነው። የት ድረስ ደርሰው እንደመጡም የሚገልፁት በተመሳሳይ መልኩ በሽለላ ነው።

ምስል 13 … የለቅሶ አዋጅ ነገራ



በለቅሶው ወቅት ሀዘንተኞቹ ሚቹን ለመሰናበት እንደተሰበሰቡ ለለቀስተኛው ሁለት ትላልቅ ከበሮዎች /ነጋሪት/ ይቀርባሉ። ሁለቱም ከበሮዎች የተለያዩ ሲሆኑ ድምፃቸውም የተለያየ ነው። እነዚህን ከበሮዎች እንዲጫወቱ (እንዲመቱ) የሚጠሩት ፉጋዎቹ ሲሆኑ በተለየ ክፍያ፣ በምግብና በመሳሰሉት ነገሮች ዋጋ ተተምኖላቸው ነው። ነጋሪቱን በሚጉስሙበት ጊዜ ሴት አልቃሾች፣ ከነጋሪቱ ድምፅ ጋር እንቅስቃሴያቸውን በማስተካከል የለቅሶ ውዝዋዜ ያሳያሉ። በዚህ ውዝዋዜ ወቅትም ነጋሪቱ ፊት ለመድረስ ሴቶች አንገታቸውን በማሾር፣ እጃቸውን በማወዛወዝ፣ ወገባቸውን በመስበቅ የሚያሳዩት ውዝዋዜ ከፍተኛ ትእይንት ይፈጥራል። አንደኛዋ ቀድማ ስትሔድ ሌላኛይቱ ደግሞ እሷን ለመቅደም የምታደርገው የሰውነት እንቅስቃሴ ያስደንቃል። ወጣቶችም ከሴቶች ጋር በተመሳሳይ የሚያሳዩት የአለቃቀስ ዘይቤ ‹‹ነጋሪተ ሂጉ›› ከፍተኛ መስህብ ያለው ነው። ይሄ ወደ ነጋሪቱ መሄድን ገትተው፣ ወንዶቹ በአንድ ተርታ ሴቶቹም ባንድ ተርታ ተሰልፈው ፊት ለፊት እየተያዩ የሚያዜሙት ዜማ እና የሚተውኑት ክዋኔ ልዩ ስሜት የሚፈጥር ነው። በዚህ ወቅት የሚዜመው የለቅሶ ዜማ፡-

| በከምባትኛ | በአማርኛ |
|---|---|
| ሆ … ሆ … ሆ … ሞራ ኣዬ | ሆ … ሆ … ሆ ወይኔ ጀግናዬ |
| ሆ … ሆ … ሆ … ሞራ ኣዬ | ሆ … ሆ … ሆ ወይኔ ጀግናዬ |
| ሆ … ሆ … ሆ … አዬ ሞራ | ሆ … ሆ … ሆ ጀግናዬ ወይኔ |
| ሆ … ሆ … ሆ … አዬ ፋሽአና | ሆ … ሆ … ሆ ወይኔ ባለፈረስ |

ሆ … ሆ … ሆ … ሠንግ አና አዬ ሆ … ሆ … ሆ ባለ ሠንጋ ወይኔ

እየተዜመ በመሀሉ እየገቡ ሁለት ሁለት በመሆን የሚቹን የጀብዱ ስራዎች የሚተርኩ ታዋቂ ሰዎች ይገባሉ፡፡ እነዚህ በባህሉ ‹‹ጌዳ›› ነጋሪዎች ሲናገሩ ለቀስተኛው ሁሉ ምርር ብሎ እንዲያለቅስ የማድረግ ችሎታ ያላቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ትወና ወቅት ጌዳውን ሲናገሩ ከተሳሳቱ ሌላ ታሪኩን፣ የጀግንነት ገድሉን የሚያውቅ ሰው በመሀል ገብቶ አስተካክሎ ማለት ይቻላል፡፡ ሟች ጀግና ከሆነና ባለብዙ ገድል ከነበረም የለቅሶው ትወና ከዚህ ከበድ ብሎ ሊደረግ ይቻላል፡፡ በዚህ የ‹‹ኦነታ›› የለቅሶ ስርዓት ወቅት ሟቹ የተከበረ ሰው ከነበረ የሚተወነው ‹‹ዶዬኮ›› የተባለው የለቅሶ ስርዓት ነበር፡፡

በዚህ ስርዓት የሟቹ ሰው መቀመጫ የነበረው ፈረስ ወይም በቅሎ፣ በወግ እቃ ተሸልሞ በአንድ በኩል እንዲቆም ይደረጋል፡፡ ሚስቱ ወይም ሚስቶቹ-ከአንድ በላይ ሚስት ከነበረው-ከተሸለመው ፈረስ በመቀጠል ይቆሙና ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡትን ለቀስተኞች ይጠባበቃሉ፡፡ ከእነሱና ከፈረሱ አጠገብም ሟች ገድል በፈፀመበት ልክ ጦሮች ይሰካሉ፡፡ ከዚያም ከአንዱ አቅጣጫ በፈረስ እየጋለቡ የሚመጡ ለቀስተኞችን የምትቀበለው የሟች ሚስት ደረቷ ተገልጦ፣ በሁለት እጆቿ እሾህ ይዛ ወደነሱ ታመራለች፡፡

በዚህ ወቅት በእጆቿ በያዘችው እሾሆች ግራና ቀኝ ጉንጯን በመሚጨር ነው፡፡ እጆቿን ወደ ላይ፣ ወደ ታች በማድረግ ደጋግማ እጆቿን እያመላለሰች፣ ደጋግማ ጉንጮቿን እየሚጨረች፣ ከጉንጮቿ የሚወጣው ደም እየወረደ፣ ወደ ሰዎቹ ታመራለች፡፡ በአንገቷ ቀደም ሲል የነበረው የወጋ ነቀል ዓይነት ስልት እንዳለ፣ የወገቧ እንደ እንዝርት መሾር ሳይቀንስ መንዝዝ ይጠበቅበታል፡፡ እየመጡ ያሉት ፈረሰኞችም ‹‹ሞራ ሆይ›› … ‹‹ሞራ ሆይ›› … ‹‹ጀግናዬ›› … ‹‹ጀግናዬ›› … እየሉ ሟችን እያወደሱ ነው የሚቀላቀሉት፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በሁሉም አቅጣጫዎች የሚመጡት ለቀስተኞች በዚሁ ዓይነት አቀባበል ትቀበላለች፡፡ በእርግጥ እንደዚህ ዓይነቱ የለቅሶ ስርዓት በአሁኑ ጊዜ የተወገዘ እና የቀረ እንደሆነ ይገለፃል፡፡

በዚህ መልኩ ለለቀስተኞቹ አቀባበል ከተደረገ በኋላ ነው የቀብር ስነ ስርዓቱ የሚከናወነው፡፡ የቀብር ስርዓቱን ለመፈፀም ለዚህ ተብሎ የተለየውን ስፍራ ማሳየት የሚች ታላቅ ልጅ ተግባር ነው፡፡ ታላቅ የሆነው ልጅ ለአባቱ መቀበሪያ የተለየውን



ADDIS ABABA UNIVERSITY
IES LIBRARY

ስፍራ በጦሩ በመውጋት ያሳያል። ይህን በሚያደርግበት ጊዜ የመቀበሪያውን ቦታ በግራ እጁ በያዘው ጦር ሦስት ጊዜ በመውጋት ነው። በእያንዳንዱ ውግ ጊዜም ከአባቱ ንብረቶች አንዳንድ እየጠራና የተሰበሰበው ሁሉ እየሰማው በዚህ ንብረት ስም ወጋሁ እያለ ነው። በዚህ አይነት የተጠሩት ሦስት ንብረቶችም የእሱ ሆነው እንዲቀሩ ባህሉ ያዛል። በዚህ ስፍራም የቀብር ስነስርዓቱ ይከወናል። ቀብሩ ከተፈፀመበት ቀን ከ‹‹በካራ›› ጀምሮ በሟቹ ሰው ደጃፍ ሀዘን ይቀመጣሉ። በቀብሩ ወቅት ያልተገኙና ያልቀበሩ ሰዎችም እዚህ እየመጡ ሃዘናቸውን መግለፅ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ሲመጡ ወደ ሀዘንተኛው ቀረብ ብለው ‹‹ግድ ሴንተሩ ግዱን›› ‹‹መገኑ ሰበራ አስኩኜ›› በማለት ነው። ተቀባዩም ‹‹ሂሊታ ጡዴኖችዬ›› ክፉ አይድረስባችሁ በማለት ይመልሳል። ሀዘን ደራሾችም ለምን በቀብሩ ወቅት እንዳልተገኙ ያጋጠማቸውን ነገር በመግለፅ ይቅርታ መጠየቅ ይችላሉ። ይቅርታ ተቀብለውም ቡና ጠጥተው ወደ መጡበት ይመለሳሉ።

በከምባታ ብሔረሰብ የሀዘን ወቅት ማፅናናቱ ከወር በላይ ጊዜ ይወስዳል። የሟች ባለቤት (ሚስት) እና እህቶች ግን በዚህ ሀዘን ውስጥ ሆነው እስከ ሁለት ዓመት ሊቆዩ ይችላሉ። በዚህ ወቅት የሟች ሚስት በአልጋ ላይ አትተኛም፣ ጥፍሮቿ አይቆረጡም፣ ፀጉሯን አታበጥረውም፣ የቅባት ዘርም አጠገቧ አይደርስም። ከየትኛውም ማህበራዊ ግንኙነት እና ህዝባዊ ስብሰባዎችም ራሷን እንድታገል ባህሉ ያስገድዳታል። ይህ የሀዘን ወቅት ሲጠናቀቅም የሟቹ እህቶች አጥበው፣ ቀባብተው፣ ገበያ አውጥተው ካዟዟሯት በኋላ፣ ቦርዴ ያጠጧትና የሀዘን ወቅት ማብቃቱ፣ ወደ ተለመደው ማህበራዊ ኑሮ ለመመለስም እንደምትችል፣ ከሀዘኑ እስራት መፈታቷን ተረድታ ወደ ማህበራዊ ህይወት እንድትመለስ ይደረጋል። ይሄ በሴቶቹ ዘንድ የሚታየው የመረረ የሀዘን ስርዓት በወንዶቹ ዘንድ የለም። በለቅሶውም ላይ እንደሚታየው ዋነኞቹ ተዋኞች ሴቶቹ ናቸው። ከዚህ አንፃር ሴቶቹ ውስጣዊ ስሜታቸውን አውጥተው በመግለፅ ረገድ ከወንዶቹ የተሻለ መሆኑን ያመለክታል።

የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከልዩ ልዩ ልማዶች ስርዓቶችና ሀገረሰብ ሃይማኖት አንፃር የሚኖራቸውን ማህበራዊ ተግባራት ደግሞ ቀጥለን እንመልከት። ባህል የተለያዩ ፍላጐቶች፣ አስተሳሰቦች፣ በልዩ ልዩ ነገሮች ላይ ያሉን መረዳቶች (በሰው፣ በቁስ፣ በመንፈስ) እና የበርካታ ባህሪያትም ጥርቅም ውጤት እንደመሆኑ መጠን የቀደመው ትውልድ ለተከታዩ ትውልድ እነዚህን እሴቶች ከሚያስተምርባቸው መንገዶች አንዱ

የሀገረሰብ ትውን ጥበባቱ ናቸው፡፡ ከነበሩት የተሻሉትን ፈልጓቸው የሚጠበቅባቸው፣ ጠብቆም የሚያስተላልፍባቸው መንገዶቹ ናቸው፡፡ ሰው ሲበድል መፍትሔውን ከማን? እንዴት? የት? እንደሚያገኝ የሚያሳዩት የሀገረሰብ ሃይማኖቱ ትወናዎች ናቸው፡፡ ችግሩንና መከራውን ለመርሳት የሚጠቀምባቸው ሀገረሰብ ጭፈራዎቹ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማምለጫ መንገዱን ያሳዩታል ማለት ይቻላል፡፡

እንዲሁም ከተፈጥሮ የተነፈጋቸውን፣ ከአካባቢው ያጣቸውን ፈልጐም ሊያገኛቸው ያልቻላቸውን ነገሮች የሚያገኝባቸው፣ ማንነቱን የሚያውቅባቸው፣ የእራሱን ስብእናም የሚገነባባቸው መንገዶቹ ሆነው ያገለግላሉ-ትውን ጥበባቱ፡፡ ለምሳሌ፣ የኑሮ አጋሩን፣ ተስማሚ ውሃ አጣጬን፣ በጥያቄ፣ በፍለጋ ብቻ ካጣት፣ የሀገረሰብ እምነቱ ባስተማረው መልኩ ገዳም ቀኖችን ጠብቆ፣ በባህሉ በተፈቀደው መሠረት በግርዘቱ ወቅት በሚተወነው ትወና አማካይነት፣ ብጤውን ለመማረክ እድል እንዳለው የተማረበት፣ ባህሉም እሱን የቀረፀበት መንገድ በትወናው ይገለፃል፡፡ በትወናው ራሱን ያውቃል፣ ብጤውን ያውቃል፣ ማህበረሰቡንም ይረዳል፡፡ የእሱን ተግባርና ግዴታዎቹን፣ ማህበረሰቡም ከእሱ የሚጠብቀውን ሁሉ የሚቀስመው በትውን ጥበባቱ አማካይነት ነው፡፡

በጥበባቱ ወጣቶች አስተሳሳባቸውን በምን መልኩ መግራት እንዳለባቸው ይሰለጥኑባቸዋል፡፡ ሀገረሰባዊው ትውን ጥበባት ልምዶቻቸውን የሚያስተላልፉባቸው፣ እውቀቶቻቸውን የሚጋሩባቸውም ናቸው፡፡ ህፃናቱ ከአካባቢያቸው ጋር የሚተዋወቁበት፣ የታላላቆቻቸውን ስሜቶች የሚገነዘቡበት፣ የቱ ነውር፣ የቱ የተገባ ተግባር፣ እንደሆነም በዘፈኖቻቸውና በጨዋታዎቻቸው ይቀስማሉ፡፡ የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸውን እንዴት፣ መቼ፣ የት መጫወት እንዳለባቸውም በዚሁ ይማራሉ፡፡ እንዲሁም የቋንቋ ችሎታቸውን የሚያዳብሩባቸው፣ የቁጥር ስሌቶችን የሚማሩበትም በዚሁ አማካይነት ነው፡፡ በደጅ እና በዱር በሚጫወቷቸው በጥልፍያ፣ በትግል እና በመሳሰሉት ጨዋታዎችም ጡንቻዎቻቸውን የሚያዳብሩበትና ማህበረሰቡን ከጠላት ለመጠበቅ የሚሰለጥኑባቸው ተግባራት ናቸው፡፡ ልጆች ንቁ፣ ቀልጣፋ እና ፈጣን ሆነው እንዲያድጉ፣ ስሜቶቻቸውን ለሌሎች እንዲያጋሩ የሚያደርጓቸውም ሀገረሰብ ትወናዎቻቸው ናቸው፡፡ በግፋታ ጨዋታዎቻቸው በጋራ የመስራት፣ አብሮ በመኖር፣ የመረዳዳትን ጠቀሜታ ያውቁባቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. ማጠቃለያ

የከምባታ ብሔረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መገለጫዎች በርካታ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት እንደታየው የብሔረሰቡን ማንነት የመሠረቱት ጐሣዎች በርካታ ናቸው፡፡

እነዚህ በርካታ ጐሳዎችም የየራሳቸው ባህል፣ እምነትና አስተሳሰብ የነበራቸው ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ከምባታነት የተመሰረተው ከተለያዩ ባህሎች፣ እምነቶችና አስተሳሰቦች ነው ማለት ይቻላል፡፡ የብሔረሰቡ መጠሪያ የሆነው ‹‹ከምባታ›› የሚለው ቃልም ትርጓሜ ይህንኑ የሚያመለክት ይመስላል፡፡ ለከምባቶቹ ይህ ቃል ‹‹እዚሁ ነን›› ‹‹ስፍራችን እዚሁ ነው›› የሚል ፍቺ ሲኖረው፣በሌላም በኩል፣ ‹‹ከም-ባታ››የሚለው በየት ትወጣለህ፤ ወይም እንዴት ታመልጣለህ፤ የሚል የኦሮምኛ ፍቺ መያዙን ደግሞ የብሔረሰቡ አባላት ይገልፃሉ፡፡ በጥናቱ እንደተጠቆመው የኦሮሞ ጐሳ አባላት የሆኑ ኦሮሞዎች - ከባሌ፣ ከአርሲ ከጊቤ ወዘተ. አቅጣጫዎች ወደ እዚህ ብሔረሰብ እየገቡ አብረው ይኖሩ እንደነበርና አሁን ከምባታነትን ተቀብለው እንደሚኖሩ ይታወቃል፡፡ የዚህ ቃል ትርጉምም በዚሁ አጋጣሚ ሳይሰርፅ እንዳልቀረ መገመት ይቻላል፡፡

በብሔረሰቡ የሚተውኑት ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎቻቸው፣ በባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች እና በተዋኞቹ ተፈጥሯዊ ድምፅ እንዲሁም በተዋኞቹ የተፈጥሮ ድምፆች ብቻ ነው፡፡ የሙዚቃ መሳሪያዎቹን በተለይም ባህላዊውን ከበሮ የሚጫወቱት ፉጋዎች /የእጅ ባለሙያዎች/ በከበሮ አጠቃቀማቸው፣ በአተዋወን ብቃታቸው፣ ለየዓውዱ ተስማሚ የሆኑ ሙዚቃዎችን ለማፍለቅ በሚያሳዩት የተለየ ብቃት፣ በብሔረሰቡ ዘንድ በተለይ እንደሚፈለጉ ተመልክቷል፡፡ በከምባቶች ዘንድ የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸውን ለመጫወትም ሁሉም የብሔረሰቡ አባላት ሳይሆኑ ለተለዩ ጐሳ አባላት የተተወ መሆኑንም ጥናቱ ያሳያል፡፡

የከምባቶች ሀገረሰብ ዳንስ ወይንም ውዝዋዜ ከሙዚቃዎቻቸው ጋር ወይም በተፈጥሮ ድምፆች ብቻ እንዲሁም በሁለቱም ቅንብር እንደሚቀርቡ በጥናቱ ታይቷል፡፡ ከምባቶችን በተለይ የሚገልጿቸው የግፋታ፣ የኤኤሬ፣ የባሊ ሄሌሌ እና የሆዬ ጨዋታዎች ከዚህ አንፃር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንደ ግፋታ ያሉት ጨዋታዎች ብሔረሰቡ ህዝባዊ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በዓላቱን፣ በጅጊ እና ደቦ በመሳሰሉት የቡድን ስራ በሚፈፀምባቸው አጋጣሚዎችም እንደሚተወኑ፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ ክብረ በዓላት ላይም የሚተወኑ ህዝባዊ ጨዋታዎች እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

በጥናቱ እንደታየው በእነዚህና በሌሎችም ሀገረሰባዊ ዳንሶች - የህዝቡ አተዋወን ተመሳሳይ መልክ ወይም ቅርፅ አለው፡፡ በሁሉም የከምባታ ሀገረሰብ ጨዋታዎችና ውዝዋዜዎች ማለት ይቻላል፣ ትወናው በአንገት፣ በእጅ፣ እና በወገብ አካባቢዎች በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ይቀርባል፡፡ አንገትን ወደ ላይ፣ ወደታች፣ ወደ ፊት ወደ ኋላ ከፍና ዝቅ፣ ወጋ ነቀል አይነት እንቅስቃሴ ይታይባታል፡፡ ጨዋታዎቻቸው በዙር መልክ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ክብ መልክ ያለው እንቅስቃሴ ማቅረቡንም ያዘወትራሉ፡፡ ይሄ በክብ፣ በዙር መልክ ውዝዋዜያቸውን የማቅረቡ ስርዓት የከምባቶቹ ዋነኛ መለያ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሀገረሰብ ሙዚቃቸውንና ዳንሳቸውን ስንመለከት በሩቅ ምስራቅ ህንድ አካባቢና በቅርብ አጐራባቻቸው የሃዲያ ብሔረሰብ ዘንድ የሚታይ ተመሳሳይ ቅርፅ አለው፡፡ በሃዲያ ‹‹ቦያ ሰሎሜ›› በሚባለው የአጨዋወት ስልት እንደሚታየው ወገብ ለወገብ ተያይዘው በአንድ መስመር ፊትና ኋላ ሆነው ከፊት ያለውን እና ከኋላ ያለውን የሚቆጣጠረው ሰው በሚያሳዩት ምሪት በመመራት የሚያሳዩት ጨዋታ በዙር የሚጠናቀቅ ነው፡፡ በእርግጥ አጀማመሩ በመስመር፣ በጥልፍልፍ መስመር ሆኖ ክቡን ሲጨርስ ነው፡፡ ይህንኑ የሚመስለው የከምባቶቹ ‹‹ባሊ ሄሌሌ›› እና ሆዬ ጨዋታዎች ይህ የጋራ ፀባይ ይታይባቸዋል፡፡ በእርግጥ የቃል ታሪክ አዋቂዎቹ እና በብሔረሰቡም ዘንድ በትወና ችሎታቸው የሚታወቁት አቶ ወልደ መስቀል እና አቶ ወርቁ እንደሚገልፁት የሃዲዮቹ ባህላዊ ጨዋታ በመጀመሪያ ‹‹የእኛ›› ነበር አሁን አሁን እነሡ እንደራሳቸው እየቆጠሩት በየመገናኛ ብዙኂኑ እያቀረቡት ስለሆነ እኛ እየተውንላቸው ነው ይላሉ፡፡ እነዚህን መሰል ልዩነቶች ለማጥናት ንፅፅራዊ ጥናት /Comparative study/ የሚያስፈልገው ነው፡፡ ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት አንፃርም ይሄ ስላልሆነ በመጠኑ ይህን ያህል ከተባለ ወደ ሚቀጥለው እንለፍ፡፡

የከምባቶች ሀገረሰብ ድራማ እራሱን ችሎ ለብቻው የቆመ አይደለም፡፡ የሀገረሰብ ሙዚቃዎቻቸውን ሲጫወቷቸው፣ ወይም የሀገረሰብ ዳንሶቻቸውን ሲያቀርቧቸው፣ ወይም መነባንብ፣ ታሪክን በመተረክ፣ ቀልዶችን በግጥም መልክ በማቅረብ በመሳሰሉት

አጋጣሚዎች የሚተወኑ ናቸው፡፡ ለዚህ ጥናት የተሳተፉት ተዋኞች ሲደንሱ ተውኔታዊነት /ድራማዊነት/ ያለው እንቅስቃሴ ነው የሚያቀርቡት፡፡ ሰውነታቸውን ሲያወዛውዙት፣ በዓይናቸው እና የአፋቸውን (የከንፈራቸውን) ቅርፅ በመቀያየር ተውኔታዊ ትእይንት ያቀርባሉ፡፡ እንዲሁም እንደ አቶ ደስታ ያሉት መነባንብ አቅራቢዎች ደግሞ የድምፃቸውን ቅላፄ /tone/ በመለዋወጥ ከፍ፣ ዝቅ፣ ጫን፣ ረገብ፣ ጐርነን፣ ለስለስ በማድረግ ለቃል ግጥሞቻቸው ትእይንታዊ ባህሪይ ያለብሱታል፡፡ አንገታቸውን፣ ግንባራቸውን ወዘተ. በማወዛወዝና በመቋጠር - በመፍታትም ለተመልካቾቹ አዝናኝ የሆነ እንቅስቃሴን ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን ራሱን ችሎ ድራማን በድራማነቱ መተወን አላጋጠመም፡፡ በቃለመጠይቅ እንደተገኘው መረጃም ይህን የተመለከተ የተለየ ሃሳብ አልተገኘም፡፡የከምባቶቹ ሃይማኖታዊ ትወናዎችም የመቀላቀል ባህሪይ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ብሔረሰብ ውስጥ ሀገር በቀሉም ታሪካዊውም ሃይማኖቶች መሳ ሆነው ይተወናሉ፡፡

የሀገር በቀል ሃይማኖታቸው መሠረቱ ከሁለት ዘሮች ይመነጫል፡፡ የመጀመሪያው ሀገረሰብ ክርስትና ነው፡፡ ይህ ሃይማኖት ከአይሁድ እምነት የተወረሱትን የተራራ ላይ አምልኮ፣ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በዚህ አምልኮ መሠረት ተራራ፣ የሥልጣን፣ የሃይል የመናፍስት ወዘተ. ተምሳሌት ሆኖ ይቀርባል፡፡ የከምባቶቹ አምበሪቾም የነገስቱ መንበር የነበረ፣ የአማልክቶቻቸው ማደሪያ የነበረ፣ የአምላካቸው መገኛ የነበረ ተደርጐ ስለሚታመን ለዚሁ እምነት የአምልኮ ስርዓት ይቀርባል፡፡ ይህም አምልኮ በቦታው ይመለኩ ለነበሩ ካህናትና ሊቀ ካህናት ‹‹መገናንቾ›› እና ‹‹አባሰሪቾ›› በየጊዜው የሚቀርቡ ነበሩ፡፡ በተራራው ላይ ፀሎት ማድረግ፣ ስግደት፣ አምልኮዎች፣ ልዩ ልዩ ከበራዎችና መናፍስቱን የመማፀን ስርዓቶች የተለመዱ ነበሩ፡፡

በተጨማሪም በአምበሪቾ ላይ ከነገሥቱ በተራራው አምልኮ ወቅት፣ አማልክቱ በተገኙበት በተመላኪ መገናንቾ፣ አባሴርቾ ይቀቡ ነበር የሚለው ትረካም ከዚህ ጋር አብሮ ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ በአምበሪቾ ተራራ ላይ የመቀባት አምልኳዊ ስርዓት ይፈፀም እንደነበር በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪ ይህ ሃገረሰብ ክርስትና አምልኮ በከምባታ ብሔረሰብ ዘንድ ግፋታ የተባለውን ባህላዊ ጨዋታ እየጫወቱ መተወናቸውም ተጠቅሷል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ከሀገረሰብ እስልምና ጋር የተያያዘው ሀገር በቀል ሃይማኖትም ሌላው ገፅታ ነው፡፡ በከምባቶቹ ሃገር በቀል ሃይማኖት እንደተጠቀሰው የፌንዳኖ እምነት ምንጩ ከዚህ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ይህ ፌንዳኖ የሚለው ሃገረሰብ ሃይማኖት በመጀመሪያ በሃዲያ አካባቢ የነበረና በኋላ ሽሪፍ በሚባል የሙስሊም ሼክ አማካይነት ወደ ከምባታ የገባ እንደሆነ ተደርጐ ይጠቀሳል፡፡ ሃይማኖታዊ ስርዓቱም በዚያው ልክ የተዋሃደ እንደሆነ ለመገመት አይከብድም፡፡ ይህ ከሃዲያ ገባ የሚባለው የፌንዳኖ ሃይማኖት ልክ እንደ ሃገረሰቡ ክርስትና ሁሉ የተራራ ላይ አምልኮን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ የአምልኮ ስርዓትም በአምበሪቾ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

እንደ ሀገረሰብ ክርስትናው ሁሉ ግፋታ የተሰኘውን ጨዋታ እዚህም ላይ ይተወናል፡፡ መስዋእት ማቅረቡ፣ ፀሎቱ፣ ምልጃው ወዘተ. ሁሉ አብረው የሚቀርቡበት ነው፡፡ ህዝቡ ስግደቱን የሚያቀርብበትም በዚሁ የአምልኮ ስርዓት ላይ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ተዓምራትና ትንቢቶች የሚታዩባቸውም አጋጣሚ አለ፡፡ ከሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ችሎታ በላይ የሆኑ በእሳት ላይ መራመድ፣ ዝናብ እንዲያዘንብ መፀለይና ይህም ሲፈፀም ማየት በዚህ አምልኳዊ ትወና ላይ ይጠብቁ ነበር፡፡ አሁን ግን በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ስርዓቶች ተለውጠዋል ይላሉ፡፡ ከአምልኳዊው ስርዓት መልስም በቦታው ከሚገኘው የተመላኪው አፀድ ላይ ቀንበጦችን እየቀነጠሱ መውሰድና በክርስትናው እምነት የሚሉትን አይነት ስርዓት መፈፀምም የተለመደ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለሙታን ዓያት ቅድመ ዓያቶቻቸው መናፍስት የሚቀርበው የፀሎትና የምልጃ ስርዓቶችም ከዚሁ የተቀዱ ናቸው፡፡ እነሱን ለማስደሰት የሚደረጉት የአምልኮ ስርዓቶችም ቢሆኑ የዚህ ነፀብራቅ ናቸው፡፡ በህልም የሚታዩ ዘመድ አዝማዶች አሉ፤ አልሞቱም የሚለውና ለዚህ መገለጥም የሚደረገው የምግብ፣ የመጠጥ መስዋእት ማቅረብ ስርዓት አብሮ የሚታይ ነው፡፡ በመሆኑም የከምባታ ሀገረሰብ ሃይማኖት ከታሪካዊዎቹ ሃይማኖቶቹ የአምልኮ ስርዓቶች ጋር የሚተወኑት፣ ትወናዎቹም ተመሳሳይ መሆን ከዚሁ በፈለቀ ምክንያት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

በከምባታ የልደት፣ የሠርግ፣ የግርዘት እና የሞት ወቅት ትወናዎችን በተመለከተም የሚከተሉት ዋና ዋና ሃሳቦች ተነስተዋል፡፡ በሁሉም ማለት ይቻላል፣ የከምባቶቹ አተዋወን ተመሳሳይ ነው፡፡ ዋና ዋና ጨዋታዎቻቸውን ሲተውኗቸው በተመሳሳይ

መልኩ ነው። ሴቶችና ወንዶች፣ በጋራ ወይም ለየብቻ በመሆን ጨዋታዎቻቸውን ይጫወቷቸዋል። የአጨዋወት ስልታቸውም በተመሳሳይ መልኩ ወገብ ለወገብ በመያያዝ፣ በአንገት፣ በእጅ እና በወገብ እንቅስቃሴዎች ላይ የተመሰረተ ነው።

የጨዋታዎቻቸው ትወናዊ ቅርፅም ክብ ነው ካልነው አይለይም። በዝግታ ወደ መሬት መቅረብ እና ከሬት ወደ ላይ መነሳትን ያመለክታሉ። የዚህ ተምሳሌታዊ ፋይዳም በኢኔሬ ጨዋታ እንዳመለከትነው የመነሳት፣ የመውጣት፣ ከፍ የማለት ትእምርታዊ ፋይዳ ያለው ነው። በሴቶቹ ብቻ ይተወናል የሚባለውና ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚተወነው የቄኔፋ አተገባበርም ወሲባዊ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን በመጠኑ ከሚያመለክተው ውዝዋዜ እና ምንም አይነት ወንድ ስለማይሳተፍባቸውም የሴቶቹ ነፃ የመዝናኛ ምሽት ከመሆኑ ውጪ በአተዋወኑ ላይ የተለየ ነገር አይስተዋልም።

በአጠቃላይ የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አንደኛ ቡድናዊ፣ ወይም ማህበራዊ ባህሪይ ያላቸውና በጋራ የሚተወኑ መሆናቸውን፣ ሁለተኛ በተናጠል ወይም በግል አቀንቃኝና ተቀባይ የሚተወኑ ትወናዎች በብሔረሰብ ዘንድ እጅግ ጥቂት መሆናቸው ተመልክቷል። ትውን ጥበባቱ የማህበረሰቡ አባላት የሚማሩባቸው፣ የሚዝናኑባቸው፣ ታሪካቸውንና ማንነታቸውን የሚገልፁባቸው፣ የሚግባቡባቸውና የሚያመልኩባቸው መሆናቸውም ተዳሷል። በቅርፅ ረገድም የከምባቶቹ ሀገረሰብ ትውን ጥበባት በክብ የሚከወኑ ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

## የማጣቀሻ ጽሑፎች (References)


ተስፋዬ ሀቢሶ፤ 1986፤ ‹‹ከምባታና ሀዲያ የአስተዳደር አካባቢና የብሔረሰቦች ታሪክ አንዳንድ ገጽታዎች››፤ አዲስ አበባ፣ ተጠርዞ የተሰናዳ፡፡

ታገሠ ሀሊቦ፤ 1989፤ ‹‹የለቅሶ ስርዓት በከምባታ ህዝቦች››፤ ከምባታ አላባ ጠምባሮ ዞን ባህልና ማስታወቂያ መምሪያ፤ ያልታተመ፡፡

ኃይለ ዳንኤል ማግቾ፤ 1986፤ ‹‹የከምባታ ብሔረሰብ ባህል››፤ በተስፋዬ ሀቢሶ፤ 1986፤ ‹‹ከምባታና ሀዲያ የአስተዳደር አካባቢና የብሔረሰቦች ታሪክ አንዳንድ ገጽታዎች››፤ አዲስ አበባ፣ ተጠርዞ የተሰናዳ፡፡

አርቲንግ ደጉ፤ 1995፤ ‹‹የከምባታ ብሔረሰብ የሠርግ ስርአትና ግጥሞች››፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ዲማጽ[32]፤ ያልታተመ፡፡

ወርቁ ጌጅባ፤ 1991፤ "የከምባታ ጎሳዎች ዝርዝር"፤ In Belachew Gebrewold Tochale.2001."The Impact Of Socio Cultural Structure Of The Kembata /Ethiopia/ On Their Economic Development." Germany. University of Hamburg.

የከምባታ ጠምባሮን ዞን፣ ማስታወቂያና ባህል መምሪያ፤ 1996፤ አምበሪቾ፤ ቅፅ 1፣ ቁጥር 1፣ ግንቦት 1996 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

____________፣ 1997፤ አምበሪቾ፤ ቁጥር 2፣ የካቲት 1997 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

____________፣ 1998፤ አምበሪቾ፤ ቁጥር 3፣ ሚያዚያ 1998 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር፤ 1990፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የባህል ፖሊሲ፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደስታ ሎሬንሶ፤ 1987፤ ‹‹የከምባታ ህብረተሰብ ባለእጆችና ስነቃላቸው››፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ዲማጽ፤ ያልታተመ፡፡

ደስታ ገብረ ሚካኤል፤ 1963፤ ‹‹የከምባትኛ ተረትና ምሳሌዎች››፤ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ዲማጽ፤ ያልታተመ፡፡


---

[32] ዲማጽ፣ የ‹‹ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ›› የሚለውን ለማሳጠር የገባ ነው፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ደስታ ፀደቀ፤1981፤“ኢከምባትኛስሞች በከምባታ ማህበረሰብ»፤አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለትምህርት፤ዲማፅ፤የልታተመ።

ዳንኤል ካቢሶ፤ 1982፤ ‹‹የግርዛት ስርዓት በከምባታ››፤ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ ጥር 19 ቀን፣ 1982 ዓ.ም፣ ገጽ 9።

ፈቃደ አዘዘ፤ 1988፤ ‹‹የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ስነቃል ጥናት ቅኝት››፤ የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የስነጽሁፍ መጽሔት፤ ቁጥር 6፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፤ ገጽ 1-28።

______________፤ የስነቃል መምርያ፣ በኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት ተቋም፤ አዲስ አበባ አልፋ አታሚዎች፣ 1992፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመፃህፍት ማእከል።

ፍሬህይወት አድነው፤ 1997፤ ‹‹ከምባቶመት›› ፥ የከምባታ ፎክሎር ይዞታና ለውጥ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፤ ኤም. ኤ. ዲ.ማ.ጽ፤ ያልታተመ።

Adams, Robert. 1973. Introduction to Folklore, Colombus, Ohio: Collegiate pub. Inc.

Bahru Zewde (ed.). 1998. A Short History of Ethiopia and the Horn. Addis Ababa University, Department of History. A.A: Commercial Printing Press.

Bascom, William. A 1965. *The Foms of Folklore*: Prose Narratives, in Journal of American Folklore 78, P. 3-20.

Bassett, Fletcher S. 1973. *The Folklore Manual*. Chicago Folklore Society. Chicago, icc.

Bauman, Richard . 1984. *Verbal Art as Performance*. Prospect Heights, IL: Waveland Press, Inc.

______________. 1986. *Story, Performance, and Event*: Contextual Studies of Oral Narrative. Cambridge: Cambridge University Press.

______________. 1991. *Genre in Folklore, Cultural Performance, and Popular Etertainment*: A Communications-centered Handbook. Oxford: Oxford University Press.

Beeman, William O. 1986. *Language, Status and Power in Iran*. Bloomington: Indiana University Press.

____________.1993. *The Anthropology of Theater and Spectacle*. Annual Review of Anthropology. Bloomington: Inndiana University Press.

Belachew Gebrewold-Tochalo. April 2001. "*The Impact of Socio Cultural Structure of the Kembata (Ethiopia) on their Economic Development.*" Ph.D Dissertation 'Germany: University of Hamburg.

Ben-Amos, Dan. 1977. "*Towards a Definition of Folklore in Context*". In A. Parades and Richard Dorsen (eds.), Towards New Prospective in Folklore. Austin: University of Texas Press (For the American Folklore Society).

Berhanu Mathewos. 1986. "*An Analysis of Kembata Proverbs*". M.A. Thesis. School of Graduate Studies, Addis Ababa University.

BrauKamper, Utrich, 1983. *Die Kambata: Geschichte und Gesellschaft easies.* Sii da thi opischem Bauern volkes. Wies baden: Frang Steiner Verlag.

Dorsen, Richard M. (ed,). 1972. *Folklore and Folk life: An Introduction.* Chicago and London: The University of Chicago Press.

____________. (ed.). 1986. *Handbook of American Folklore*. Bloomington: Indiana University Press.

Dundes, Alan (ed). 1965. *The study of Folklore*. English Wood Cliffs, N.J: Printice Hall, inc.

____________. 1980. *Interpreting Folklore*. BloomIngton: Indiana University Press.

____________. 1984. *Sacred Narrative*: Readings in the Theory of Myth. Berkeley: University of California Press.

Finnegan, Ruth. 1970. *Oral Literature in Africa* Oxford: Clarendon Press.

Glassie, Henry. 1993. *Turkish Traditional Art Today*. Bloomington: Indiana University Press.

____________. 1995. *A Tradition, in Common Ground*: Key Words for the Study of Expressive Culture, ed. Burt Feintuchy, Journal of American Folklore Vol. 108, Number 430: 395-412.


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

____________. 1999 (b) Matereal Culture. Bloomington: Indiana University Press.

Goldstein, Keneith. 1964. A Guide for Field Workers in Folklore. Hatboro: Folklore Associates, Inc.

Grenstedt, Staffan. 2000. "*Ambaricho and Shonkolla*: From Local Independent Church to the Evangelical Main Stream in Ethiopia. The Origins of the Mekane Yesus Church Kembatta and Hadiya". Uppsala University: The Faculty of Theology. Ph.D dissertation. Sweden: Glandersgotab, Stockholm.

Handebo Ergano. 1982, "*The Family System of the Nationality of Kembatta.*" A.A. Addis Ababa University. Senior Paper in Sociology. Unpublished.

Magoulick, Mary. 2003. "*Folklore Field work*: Ethnography and Performance Theory." http.www.//A:\Folklore.htm.

Mulugeta Eyoel, 2001. "*Ethnic Relations and Socio Cultural change among the Danta*" *(Dubamo)*. Of Southern Ethiopia. "M.A. Thesis. School of Graduate Studies. A.A.U.

Mulugeta Jaware — Dolasso. *A Preliminary Classification and Descriptive Study of Oral Narrative:* The case of Dubamo. "Tarika". M.A. Thesis, School of Graduate Studies, A.A.U.

Okpewho, Isidore. 1992. African Oral Literature: Backgrounds, Character and Continuity. Bloomington and Indiana Polis: Indiana University Press.

Peredes, Americo and Richard Bauman (ed.) 2000. Towards New Perspectives in folklore. Bloomington: Trickster Press. Addis Ababa University College of education School of Graduates. MA Thesis (unpublished)

Schechner, Richard. 1988. Performance Theory. London and New York: Routledge.

____________. 1990. Magnitudes of Performance; By Means of Performance: Inter Cultural Studies of Theatre and Ritual ed. Richard

Schechner and Willa Apple; Cambridge; Cambridge University Press.

______________. 1993: The Future of Ritual. London and New York: Routledge.

Schoemaker, Goerge H. 1990. The Emergence of Folklore in Everyday Life, Bloomington, Indiana: Trickster Press.

Singer, Norman J." 1977. *Some notes on the Origin of the Cambata of Southern Shoa"* London:School of Oriental and African Studies./ paper presented Ethiopian origins, conferance held at SOAS, University of london.28-29 June, 1977./

Taggese Halibo. 1995. "*Indigenous Marriage Practices Among the Kamabata People of Kachabira woreda*". A.A. University. Senior Paper in Sociology Department. UP.

Teketel Abebe. 1985. *"A Study of the Socio-economic Conditions of Fuga.* (a low-caste occupational group) with Particular Reference to Kambatta. A.A. University: Senior Paper in Sociology. UP.

Tesfaye Habiso. 1987. "*Some Records of South West Ethiopia Land a Short History of Kambatta and its People.*" Addis Ababa. UP.

Tesfaye Sadebo. 1984. "*Mourning and Burial Customs Among the Kambattas."* Addis Ababa University. Senior Paper in Sociology.

The New Encyclopedia Britannia. Micro Pedia. 1985. Vol.4. 15th Edition. Chicago: Encyclopedia Britannica Inc. PP. 861.

Turner, Victor . 1986. The Anthropology of Performance. New York: PAJ Publications.

______________. 1982. *From Ritual to Theater:* The Human Seriousness of Play. New York: PAJ Publication.

Woldesellassie Abute. 1984"*Kambatta Folktales*". Addis Ababa University. Senior Paper in Foreign Languages and Literature. UP.

______________. 2001. "*Kambatta*" in Dena Freeman and Alula Pankhurst (eds.) Living in the edge Marginalized Minorities of Craft Workers and Hunters in Southern Ethiopia. Addis Ababa University. Department of SOSA. PP. 16-72.

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

Yakob Arsano. 2002. "*Seera: a Taditional Institution of Kambatta*". In Bahru Zewde and Sieg Fried Dause Wang (eds.). Ethiopia: The Challenge of Democracy From Below. Nordiska Africa Institute, UPPSALA and Forum for Social Studies, Addis Ababa Sewden: Elanders Gotab, Stock holm. Pp.45-58.

Zeleke Sendabo. 1995. "*The Educational Value of Kambatta Riddles.*" Addis Ababa University. Senior Paper in Foreign Languages and Literature. UP.

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አባሪዎች

1. ጥቅሶች በመጥገኛ ቋንቋቸው

- *I see folklore as an action. My argument here is that this kind of focus on the doing of folklore, that is, on folklore performance, is the key to the real integration between people and lore on the empirical level. This is to conceptualize the social base of folklore in terms of the actual place of the lone in social relationships and its use in communicative interaction (Bauman, 1972, 16)*

- *It is possible ... to define both folk and lore in such a way that even the beginner can understand what folklore is. The term "folk" can refer to any group of people what soeuer who share at least one common factor. It does not matter what the linking factor is ... it could be a common occupation, language or religion ... but what is important is that a group formed for what ever reason will have some traditions which it calls its own. (Dundes, 1965, 32)*

- *Recognize that the symbolic forms we call folklore have their primary existence in the action of people and their roots in social and cultural life. The texts we are accustomed to viewing as the raw materials of oral literature are merely the thin and partial record of deeply situated human behavior. My concern has been to go beyond a conception of oral literature as disembodied super organic stuff and to view it contextually and ethnographically, in order to discover the individual, social and cultural factors that give it shape and meaning in the conduct of social life. (Bauman, 1986, 2)*

- *The emergent quality of performance resides in the inter play between communicative resources, individual competence, and the goals of the participants, with in the context of particular situations ... Relevant here are the keys to performance, genres, acts, events and ground rules for the conduct of performance that make up the structured system of conventionalized performance for the community. (Bauman, 1977, 15)*

- *Analytic — the performer must assess the task and what she/he needs to accomplish to achieve successful representation.*
- *Technical — the performer must develop the necessary motor skills to actually carry out the per formative activity.*
- *Interpretive — the performer must develop a method to making the performtive activity uniquely their own*

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

*— an embodiment of their own skill. (Beeman, 1993, 202)*

*- Flow is the experience of loss of sense of the physical body or of conscious control of one's own actions when one becomes totally engaged in a given activity. This typically takes place when the activity is not so familiar as to be boring, and not so challenging as to be anxiety producing. (Beeman, 1986, 202)*

*- The "force" of a social drama consists in its being an experience or sequence of experience which significantly influences the form and function of cultural performative genres. Such genres partly "initiate (by mimesis), the processual form of social drama, and they partly, through reflection, assign "meaning" to it. (Turner, 1986: 95).*

*- Those folklorists attendant to performance theory offer relatively full contextual pictures of the community in which they work. Those contexts aid our understanding of particular narratives or other expressive forms. Remember that folklore embodies synthesis of the "folk" and the "lore" ultimately; all of culture and humanity share these foci of folklore creativity and society. (Magoulick, 2003, 3).*

*-In summary, it may be said that almost every known culture involves the religious in the above sense of a depth dimension in cultural experiences at all levels — a push, whether ill-defined or conscious, toward some sort of intimacy and transcendence that will provide norms and power for the rest of life. When more or less distinct patterns of behavior are built around this depth dimension in a culture, this structure constitutes religion in its historically recognizable form. Religion is the organization of life around the depth dimensions of experience — varied in form, completeness, and clarity in accordance with the environing culture. (Winston King, Encyclopedia of Religion, p. 7693)*

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## II. የመረጃዎች መግለጫ

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡት መረጃዎች በሦስት መንገዶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም በቪዲዮ የተቀረጹ፣ በቴፕ የተቀዱ እና የፎቶ ካሜራ የተወሰዱ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የመጃዎቹ ብዛትም 5 ቪዲዮ ካሴቶች፣ 8 ኦዲዮ ካሴቶችና 3 ፊልሞች ሲሆኑ በተጨማሪ 8 ፍሎፒ ዲስኮችም አባሪ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በእያንዳንዳቸው ላይ የሚገኙት መረጃዎችም እንደሚከተለው የቀረቡ ናቸው፡፡

1. በቁጥር አንድና ሁለት ካሴቶች ላይ በ23/3/99 ዓ.ም የተቀዳ ቃለ መጠይቅ እና ትወናን ይዟል፡፡ በዚህ ካሴት ላይ የቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ነዋሪዎች የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎችና የብሔሰቡን ውዝዋዜዎች ለሚችሉ አራት ሴቶች እና ሰባት ወንዶች በድምሩ ለ11 ሰዎች የተደረጉ ቃለመጠይቆችን ይዘዋል፡፡ የቃለ መጠይቆቹ ይዘትም ስለከምባታ ብሔረሰብ ባህል፣ ከየትመጣና ታሪኩ የተደረጉ ጥያቄዎችና መልሶች፣ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የብሔረሰቡ የልደት፣ የሠርግ፣ የግርዘት እና የሞት ወቅት አተዋወኖች ሲተወኑ ተቀርፀው ይገኛሉ፡፡
2. በቁጥር ሦስት እና አራት ቪዲዮ ካሴቶች ላይም በተመሳሳይ ቀን የተቀረጹ እና በተመሳሳይ ርእስ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ቃለ መጠይቆችና ትወናዎች ተቀርፀውባቸው ይገኛሉ፡፡
3. በተራ ቁጥር አምስት እና ስድስት ቪዲዮ ካሴቶች ላይ ደግሞ በ28/4/99 ዓ.ም በዱራሜ ከተማ፣ በዞኑ ማስታወቂያና ባህል ቢሮ ቅጥር ግቢ ውስጥ በተደረገው የመረጃ ማሰባሰብ ሂት የተሳተፉት ሰባት የሃገር ሽማግሌዎችና ቃለ ታሪክ አዋቂዎች የሰጡት የቃለምልልስ እና በተግባር የተተወኑ የሀገረሰብ ውዝዋዜዎችን ይዘው ይገኛሉ፡፡ በቪዲዮ ካሴቶቹ ላይ እንደ ተመለከተው የእያንዳንዱን መረጃ አቀባይ ማንነት፣ የሚገልፅ ፅሁፍ አብሮ እንዲቀርብ በመደረጉ ለመለየት ቀላል ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡
4. ኦዲዮ ካሴት አንድ በ 23/3/99 የተደረገ ቃለ ምልልስን ይዟል፡፡
5. ኦዲዩ ካሴት ሁለት በ23/3/99 የተደረገ ቃለ ምልልስና የትወናውን ሂደት በድምፅ ብቻ ይዞ ቀርቧል፡፡

6. ኦዲዮ ካሴት አራት እና አምስት በዞኑ ማህበረሰብ ዘንድ ታዋቂ የሆኑት አቶ አድነው፣ ወ/ሮ አዳነች፣ አቶ ወርቁ፣ አቶ ፊሊጶስ እና አቶ ምህረቱ ስለ መስቀል በዓል አከባበር የሰጡት መረጃ ይገኝበታል።
7. በኦዲዮ ካሴት ስድስት እና ሰባት በ28/4/99 ዓ.ም በዞኑ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተደረገውን ቃለመጠይቅና ትወና በድምፅ የያዙ ናቸው።
8. ፍሎፒ አንድ፣ ሁለት እና ሦስት በ23/3/99 ዓ.ም በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ የተደረገውን የቃለ መጠይቅ እና የትወና ተግባራት በምስል ያሳያሉ።
9. ፍሎፒ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት እና ስምንት ደግሞ በ28/4/99 ዓ.ም በከምባታ ጠንባሮ ዞን ማስታወቂያና ባህል መምሪያ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተደረጉትን ቃለ መጠይቆችና በእያንዳንዱ ትወና ወቅት የተነሱትን ትወናዎች ይዘው የሚገኙ መረጃዎች ናቸው።

በቪዲዮ ካሴቶች እና በፍሎፒ ዲስኮቹ ላይ የሚገኙት መረጃዎች በሙሉ ቃለ መጠይቆቹም ሆኑ የተቀረጹት ክወናዎች በሙሉ መቼ እንደተደረጉ እና እንደተቀረጹ ስለሚያመለክቱ ተጨማሪ ጥናት ለማድረግ ለሚነሱ አጥኚዎች ግልጽ መረጃዎች የያዙ መሆናቸውን በተጨማሪ መግለጽ ይቻላል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## III. የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የአቀባይ ሁኔታ መረጃ | | | | | | | የመረጃው ዓይነትና አሰባሰብ | | | | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ስም ከነ አባት | ፆታ | እድሜ | የት/ደረጃ | አድራሻ | ስራ | ሃይማኖት | ቀን | ስፍራ | ርእስ ጉዳይ | መሣሪያ | |
| 1 | አቶ ኡታሎ ኤጄቴ ኩማሌ ዋቆ | ወ | 80 | መ.ት | ቀዲዳ ጋሜላ | ገበሬ (ንጉሥ) | ክርስቲያን ፕሮቴስታንት | 28/4/99 | ዱራሜ | ስለ ከምባታ ታሪክ ባህልና ሃይማኖት ስለ ክብረ በዓላቱ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በዞኑ ባህል ቢሮ ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅ |
| 2 | አቶ ሻትመሎ ደንታሞ ሰንቤቦ | ወ | 78 | 7 | አንገጫ | ገበሬ ቃል ገጣሚ | ክርስቲያን ፕሮቴስታንት | 28/4/99 | ዱራሜ | ስለ ከምባታ ባህል፣ ሃይማኖትና የለቅሶ ስርዓት ጌዳ፣ አረጃ፣ ድራንቻ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በዞኑ ባህል ቢሮ ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅ እና ክወና |
| 3 | አቶ ኤር ሲዶ ሚኮሮ ማሎሮ | ወ | 80 | - | ቀዲዳጋሜላ | ገበሬ ታሪክ አዋቂ | በፊት እስላም የነበሩ አሁን ፕሮቴስታንት የሆኑ | 26/3/99<br>28/4/99 | ዱራሜ | ስለ ታሪኩ፣ ባህሉ፣ ሃይማኖቱ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በዞኑ ባህል ቢሮና በቀዲዳ ጋሜላ አስተደደር ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅና ክወና |
| 4 | አቶ አብሶ አርጃኖ ኦልበሞ | ወ | 66 | - | ደንቦያ | ገበሬ | ክርስቲያን ኦርቶዶክስ | 28/4/99 | ዱራሜ | ስለ ከምባታ የቃል ታሪክ፣ የቃል ግጥም፣ የለቅሶ እወጃ፣ ሽለላና ቀረርቶ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በዞኑ ባህል ቢሮ ግቢ የተደረገ ቃለ መጠይቅና ክወና |
| 5 | አቶ ደስታ ደንታሞ ዲመንሶ | ወ | 59 | - | ቃጫቢራ | ገበሬ | ክርስቲያን ፕሮቴስታንት | 28/4/99 | ዱራሜ | የቃል ግጥም አዋቂና መነባንብ አቅራቢ ስለ እንስት ጥቅም በግጥም ያቀረበ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በዞኑ ባህል ቢሮ ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅና ትወናው የተቀረፀበት |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | አቶ ወርቁ ጌደባ ጋዜና | ወ | 46 | ዲፕሎማ በዚህ ዓመት ዲግሪ የሚይዝ | ዱርሜ | ጋዜጠኛ ታሪክ አዋቂ | ክርስቲያን ፕሮቴስታንት | 28/4/99 | ዱራሜ | ታሪኩን፣ ባህሉን ሀገረሰብ ጨዋታዎችን ያስተረጐመና የከወነ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በዞኑ ባህል ቢሮ ግቢ እና አዲስ አበባ በአጥኚው ቤት ቃለመጠይቅ |
| 7 | አቶ ወ/መስቀል እስጢፋኖስ ለሬቦ | ወ | 46 | 12 | ዱራሜ | ሪፖርተር ዘፋኝ ከዋኝ | ክርስቲያን ኦርቶዶክስ | 28/4/99 | ዱራሜ | የከምባታን ባህላዊ ጨዋታዎችና ታሪካቸውን በክዋኔ ያቀረበ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በዞኑ ባህል ቢሮ ግቢ ውስጥ በቃለመጠይቅና በክወና የተቀረፀ |
| 8 | አቶ ዶጊሶ ጊንጆ ጉዶ | ወ | 90 | - | ዱራሜ | ገበሬ | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | ስለ ፊንዳኖ ሃይማኖት ስርዓትና ስለ ታሪኩ የገለፁ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ አስተዳደር ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅና ክወና የተቀረፀ |
| 9 | አቶ ወናቅ ጠቦሌ ጉሌ | ወ | 70 | - | ዱራሜ | ገበሬ | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | ስለ አምበርቾ ታሪክና በዚያ ስለሚደረገው አምልኮ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ አስተዳደር ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅና ክወና የተቀረፀ |
| 10 | አቶ ቀልቢሶ መኮ ደጋሞ | ወ | 100 | - | ዱራሜ | ገበሬ | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | የከምባታን ታሪክ ባህላዊ ጨዋታዎችንና ስርዓቶችን የገለፁ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ አስተዳደር ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅ |
| 11 | አቶ ደቦጭ ቲሮሬ ኩማዬ | ወ | 81 | - | ዱራሜ | ገበሬ | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | የለቅሶ /ኦናታ/ ስርዓትን የገለፁ እና የተወኑ | በቪዲዮ በቴፕ በካሜራ | በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ አስተዳደር ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅና ክወና |
| 12 | ወ/ሮ አዳነች አሻንጉ አላሮ | ሴ | 40 | - | ዱራሜ | ገበሬ የቤት | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | ስለ ልደት ስርዓትና | በቪዲዮ | በቀዲዳ ጋሜላ |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | እመቤት | | | | ስለቴኔፋ አጨዋወት የገለፁ፣ የተወኑ | በቴኘ በካሜራ | ወረዳ አስተዳደር ግቢ የተደረገ ቃለመጠይቅና ክወና |
| 13 | ወ/ሮ ወርቂ ሃምዛ ሪጃቶ | ሴ | 52 | - | ዱራሜ | ገበሬ የቤት እመቤት | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | ስለ ቦሎቻ(ሠርግ) ባህላዊ ስርዓትና አከዋወኖቹን ያሳዩ | በቪዲዮ በቴኘ በካሜራ | በቀዲዳ አስተዳደር ግቢ በቃለ መጠይቅና በትወና የተሳተፉ |
| 14 | ወ/ሮ ወ/መስቀል ዲልበቶ | ሴ | 45 | - | ዱራሜ | ገበሬ የቤት እመቤት | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | የከምባታን ልዩ ልዩ ጨዋታዎች የተወኑና የገለፁ | በቪዲዮ በቴኘ በካሜራ | በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ አስተዳደር ግቢ በቃለ መጠይቅና በትወና የተሳተፉ |
| 15 | ወ/ሮ አማሶ ሚግሶ ሄቦ | ሴ | 70 | - | ዱራሜ | ገበሬ የቤት እመቤት | ክርስቲያን | 26/3/99 | ቀዲዳ | የከምባታን ልዩ ልዩ ጨዋታዎች የተወኑና የገለፁ | በቪዲዮ በቴኘ በካሜራ | በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ አስተዳደር ግቢ በቃለ መጠይቅና በትወና የተሳተፉ |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY